ሕፃኒቱ ቆሮንቶስ

ስለ ሦስቱ የሕይወት ደረጃዎች ምዕራፍ አምስት ላይ ተመልክተናል። እነርሱም ተፈጥሮአዊ ሰው፥ መንፈሳዊ ሰውና ስጋዊ ሰው ናቸው። ተፈጥሮአዊ ሰው እንደ ተፈጠረ ብቻ ያለ፤ ዳግመኛ ያልተወለደ እንደሆነ አውቀናል። መንፈሳዊ ሰው ግን ዳግመኛ የተወለደና በክርስቶስ ባገኘው አዲስ ሕይወት የእድገት ግሰጋሴ በማድረግ ላይ እንደሆነ አይተናል። ሥጋዊ ሰው ደግሞ ዳግመኛ የተወለደ ቢሆንም መንፈሳዊ እድገቱ የተገታና ቀጭጮ የቀረ ሕፃን እንደሆነ ተመልክተናል።

በሥጋዊ ሰውና በመንፈሳዊው ሰው መካከል ያለው ልዩነት የእድገት ልዩነት ነው። አንዱ በመንፈስ እያደገ ይሄዳል። ሌላው ደግሞ ሕፃን ነው። መንፈሳዊ ሰው የክርስቶስን ባሕርይ እየወረሰ ሲሄድ ሥጋዊ ሰው ደግሞ ምንም ዓይነት የመንፈስ እድገት አይታይበትም። የሚከተለውን ጥቅስ እንደገና እንመልከት ፦

> «እኔም፥ ወንድሞች ሆይ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልኩም። ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና አስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? አንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን? አንዱ እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ ሁለተኛውም እኔ የአጵሎስ ነኝ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን?» 1ኛ ቆሮ. 3፥1-4

በዚህ ጥቅስ በግልጽ እንደሚታየው ሥጋዊ ሰው ወይም ሥጋዊ ክርስቲያን፥ ሕፃን ስለሆነ መንፈሳዊነት ይጐድለዋል።

ሕፃንነት ለማንም የማይቀር ግዴታ ነው። ሁላችንም በአካል ወደዚህ ዓለም የምንመጣው ሕፃናት ሆነን ነው። ሕፃን ሳይሆን ያደገ ማንም የለም። ሁሉም በእናትና በሞግዚት እቅፍ ቆይቶ በአንቀልባ ታዝሎ፥ በአፈርና በሽንት ተጫውቶ ነው አሁን ካለበት አድገት ደረጃ የደረሰው። በመንፈሳዊውም ሕይወት ሕፃንነት የማይቀር ነው። ማንም ሰው ወደ ጌታ ሲመጣና ዳግመኛ ሲወለድ በመንፈስ ሕፃን ሆኖ ይጀምራል። አዲስ ክርስቲያን በአንድ ሳምንት ወይም በአንድ ወር የበሰለ አንዲሆን አይጠበቅም።

አድገት ጊዜ ይወስዳል። ሰዎች ሲድኑና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲቀላቀሉ በዓለም የነበረውን ባሕርያቸውን በሻንጣቸው ሙሉ እንደ ያዙ ይመጣሉ። የዱሮው አሰተሳሰባቸውን፥ ልምምዳቸውን፥ ንግግራቸውንና ጠቅላላ ሥጋዊ ነገሮቻቸውን መጣል የሚጀምሩት ቤተ ክርስቲያን ከመጡ በኋላ ነው። የእግዚአብሔር ቤት የማደጊያ ሥፍራ ስለሆነች አዳዲስ ነፍሳት ቃሉን ሲያውቁና ፈቃዱንም መረዳት ሲጀምሩ ሥጋዊ (ዓለማዊ) ባሕርያቸውን አንድ ባንድ ማስወገድ ይጀምራሉ።

አንዳንድ ሰዎች በሻንጣ የሞላውን ሥጋዊ ባሕርይ አውጥቶ ለመጣል ብዙ ጊዜ ስለማይፈጅባቸው፤ በቶሎ የሕፃንነትን ባሕርይ ይሽራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ከብዙ ዓመትም በኋላ ሻንጣው ውስጥ ያለውን ወርውሮ ያልጨረሰ አለ። የአንዳንዱም ጢም ብሎ እንደ ሞላ ሳይነካ ይቀመጣል።

በሕፃንነት ውስጥ አልፎ መሄድ ለማንም የማይቀር ግዴታ ነው። ሥጋዊ ሰው (ሥጋዊ ክርስቲያን) ግን፥ እድገት ጀምሮ ያቆመ ወይም ቀጭጮ የቀረ «ትልቁ ማሙዬ» ነው። በመንፈሳዊ ሕይወት፥ በማይቀረው ግዴታ፥ በሕፃንነት ውስጥ ማለፉ ሳይሆን አደገኛው ሁልጊዜ ሕፃን ሆኖ መቆየቱ ነው።

በአገሬ በኢትዮጵያ ሳለሁ አንድ አቶ ኪዳም የተባሉ ወንጌላዊ ይህን ነገር በሚመለከት ጉዳይ የሚከተለውን ምሳሌ ሲሰጡ ሰምቻለሁ። እኚህ ወንጌላዊ እንደሚሉት በደቡብ ሸዋ በባላገር ውስጥ በነበሩበት

ጊዜ አንድ ክተወለደ በኋላ እንቅስቃሴ የማያሳይ ልጅ በጐረቤት ነበረ። ይህ ልጅ እንደ ሌሎቹ ሕፃናት አይንሏቀቅም፥ አይድህም፥ ለመሄድ አይሞክርም። ቡና ለመጠጣት እናትየው ይዛው ወደ ጐረቤት ስትሄድ አንዴ ካስቀመጠችው ቦታ ሳይንቀሳቀስ ቡናው ተጠጥቶ አልቆ ሰው ይበታተናል። ልጁ ከተቀመጠበት አይንቀሳቀስም። ነገር ግን በተቀመጠበት ሆኖ ሰው ለየ፤ ነገር ለየ። እንደ ሌሎቹ ልጆች መቆምና መራመድ አልመቻሉ እናትየዋ ያሳዘናት መሆኑን የተገነዘቡ አንዲት ጐረቤት መቀመጫው ላይ በአሳት አንድትጠብሰው ይመክርዋታል። እናትየዋም እንደተመከረችው አደረገች። የልጁ መቀመጫ ቆሰለ ከተቀመጠበት በእንፋቅቅ ለመሄድ ቢፈልግ የበለጠ ቁሰሉ እየተላጠ አመመው። ሰለዚህ ቁሰሉን መሬቱ እንዳይነካበት ትንሽ ትንሽ ብድግ ማለትና መንሏቀቅ ጀመረ። በመጨረሻ ግድ ስለሆንበትም ለቁስሉ ሲል ብድግ ብድግ ሲል እንደ ሌሎቹ እኩያዎቹ ራሱን ችሎ በእግሩ መሄድ ቻለ። አቶ ኪዳም ይህንን ምሳሌ ከተናገሩ በኋላ እንደዚህ ልጅ በመንፈስ ላያድጉ የቀጨጩ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን እንዳሉና አንዳንድ ጊዜ እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ችግርና ፈተና ሕይወታቸውን እንዲያሰተካክሉ አንደሚረዳ አሰተማሩ።

በክርስቶስ ገና ሕፃን መሆን (አዲስ ክርስቲያን መሆን) እና በመንፈስ ሕፃን መሆን (በክርስትና ሕይወት ያለማደግ) ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። በመንፈስ ሕፃን ሆኖ መጀመር ግዴታ ነው። በመንፈስ ያለ ማደግ ወይም ሕፃን ሆኖ መቅረት ግን ምርጫ ነው። ለአንድ ክርስቲያን ምንም የአድገት ምልክት ላያሳይ ያመነበትን ዘመን በማስላት ዕድሜ መቁጠር ምንም አይጠቅምም። አንድ ልጅ ተወልዶ ባያድግ የወላጆቹን የዘመዶቹንና የወዳጆቹን ልብ ያሳዝናል። መንፈሳዊ ሕፃንነትም እንዲሁ ነው።

በመንፈስ ሕፃን ሆኖ መቅረት በብዙ መንገድ ቤተ ክርስቲያንን ይጐዳታል። ሰለሆነም እግዚአብሔርንም ያሳዝናል ብዬ እገምታለሁ።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን ሕይወት ስንመለከት አብዛኛዎቹ ገና ሕፃናት ነበሩ። በሕፃንነት ሕይወት ውስጥ አልፈው ማደግ ሲገባቸው እዚያው ቀጭጨው በመቅረት የብዙ ችግሮች ምክንያት መሆን ቻሉ። በእነሱና ባላመኑት ሰዎች መካከል ብዙ የባሕርይ

ልዩነት አልነበረም። እንዲያውም በቆሮንቶስ ከተማ ውስጥ ይታይ የነበረው ችግር በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ይታያል። በወንጌል ተለይተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሕብረት የገቡት በሻንጣ ሙሉ ክዓለም ይዘው የመጡትን ባሕርይ ገና ወርውረው አልጨረሱም።

ቆሮንቶስ የሕዝብ ሞራል ብልሹ የሆነባትና ኃጢአት የሞላት የወደብ ከተማ ነበረች። ለንግድ ወደ ከተማይቱ ይመጡ የነበሩት መርከበኞች የከተማይቱን ሰም ራሱ ሞራል ለጉደለው ባሕርይ መግለጫ አድርገው «ወደ ቆሮንቶስ እንሂድና እንቆረንጥስ» ይባባሉ ነበር። ይህ «እንቆረንጥስ» የሚለው ቃል በከተማይቱ ውስጥ ያለውን የረከሰ ተግባር ሁሉ የሚገልጽ ነበር።

የታወቀው የግሪኮች የፍቅርና የሌሸኘነት ጣዖት መቅደስ ያለው በቆሮንቶስ ከተማ ነበር። በዚህ መቅደስ ውስጥ የመቅደስ አገልግሎታቸው ዝሙት የነበረ አንድ ሺህ የሚያህሉ የሴት ቀላውስት ነበሩ። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ በዝሙት ተግባር የተሰለፉ ቀላውስት ክጣዖት መቅደሳቸው አላፈው በከተማይቱ ጐዳናዎች አየቆሙ የረከሰ ተግባር ይፈጽማሉ። ለእነዚህ አንድ ሺህ የሴት ቀላውስት ዝሙት ጣዖታቸውን የሚያወድሱበት ቅዳሴያቸው ነበር።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት ሁሉ በዝሙት አልተከለሱም። ሥጋዊነታቸው የተገለፀበት ሌሎች ልዩ ልዩ ባሕርያት እንደነበሩ በመልእክቱ ውስጥ ተዘርዝሯል። ዝሙትን በሚመለከት መንገድም ቢሆን የአባቱን ሚስት አግብቶ የነበረ የቤተ ክርስቲያን አባል ነበር። ይህንኑ በማሰመልከት ጳውሎስ የሚከተለውን ይጽፋል ፦

> «በአጭር ቃል በአናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብስ እንኳ የማይገኝ ነው፥ የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው ይኖራልና። አናንተም ታብያችኋል፤ ይልቅስ አንድታዝኑ አይገባችሁምን? ይህን ሥራ የሠራው ክመካከላችሁ ይወገድ» ይላል 1ቆሮ. 5፥1-2።

ኃጢአቱን በተግባር የፈጸመውን ሰው ብቻ ሳይሆን በዚህ አሳፋሪ ሥራ በማዘን የቤተ ክርስቲያንን ንጽህና መጠበቅ ሲገባቸው ዝም ያሉትንና ምንም አርምጃ ያልወሰዱትን መሪዎችና ምዕመናንን ጭምር

ይወቅሳል። ቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን ኃጢአት ብላ ካላስተማረች የምዕመኖቿ ሕይወት በኃጢአት ይተላሰራል። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሕፃንነት የተገለጸው የአባቱን ሚስት ያገባ በመኖሩ ወይም ቤተ ክርስቲያኒቱ ንጽህናዋን ለመጠበቅ አርምጃ ባለመውሰዷ ብቻ አይደለም።

የቆሮንቶስን ምዕመናን ሥጋዊነት (ሕፃንነት) ለመመልከት ጳውሎስ የጻፈላቸውን መልእክት ማንበብ ይጠይቃል። በቆሮንቶስ መልእክት ከምናየው ክፉ ባሕርያት ውስጥ እንዳንዶቹ የሚከተሉት ዓይነት ናቸው።

ሀ- በምዕመናን መካከል ቡድን (ፓርቲ) ማበጀት

ለ- በቡድን መሪዎቻቸው ዓላማና ሰንደቅ ስር ተሰልፈው፥ «እኛ የአገሌ ነን እናንተ የአገሌ ናችሁ» በማለት መከፋፈል

ሐ- የእርስ በርስ መቀናናት

መ- ራስ ወዳድነት

ሠ- የግል ጥቅምን ከመመልከት የተነሳ ወንድምን በአሕዛብ መካከል መክሰስ

ረ- የክርስቶስን ሳይሆን የራስን ዝናና ክብር መፈለግ

ሰ- የቤተ ክርስቲያንን ንጽህናና ሞራል አለመጠበቅ

ሸ- ፍትወት በጋብቻ ውስጥ ያለውን ቦታ አለማወቅ

ቀ- ክማያምኑ ጋር በማይመች አኳኋን መጠመድ

በ- የጌታን ራት ትርጉምና ምስጢር አለማወቅ

ተ- ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎችና አጠቃቀማቸው ተገቢ አውቀትና ልምምድ ማጣት

ቸ- መሠረታዊ ዶክትሪን አለማወቅ

ኀ- በተጨማሪም ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን በሚመለከቱ የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ ከአምነት ተቃራኒ የሆነ አመለካከት መያዝና ሌሎችም ሁኔታዎች ነበሩ።

«ወንድሞች!»

«ወንድሞች» የሚለውን ቃል ለይቼ ያወጣሁት ቀደም ሲል ክጠቀስነው ጥቅስ ነው። ክ1ኛ ቆሮ. 3፥1-4 ውስጥ ጳውሎስ ስለ ሥጋዊነታቸው (ሕፃንነታቸው) ሲናገር «ወንድሞች ሆይ» በማለት ይጠራቸዋል። «ወንድሞች» ወይም «እህቶች» የሚሉት ቃላት ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው የሚጠራሩበት የተለመዱ ቃላት ናቸው። ቀደም ሲል በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታዩ የነበሩትን ችግሮች ዘርዝረናል። እነዚህን ችግሮች በመመልከት ጳውሎስ የጻፈላቸው ሰዎች ክርስቲያን መሆናቸውን ልንጠራጠር እንችል ይሆናል። ጳውሎስ እንዴት ብሎ እንደጠራቸው ለማስታወስ የመረጥኩት ለዚህ ነው።

የእግዚአብሔር ቤት ሰፊ ነው፥ ልጆቹም ብዙዎች ናቸው፥ ባሕርይዎቻቸውም ለየቅሉ ነው። ወላጆች ልዩ ልዩ ባሕርይ ያሏቸውን ልጆቻቸውን አመል በማረቅና በመምክር ሁሉንም እኩል ያሳድጋሉ። እግዚአብሔርም ልጆቹን የሚያሳድገው እንዲሁ ነው። እንደ እርሱ ሁሉን እንደ አመሉ እየተሸከመ በመምክር የሚያሳድግ አባት የለም።

ለልጅ በልጅነት እድሜው ሁሉ ነገር ብርቁ ነው። በጓደኛው እጅ ያየውን መጫወቻ የራሱ ለማድረግ ይመኛል፤ ይቀማልም። የተቀማ ደግሞ ይደባደባል ወይም ያለቅሳል። ወላጆች የልጆቻቸውን መወቃቀስና መጣላት ሲያዩ፥ ሁሉንም እኩል ሊዳኙ ይገባል።

ልጆች በበዙበት ባሕርዩም ብዙ ነው፤ ጭቅጭቁና ንትርኩም የዚያኑ ያህል መሆኑ ግልጽ ነው። በማይረባ መጫወቻ ምክንያት መኮራረፍና መጣላት በልጆች መካከል የተለመደ ነው። ልጆች ሁሉ እየተጨቃጨቁ ያድጋሉ ብዬ መደምደም ያስቸግረኛል። ምክንያቱም እኔ ሁለት ልጆች በተቀራረበ እድሜ ውስጥ አሳድጌአለሁ። እነዚህ ልጆቻችን የተጣሉበት ወይም የተደባደቡበት ጊዜ ትዝ አይለኝም። የቤተ ሰብ ሕግና መመሪያ፥ የልጆቹ አስተዋይነት፥ በተለይም የእግዚአብሔር በረከት ይህን ሊያደርግ እንደቻለ አምናለሁ።

ልጆች በበዙበት ቤት የልጆች ጭቅጭቅና ጠብ አለ። ነገር ግን የልጆች ጠብ የልጆች ጠብ ብቻ ነው። ለጊዜው እንጂ ሥር የሰደደ መራርነትና መርዝነት የለውም። ብርቱው ደካማውን እየጐዳ አይኖርም። ብዙ ይቅርታ አለ። እጅግ የሚያስደንቀው ደግሞ ልጆች እያደጉና እየበሰሉ ሲሄዱ እንደዚህ ያለውን ባሕርይ መሻራቸውና ጭቅጭቅን በፍቅርና በትዕግሥት፥ ጠብን በመቻቻል፥ እየተኩት መሄዳቸው ነው። እድገት የልጅነትን ባሕርይ ይሽራል።

በመንፈሳዊው ሕይወትም በልጅነት ወራት ሊታዩ የሚችሉ ብዙ የልጅነት ባሕሪያት አሉ። ነገር ግን እነዚህ ባሕሪያት ከበሰሉና ካደጉ ሰዎች አይጠበቁም።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት ዋና ችግር አዲስ ክርስቲያንነት ሳይሆን የመንፈሳዊ እድገት ጉድለት የፈጠረው ሕፃንነት (ሥጋዊነት) ነው። እንደ ጳውሎስ በእረኛ ዓይን ሲያዩት የዚህ ዓይነት ሕፃንነት አሳዛኝ ነው። ያየባቸው አለማደግ ምን ያህል ስሜቱን እንደነካ ለማወቅ ካስፈለገ፥ «...የሥጋ እንደ መሆናችሁ በክርስቶስም ሕፃናት እንደሆናችሁ እንጂ መንፈሳዊ እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልችልም» ሲል የጻፈውን መመልከት ይበቃል። እነዚህ ሰዎች የጐደላቸው መንፈሳዊነት ነው። ሥጋውያን በመሆናቸው «ገና ሥጋውያን ናችሁና ...» ይላል። ደግሞም «... ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን?» ሲል ይጠይቃል። እንዲህ ያለው፥ መላእክት ናቸው ብሎ ጠበቆ ሰው ሆነው ስለተገኙ አይደለም። ሰው መሆናቸው የታወቀ ነው። ስለ ሦስቱ የሕይወት ደረጃዎች ስንመለከት ተፈጥሮአዊ ሰው እንደ ተፈጠረ ያለ፤ ዳግም ያልተወለደ ያልተለወጠ እንደሆነ ተነጋግረናል። ስለዚህ ባልተለወጠ ሰው ውስጥ እግዚአብሔርን የማያስደስቱ ብዙ ባሕሪያት አሉ። ሰው መንፈሳዊ ሲሆን እነዚህን ባሕሪያት እየተወና እየተለወጠ፤ ክርስቶስን እየመሰለ ይመጣል።

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ምዕመናን ያየው ነገር የማያስደስት ስለነበር፥ «በእናንተና ባልተለወጠው ሰው መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? እነዚህ ተግባሮች፥ እንዳልተለወጠ ሰው እያደርጓችሁምን?» ማለቱ ነው። ይህም ቢሆን በእነሱና ባልተለወጠ ሰው መካከል ያለውን ልዩነት ጠየቃቸው እንጂ ክርስቲያንነታቸውን አልካደም። ችግራቸው የመሰረት

ችግር ሳይሆን የእድገት ብቻ እንደሆነ ያውቃል። ሰለዚህ ነው «ወንድሞች ሆይ!» ሲል የጠራቸው።

የሕፃንነት ምልክቶች

መንፈሳዊ ሕፃንነት ለመታወቅ ይችላልን? ብለን እንጠይቅ ይሆናል። ጥያቄው ሊመለስ የሚችለው በአዎንታ ነው። አዎ! ሕፃንነት ለራሰም ሆነ ለሌላ ሰው መታወቅ ይችላል።

አንዳንድ ልጆች ቶሎ ያድጋሉ። በአሰተሳሰባቸውም ቶሎ ይበለላሉ። አባቶቻችን እንዲህ ያሉትን «የልጅ አዋቂ» ይሏቸዋል። በዚያው አንጻር አንዳንዶቹን ደግሞ «የአዋቂ አጥፊ» «ሁሉጊዜ ማሙዬ (ማሚቱ)» የሚል ቅጽል እንዲሰጧቸው የሚገደዱባቸው አሉ። ይህ ሁሉ መንፈሳዊ ብስለትም ሆነ ሕፃንነት ለመታወቅ የሚችል እንደሆነ ለመገምገም ይረዳናል።

ከዚህ በታች ባሉት ክፍሎች የሕፃንነት ባሕርይ ሊገለጽ ከሚችልባቸው ምልክቶች መካከል ጥቂቶቹን ለመዘርዘር እሞክራለሁ።

1. <u>ሕፃን በንግግሩ ይታወቃል</u>፤ ጮርቃ ሕፃናት የሚናገሩትን ሁሉ መስማት ለወላጅ እንደማይሰለች አውቃለሁ። ሕፃናት ከምላሳቸው ኮልታፋነት እሰከ ሃሳባቸው አሰቂነት ድረሰ ያላቸው ልዩ ጣዕም ንግግራቸውን ያጣፍጥላቸዋል። ሆኖም ሕፃናት ሀ) ብዙ ይለፈልፋሉ፥ አይደክሙም። ለ) ብዙ ይናገራሉ፥ ከንግግራቸው የሚገኘው ፍሬ አምብዛም ነው። በንግግራቸው መጨረሻ ጥልቀት ያለው ነገር ምን ሰማሁ? ብላችሁ ብትጠይቁ ምንም አታገኙም። ይህ ሊሆን የሚችለው ሕፃናቱ እንደማንኛውም ሰው ከአፋቸው የሚወጣው ቃል በልባቸው ሞልቶ ከተረፈው ሰለሆነ ነው። መጽሐፍ ቅዱሰ «ሰው ከልቡ ሞልቶ የተረፈውን አፉ ይናገራል» ይላል (ሉቃ.6፥45)። ስለዚህ ሕፃናት ክትንሿ የልብ ኮረጆ ውሰጥ ያለችውን ያችኑ ትንሿን አውቀታቸውንና ልምምዳቸውን ይናገራሉ። ገና ብዙ ማወቅና ብዙ ልምምድ ማግኘት አለባቸው።

የሚያውቁትን መናገራቸው ተገቢ ነው፤ አይወቀሱበትም። ነገር ግን ለመግለጽ የፈለግሁት ልጅ የሚያውቀውን ያችኑ ብዙ ጊዜ ደጋግሞ መለፍለፍ መውደዱን ነው። በአሁኑ ጊዜ የሦስት ዓመት ልጅ አለችን። በቅርቡ የምትሄድበት መዋዕለ ሕፃናት ሰለ ወራቶች አቆጣጠር፥ ሰለ ዓመቱ ወቅቶችና ሌሎችም ነገሮች አስተምረዋታል። የተማረችውን ብዙ ጊዜ ነግራናለች፤ ይሁን እንጂ የረካችበት አትመሰልም። ከሥራ በገባን ቁጥር በየቀኑ ትነግረናለች። አሁን ያንን ነገር መሰማት ለእኛ የተለመደ ሙዚቃ ሆኖአል።

መንፈሳዊው መንገድም ከዚህ የተለየ አይደለም። ብዙ ጥልቀት ባይኖረውም ያወቋትን ትንሽ አውቀት እሰኪሰለች ድረስ ደጋግሞ መናገር የመንፈሳዊ ሕፃናት ባሕርይ ነው። እዚህ ላይ ለማሰጠንቀቅ የምፈልገው «አድጌአለሁ፥ አውቄአለሁ»በሚል አስተሳሰብ የታዳጊ ክርሰቲያኖችን ሃሳብ ማናናቅ ወይም መተቸት ተገቢ አለመሆኑን ነው። ሐዋርያው ጳውሎሰ «አውቀት ያሰታብያል ፍቅር ግን ያንጻል» በማለት በ1ኛ ቆሮንቶሰ ምዕራፍ ሰምንት ያሰተማረውን ማሰብ ራሱ የእድገት ምልክት ነው።

2. <u>ሕፃን የሚደሰተው የሕፃን በሆነ ጉዳይ ነው</u>፤ ብዙ ውድዋጋ ያላቸውን ጠቃሚ ነገሮች ከአሻንጉሊት ጋር ቀላቅለን ለሕፃን እንዲመርጥ ብናመጣለት የሚመርጠው አሻንጉሊቱን ነው። ለሕፃን ትልቁ ብርቅ ነገር መጫወቻዎቹ ናቸው። ነገር ግን ይህንኑ አድል ለአዋቂ ሰው ብንሰጥ በጣም ውድና ጠቃሚ የሆኑትን ነገሮች እንደሚመርጥ ግልጽ ነው።

በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ ሰው፤ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ አሰፈላጊና ጠቃሚ የሆኑትን ነገሮች ከምንም ነገር ይልቅ ያስበልጣል፤ ይመርጣልም። በተለይም ከመንፈሳዊው ነገሮች ጋር ሲነፃፀሩ ምንም ዋጋ ለሌላቸው አለማዊ ነገሮች ልብን መሰጠት በመንፈሰ ገና ሕፃን የመሆን ምልክት ነው። በመንፈሰ ያደገ ሰው በዚህ ሕይወት አስፈላጊ ናቸው የሚባሉትን ነገሮች ቅደም ተከተል ያሰተካከለ ሰው ነው። ምድራዊው ነገር ከመንፈሳዊው ነገር የሚበልጥበት ሰው ማደግ አይችልም። ሙሴ በግብጽ የፈርዖን የልጅ ልጅ በመሆን የሚያገኘውንና

ከአስራኤል ሕዝብ ጋር መስደድን ከአወዳደረ በኋላ የሚሻለውን በአምነት መረጠ። (ዕብ.11፥25-27) ምድራዊው ነገር ከሰማያዊው ጋር ሲነፃፀር እንደ ጉድፍ ሲቆጠር ይገባል። «ዓለምን የሚወድ ከእግዚአብሔር ጋር ይጣላል፤ ፍቅሩም በውስጡ የለም» (1ኛ ዮሐ.2፥15-17)። አንድ ጊዜ እጅግ ሀብታም የነበረ ጫማ ነጋዴ እንዴት ሀብታም እንደሆነ ተጠይቆ ሲመልስ ፦ «በቅድሚያ እግዚአብሔር ቀጥሎ ቤተሰቤ ከዚያ በኋላ ጫማ» ሲል የሕይወቱን ቅደም ተከተል ዘረዘረ። መንፈላዊው ነገር የመጀመሪያ ምርጫችን ካልሆነ ያ በመንፈስ ያለማደግ ምልክት ነው።

3. <u>የራጋ ባሕርይ የለውም</u>፤ ሕፃን የውስጥ ሰሜቱ በተለዋወጠ ቁጥር የውጭ ባሕርይውም ይለዋወጣል። ሕፃን ከሰሜቱ በላይ መኖር አይችልም። ከጓደኞቹ ጋር ሲጫወትና ሲስቅ ብታዩት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ አኩርፎና ለንቦጩን ጥሎ ታገኙታላችሁ። በጥቂቱ ደስ ይለዋል፤ በጥቂቱ ደግሞ ይከፋዋል። መለመን መለማመጥ ይወዳል። ሕፃናት በአንድ ነገር ላይ ሰረጅም ጊዜ አይቆዩም፤ ጫወታም ቢሆን መቀያየርን ይወዳሉ። ዝም የሚባባሉበትም ጊዜ አለ።

በየጊዜው መለዋወጥ የሕፃንነት ባሕርይ ነው። ያደገ ሰው ግን ከሰሜቱ በላይ መኖር ይችላል።

ጌታ ኢየሱስ አንድ ጊዜ የሰዎች ባሕርይ አሰገርሞት እንዲህ አለ፥ «እንግዲህ የዚችን ትውልድ ሰዎች በምን አመሰላቸዋለሁ? ማንንስ ይመስላሉ? በገበያ የሚቀመጡትን ልጆች ይመስላሉ፥ እርስ በእርሳቸውም እየተጠራሩ፥ እንቢልታ ነፋንላችሁ እልዘፈናችሁምም፤ ሙሾ አወጣንላችሁ አላለቀሳችሁምም ይላሉ» ሉቃ. 7፥31-32።

ጌታ ይህንን ምሳሌ የሰጠበት ምክንያት ፈሪሳውያን የሚቀያየር ባሕርይ ስለነበራቸው ነው።

ስሜት ባሕርይን እንዳይለዋወጥ መጠንቀቅ የአደገ ሰው ምልክት ነው።

ስለ ስሜት ከዚህ በላይ ያለውን ሃሳብ በምገልጽበት ጊዜ በደፈናው

ስሜት መጥፎ ነው ለማለት አይደለም። በበኩሌ ስሜት የሌለው ድንጋይ ብቻ እንደሆነ አውቃለሁ። ሰው ሆኖ ስሜት የሌለው የለም። ስሜቴ የሚያስደስት ነገር ሲያገኝ እንድዘል፥ እንድጨፍር ይገፋፋኛል። በጌታ ላይ ያለኝ እምነቴም ስሜት ሲሰጠኝ ይገባል። እምነቴ ስሜት የማይሰጠኝ ቢሆን እምነቴን መመርመር አለብኝ። ጌታ ኢየሱስ ሰይጣን የዘረጋውን አሽክላ ሁሉ እያሸቀነጠረ ከፊቴ ሲጥለው ሳይ ዝም ማለት አይቻለኝም።

ሰው የግል ባሕርይው እንደፈቀደለት ደስታም ይሁን ሀዘኑን መግለጽ አይከለከልም። የሰው ሁሉ ባሕርይ ለየቅል ነው። እያንዳንዱ ሰው ደስታውን ሆነ ህዘኑን የሚገልጸው በራሱ መንገድ ነው። ሲደሰት ጮቤ የሚረግጥና የሚዘል፥ የሚያጨበጭብ፥ ሃሌሉያ የሚል፥ የሚስቅ አለ። ሀዘንንም የተለያዩ ሰዎች በተለያየ መንገድ ይቀበሉታል። ሰው ሁሉ በአንድ ዓይነት ተመሳሳይ መንገድ ስሜቱን መግለጽ እለበት ብሎ መጠበቅ አይቻልም። ሰማስገደድ ደግሞ አይፈቀድልንም። ስለዚህ ሁላችንም ስሜት አንዳለን ስሜታችንንም ደግሞ በራሳችን መንገድ መግለጽ እንደምንችል ብቻ ማወቅ አለብን።

ስሜት መጥፎ የሚሆነው፥ ሕይወታችንን የሚመራው ዋና ነገር ሲሆን ነው። በስሜት መመራት በተለይ በመንፈላዊ ሕይወት ትልቅ ችግር ያለከትላል። ስለሆነም ከርስቲያን የሚከተሉትን ሦስት ነገሮች ቅደም ተከተል ማወቅ አለበት። እነዚህም ህ) አውነት ለ) እምነት ሐ) ስሜት ናቸው። ብዙ ሰዎች አነዚህን ነገሮች በሚከተሉት ሁለት የተሳሳተ መንገድ ያስቀምጧቸዋል ፦

1. ስሜት	1. ስሜት
2. እምነት	2. እውነት
3. እውነት	3. እምነት

በእንደኛው ወገን የምናየው አስቀድመው በስሜት የሚሄዱና ከተሰማቸው በኋላ የሚያምኑ፤ ከዚያም ላመኑት ነገር ከእግዚአብሔር ቃል እውነትን የሚፈልጉ ሰዎችን ነው። ሁለተኛው መደብ ላይ ያሉት ደግሞ ከሁሉ በፊት በስሜት የሚመሩ፤ በኋላ ለሚሰማቸው ነገር መመስረቻ ጥቅስ የሚፈልጉና የሚያምኑ ሰዎች ናቸው።

እውነተኛና ትክክለኛ መንፈሳዊ ሕይወት ከሁሉ በፊት የሚያስቀድመው እውነትን ነው። እምነት የሚመሰረተው በእውነት ላይ ነው። አንድን ያላወቅነውን ወይም ያልጨበጥነውን እውነት ማመን ያስቸግራል። እውነትን ስናውቅ እንቀበለዋለን። እምነት በእውነት ላይ ይመሰረታል። አንድን እውነት ስናምን ደግሞ በዚያ እውነት ማመናችን ስሜት ይሰጠናል። እውነት ላይኖር እምነት መቅደም የለበትም። ከአምነት በፊትም ስሜት መቅደም አይገባውም። ኳስ ሜዳ ጫወታ ለመመልከት ገብቶ ገና ጫወታው እንደተጀመረ ግብ ላይገባ ተነስቶ ጮቤ እየረገጠ «ጐል! ጐል! አሸነፍን!» ለማለት የሚችል ምን ዓይነት ሰው ነው? ሌሎችስ እንዴት ይመለከቱታል? የምናምነውም ነገር ሆነ የሚለማን ነገር እውነት ላይ ካልተመሰረተ ዋጋ የለውም።

በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር 1960 ዓ.ም ላይ በአዋላ ኮንፍራንስ የመጀመሪያ ስማቸውን ዴቪድ ብለን የምንጠራቸውና በሐረር አስተማሪ የነበሩ ሕንዳዊ ሲያስተምሩን የሚከተለውን ነገሩን። «በሕንድ አገር እኛን የጴንጤቆስጤ እምነት ተከታዮችን ስሜታዊ ይሉናል። አንዳንዶችም ከእምነቶቻቸው እየጠቀሱ በመጨረሻ ዘመን እንደ እንቁራሪት የሚጮኹ ሰዎች ይመጣሉ የተባሉት እነዚህ ናቸው» ይሉናል። አዎ! እኛ እንጮኻለን ደስም ይለናል። ነገር ግን ማወቅ የሚገባን እንቁራሪት እንኳ የምትጮኽበት ጊዜ እንዳለ ነው። እንቁራሪት ከውኃ ርቃ በመሬት ላይ እያለች አትጮኽም ሮጣ ዘላ እንደምንም ከኩሬዋ ውስጥ ስትገባና በውኃ ውስጥ መሆኗን ስታውቅ ጩኸቷን ትጀምራለች። እኛም ጌታ ኢየሱስ በመንፈሱ ሲያጥለቀልቀንና ተጨባጭ ነገሮችን በዓይናችን ፊት ሲያደርግ ስናይ ነው በደስታ የምንፈነጨው»አሉ። እኚህ ሰው የተናገሩት የእንቁራሪት ምሳሌ ከስሜት በፊት እውነትና እምነት ቅድሚያ እንዳላቸው ለማወቅ ረድቶኛል።

ስለዚህም የእነዚህ ሦስት ነገሮች ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ሊሆን ይገባል።

1. እውነት
2. እምነት
3. ስሜት

ስሜት ቀድሞ ከመራ ችግር ይፈጠራል፤ የልጅነት ባሕርይ ይገዛናል። ስሜት አንዳንድ ጊዜ ከእውነቱ ጋር የተቃረነ መልእክት ይሰጣል። ለምሳሌ እግዚአብሔር «አልጥልህም አልተውህም ሲል ቃል ገብቶአል። ነገር ግን ስሜታችን እግዚአብሔር ፈጽሞ እንደረሳንና እንደተወን ሊነግረን ይችላል። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ተቀብለን በማመን ስሜታችንን መለወጥ ይገባናል። እንዲህ በማሰብ ፈንታ ዝም ብለን በስሜታችን ብንመራ በእምነታችን እንናወጣለን። ሕፃናት የረጋ ባሕርይ የማይታይባቸውና የሚቅበጠበጡት በስሜት እንጂ በእውነት ላይ የሚመሰረት እምነት ስለሌላቸው ነው። ስሜት ሊኖረን ይገባል ነገር ግን በስሜት ብቻ የምንመራ ከሆነ አደገኛ ከመሆኑም በላይ መንፈሳዊ እድገታችን ከምን ላይ እንደሚገኝ ይገልጻል።

4. <u>ከኃላፊነት መሸሽ</u> ወይም ብቁ ያለመሆን፤ ከኃላፊነት መሸሽ ወይም ብቁ አለመሆን ያለማደግ ምልክት ሊሆን ይችላል። የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት፥

> «ከጊዜው የተነሣ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም። ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤ ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በሥራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው» ዕብ.5፥12-14።

ከዚህ ጥቅስ የሚከተለውን መመልከት እንችላለን።

ሀ) ቃሉ የተጻፈላቸው ሰዎች አዲስ ከርስቲያኖች ሳይሆኑ የቆዩ ከርስቲያኖች ነበሩ፥ «ከጊዜው የተነሳ አስተማሪ ልትሆኑ ይገባ ነበር» የሚለው ቃል ይህንን እውነት ያሳያል። ጌታን ያመኑበትና ከርስቲያን የሆኑበት ዘመን ሊቆጠር ብዙ ነው በከርስትና እንዳላለፉት እድሜ ቢሆን ኖሮ ዛሬ አስተማሪዎች መሆን ይገባቸው ነበር። አሁን ግን ሀ-ብሎ ሌላ ሰው እንደገና ሊያስተምራቸው አስፈለገ።

ለ) እነዚህ አማኞች በከርስትና እድሜ ቢቆዩም መንፈሳዊ እድገት የማይታይባቸው፤ በመንፈስ ገና ሕፃናት ነበሩ፤ ሕፃንነታቸው ወተት

በመጠጣታቸው ይታወቃል። መልእክቱን የጻፈላቸው ሐዋርያ፥ «... ወተት ጋትጎችሁ» ይላቸዋል። የሚጋት ለራሱ ጥቅም የሚሆነውን የማያውቅ ምግብ የመቀበል ፍላጐት ያጣ ሕፃን ነው። ብዙ ጊዜ በአገራችን ያሉ አናቶች አንዲህ ያለውን ሕፃን አፍንጫውን ያዝ ለቀቅ እያደረጉ ሳይወድ የግድ አንዲጋት ያደርጉታል።

ሐ) እነዚህ ክርስቲያኖች እንደገና አንዲማሩ ያስፈለገው ሰው ወደ ጌታ ገና ሲመጣ ሊማረው የሚገባውን የመጀመሪያ ትምህርት (የደህንነት ሀ-ሁ) ነበር። መልእክቱን የጻፈላቸው ሐዋርያው፥ «የመጀመሪያ ትምህርት ... የሕፃንነት ትምህርት» እያለ የሚገልጸው ለዚህ ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል የማስተማር አገልግሎት ያለው ሰው በዚህ የተጻፈው ሁሉ ሐቅ እንደሆነ ያውቃል። አንዳንድ ጊዜ አስተማሪዎች ለቆዩት የሚያስፈልግ መሆኑን አውቀው የጠነከረ ምግብ ሲያቀርቡ መቀበል የማይችሉ ሕፃናት ያጋጥሙአቸዋል። አቡጊዳን፥ መልእክተ ዮሐንስን ልታሳዩአቸው ስትፈልጉ ያው ሀ-ሁ ካልሆነ በቀር ጠልቀ የማይገባቸው አሉ። የዚህ ችግር ምክንያቱ በመንፈስ ያለማደግ ነው። የዕብራውያን ፀሐፊ ያየነውን ጥቅስ ከመናገሩ በፊት አንድ ቁጥር ቀደም ብሎ እንዲህ ይላል፥ «ስለ አርሱም (ክርስቶስ) የምንናገረው ብዙ ነገር አለን፥ ጆሮአችሁም ስለፈዘዙ በቃል ልንተረጉመው ጭንቅ ነው» ዕብ.5፥11። ለማስተማር የሚወደው ብዙ አያለ በመንፈስ ባለማደጋቸው፤ ለመቀበልም ባለመቻላቸው ምክንያት ሲተወው እናያለን።

ጳውሎስ የቆሮንቶስን ምዕመናን ያገኛቸው በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሆነው ነው። ሕፃናት ሁሌ ረዳት ይፈልጋሉ። በራሳቸው ትልቅ ነገርን ለማድረግ ብቃት ያንሳቸዋል። ብዙ ጊዜም ከኃላፊነት መሸሽ ይወዳሉ።

5. <u>የችሎታ ጉድለት</u>፤ ልምምድበሚጐድልበት ቦታ ችሎታ ያንሳል። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሲጽፍ «ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትጓችሁ ገና ሥጋውያን ናችሁና አለክ አሁን ድረስ አትችሉም» ይላል 1ኛ ቆሮ.3፥2-4።

ለሕፃናት ሁሉ ነገር ክአቅም በላይ ነው። የችሎታ ማነስ የልምምድ ማነስ ውጤት ነው። የልምምድ ማነስ ደግሞ ክአውቀት ማነስ የተነሳ የሚመጣ ነው።

የቆሮንቶስን ክርስቲያኖች ሕፃንነት ማወቅ የሚቻለው ክሌሎች አኩያዎቻቸው ጋር ስታነፃፅሩአቸውና ስታዩአቸው ነው። ለዚህ በጳውሎስ አገልግሎት ካመኑና ካደጉት የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ጋር ስናነፃፅራቸው የሚከተለውን እናውቃለን።

ጳውሎስ በተሰሎንቄ የተቀመጠውና የእግዚአብሔርን ቃል ያስተማረው ለሦስት ሳምንት ብቻ ነበር። (የሐዋ.ሥራ 17፥2) ለእነዚህ ክርስቲያኖች ከሌላ ቦታ ሆኖ መልእክት ሲጽፍላቸው እንዲህ ይላል።

«... ደግሞ እናንተ ቃሉን በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ተቀበላችሁ፥ እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ፤ ስለዚህም በመቄዶንያና በአካይያ ላሉት ምዕመናን ሁሉ ምሳሌ ሆናችሁላቸው። ከእናንተ ወጥቶ የጌታ ቃል በመቄዶንያና በአካይያ ብቻ አልተሰማምና፥ ነገር ግን ምንም እንድንናገር እስከማያስፈልግ ድረስ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚሆን እምነታችሁ በሁሉ ስፍራ ተወርቷል» ይላል 1ተሰ. 1፥6-8።

ለሦስት ሳምንት ብቻ ያስተማራቸው ሰዎች ቃሉን በደስታ ተቀብለዋል። የጳውሎስን የህይወት ምሳሌነት እየተከተሉ ክርስቶስን መስለዋል። (የእድገት ግቡ ክርስቶስን መምሰል እንደሆነ ባለፉት ምዕራፎች ተምረናል) ቃሉ ደግሞ በውስጣቸው ፍሬ አፍርቷል። መልካም ተግባራቸው ክከተማቸው አልፎ ለሌሎች ክተሞች ደርሷል። የእግዚአብሔርን ቃል ለአካባቢው ክተሞች ሁሉ አድርሰዋል። የአገልግሎታቸውና የሕይወታቸው ምስክርነት በየቦታው ሁሉ ይወራል። ነገር ግን የቆሮንቶስን ክርስቲያኖች ሕይወት ስንመለከት እንዲህ ያለ እድገት አይታይባቸውም። ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ቁጭ ብሎ ያስተማረው ለአሥራ ስምንት ወራት (ዓመት ከመንፈቅ) ያህል ነው። ይህን በተሰሎንቄ ካሳለፈው ጊዜ ጋር ስናወዳድረው የሰባ አምስት ሳምንታት ልዩነት እናገኝበታለን። የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በሦስት ሳምንት ትምህርት አድገው ፍሬ ሲያፈሩ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ግን

ለሰባ ስምንት ሳምንታት የተማሩት ምንም አልጠቀማቸውም። እነዚያ ከራሳቸው አልፈው ዓለም አቀፍ ለሆነው የወንጌል ሥራ አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ እነዚህ ግን የሚያመልኩበትን የራሳቸውን ጎበረት አንኳ ያፈራርሳሉ። በአገልጋይ ዓይን ይህንን ሁኔታ ማየት በጣም ያሳዝናል። ሁልጊዜ ወተት ይፈልጋሉ ወተት ቢሰጣቸውም እንኳን ያንን መቀበል አይችሉም። የግድ መጋት ይፈልጋሉ። በምዕራቡ አገር ከአንድ እስከ ሦስት ዓመት ላላቸው ልጆች የተሰራውን ብቻ ካልሆነ ሌላ ነገር መመገብ የማይችሉ አረጋውያን አሉ። ግሮሰሪ ሲገቡም ቶሎ ወደ ሕፃናቱ ምግብ ተራ ነው የሚሄዱት። የእነዚህ አረጋውያን ጨጓራ ጠንካራ ምግብ መፍጨት አይችልም። አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ በሽታ የጠነከረ መንፈሳዊ ምግብ ለመውሰድ የማንችል ሊያደርገን ይችላል። እንዲህ ያለ አመለቻል ወይም የአቅም ማነስ ለመንፈሳዊ ብርታትና ጥንካሬም መለኪያ መሆን ይችላል።

6. <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ አለማወቅ</u>፤ በዕብራውያን መልእክት ውስጥ እንደተጻፈው :- «ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና። ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በሥራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው» ዕብ.5፥13-14። በጠንካራ ምግብ የመሰለው ከሕፃንነት ትምህርት በኋላ ከእግዚአብሔር ቃል የምንማረውን ትምህርት ሁሉ ነው። ጠንካራ ምግብ መልካሙንና ክፉውን ለመለየት ልምምድ እንደሚሰጥ ይናገራል። መልካሙንና ክፉውን ለይቶ ማወቅ እግዚአብሔር የሚደሰትበትን ፈቃዱን ለይቶ ማወቅ ነው። ስለሆነም ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሲሞላ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማወቅ ችሎታ ያገኛል። ቃሉን ያወቀ ሰው ሆነ ብሎ ካልሆነ በቀር በአውቀቱ ጉድለት ምክንያት የእግዚአብሔርን ፈቃድ አይስትም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ወይም አለማወቅ በክርስትና ሕይወት ብዙ ልዩነት ያመጣል። አንዳንድ ክርስቲያኖች ግልጽ የሆነውን ፈቃዱን እንኳን መለየት ያዳግታቸዋል። ለመመስከር ጌታ ኃይል አንዲሰጠን ወይም ምስክርነታችን ፍሬ አንዲኖረው ፀልዩልን ማለት ሲገባቸው ለመመስከር የእግዚአብሔር ፈቃድ አንዲሆን ይፀለይልን የሚሉ አሉ። ደግሞም ለመፀለይ ጌታ ጊዜ አንዲያመቻችላቸው መፀለይ

ሲገባቸው በፀሎት ቤታቸው ፀሎት ለመጀመር ፈቃዱ አንዲሆን እንፀልይ የሚሉም አጋጥሞኛል። ቀላሉን ምላሌ ለመጥቀስ ያህል አንጂ ግልጽ የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሰዎች አንዴት አንደሚሰወር ብዙ ማስረጃዎች መስጠት ይቻል ነበር።

አዲስ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል እስኪያውቅ ድረስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ባያውቅ ምክንያቱ ለሁሉ ሰው ግልጽ ነው። ነገር ግን ለብዙ ጊዜ የቆዩ ክርስቲያኖች ግልጽ የሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ አንኳን ሲማታባቸው ማየት አስገራሚ ነው። አንዲህ ያሉ ሰዎች የእድገት ችግር አንዳለባቸው ግልጽ ነው።

7. <u>በትምህርተ ነፋስ መፍገምገም</u>፤ ሕፃን ገና ሕፃን በመሆኑ አውቀትና ልምምድ ያንሰዋል። የእውቀትና የልምምድ ጉድለት በአንድ ነገር ላይ ጽኑ የሆነ የራስ አቋም ያሳጣል። የሚቆምለት አቋም የሌለው ደግሞ ወደ ገፉት ሁሉ ይገፋል። በእግዚአብሔር ቃል ላይ መሠረት ያጣ ሰው በቀላሉ ወደ ማንኛውም አቅጣጫ ይላባል። ወዲያ ወዲህ ሲሰቡት በቀላሉ የሚሳብ ሰው የጠነከረ አምነት የሌለው ነው። ይህም ሕፃንነቱን ያሳያል። ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶንን ክርስቲያኖች እንደሚከተለው ይመክራል :-

«እንደ ሰሕተት ሽንገላ ባለ ተንኰል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም» ኤፌ.4፥14።

በባሕር ላይ እንደተጣለች ኩበት በትምህርት ነፋስ ወዲያና ወዲህ መፍገምገም በመንፈስ ሕፃን የመሆን ምልክት ነው። በእድገት ላይ ያለ ክርስቲያን ግን እንደ ጳውሎስ «ያመንኩትን አውቃለሁ» ለማለት ድፍረት አለው።

8. <u>ራስ ወዳድነት</u>፤ ሕፃናት ራስ ወዳድ ናቸው። ራስ ወዳድነታቸው፥ ሁሉን «የእኔ ለእኔ» በማለታቸውና ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ይገለጻል። ሥጋዊነት ወይም በመንፈስ አለመብሰልም እንዲህ በመሰለው ባሕርይ ሊግለጽ ይችላል።

9. <u>ራስን ያለመቻል</u>፤ ሕፃናት ራሳቸውን ችለው መኖር አይችሉም።

ሁልጊዜ የሚንከባከቡ ሞግዚቶች ያስፈልጓቸዋል። በመንፈስ ያላደገ ሰንል ወደ ጌታ ገና የመጣውን አዲስ ክርስቲያን ሳይሆን ሳያድግ ቀጭጮ የቀረውን ማለታችን እንደሆነ ተነጋግረናል። እንዲህ ያለ ሰው ሁልጊዜ ሕፃን ስለሆነ ራሱን የሚችልበት ጊዜ የለም። ሁልጊዜ የሚመራው ሰው ይፈልጋል።

10. <u>ልታይ ልታይ ማለት</u>፤ ሕፃናት እኔ ብቻ ልታይ ማለት ይወዳሉ። በሚወታም ላይ ሲሆኑ ይሄው ጠባያቸው ይገለጻል። በቤተሰብ መካከልም አዋቂዎች ሲጫወቱ አንኳን ፋታ አይሰጡም። እነሱ ብቻ የምንም ነገር ኮከብ መሆን ይወዳሉ። እንደዚሁም ሥጋዊ ክርስቲያኖች ገና ስላልበሰሉ፤ በሁሉ ቦታ ኮከብ ሆነው መታየት ይወዳሉ። ክንቱ ውዳሴ ያታልላቸዋል። ዝናና ክብር ለማግኘት ይደክማሉ።

11. <u>ቅናትና ክርክር (ጠብ)</u>፤ ጠብና ጭቅጭቅ ዋና የሕፃንነት ምልክት ነው። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን መካከል ብዙ ጭቅጭቅ ነበር። የአብዛኛው ጭቅጭቃቸውና የንትርካቸው ምክንያት የልጅነት ባሕርያቸው ነው። ሕፃን ሁሉን ነገር «የእኔ ለእኔ» ማለት እንደሚወድ ተነጋግረናል። እንዲህ ያሉ ባሕርያት በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ብዙ ችግሮችን ያስክትላል። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ከጊዜያዊ ጭቅጭቅም አልፈው ፍርድ ቤት ድረስ በመጓተት ከወንድሞቻቸው ጋር በአደባባይ ይካሰሱ ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ የችግራቸውን ዋና ምንጭ ሲያሳያቸው እንዲህ ብሎ ይጽፋል ፦

«ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደለምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን?» 1ቆሮ.3፥3።

ከዚህ ጥቅስ እንደምናየው የጠብ የክርክርና የጭቅጭቅ ምክንያት ሥጋዊነት ነው። በቤተ ክርስቲያን የሚያጋጥሙን ችግሮች ሁሉ ምንጭ ሥጋዊነት ነው። ሥጋዊነትንና ሕፃንነትን ጳውሎስ በአንድ ዓይነት አመለካከት እንደሚመለክታቸው ቀደም ሲል አይተናል።

ስለ ክርክር በሚናገርበት ጊዜ የሃሳብ መለያየት አይኑር ማለቱ

አይደለም። ክርስቲያን ሁሉ የግድ አንድ ዓይነት አስተሳሰብ ማሰብ አይችልም። አነስተኛ በነበሩት የክርስቶስ ሐዋርያት መካከል እንኳ የተለያየ አመለካከትና ግላዊ ስብዕና (ፐርሰናሊቲ) እንደነበራቸው እናውቃለን። ነገር ግን ጌታ ሁሉንም እንዳሉ ተቀበላቸው። በወንጌል ውስጥ የትም ቦታ ቢሆን ሁሉም አንድ እንዲመስሉ ግላዊ ስብዕናና ባሕርያቸውን ሲጨፈልቅና አንዱ ሌላውን አንዲመስል ሲያደርግ አናይም። ሰዎችን በአንድ ዓይነት መቁረጫ እንደተቀረጸ ብስኩት (ኩኪ) ለማድረግ የሚደክሙ የግል ፍላጐት አእምሮአቸውን ያላወረባቸው ሰዎች ብቻ ናቸው። እግዚአብሔርስ በዓለም ላይ ሁለት ሰዎችን እንኳን አንድ አድርጐ አልፈጠረም። ማንም ሰው የራሱ ቅጂ የሆነ ሌላ ኮፒ የለውም። በዓለም ላይ የማንኛቸውም ሁለት ሰዎች እሻራ እንኳን አንድ አይነት አይደለም። እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ልዩ እድርጐ ነው የፈጠረን። በሁለት የበረዶ ብናኝ መካከል እንኳ ልዩነት እንዳለ አዋቂዎች ይነግሩናል። እግዚአብሔር የምድር አበባዎችን ሁሉ የፈጠረው በቀለም፥ በመልክ፥ የተለያዩ አንዲሆኑ አድርጐ ነው። ዝሆንንና ጥንቸልን፥ ጉማሬንና ዓሣን የፈጠረ አምላክ የተፈጥሮ ልዩነቶች የሚያስደስቱት መሆን አለበት። ሁሉን ነገር አንድ አድርጐ ቢፈጥር ኖሮ የምናየው ፍጥረት ሁሉ ለዐይን የሚሰለች በሆነ ነበር።

ልዩ ልዩ መሆናችን ብርታት እንጂ ድካም አያመጣም። የሁላችን አስተሳሰብና አመለካከት እንድ ዓይነት ቢሆን የትም አንደርስም። ጥፋትም ሲመጣ የሚያስተውል አይገኝም። አንዱ ሲሳሳት «ተው፥ ተሳስተሃል» ብሎ የሚመልስም ባልኖረ ነበር። እርስ በእርስ ለመመካከርና ለመተራረም ብሎም አንዳችን ከሌላው ለመማር የቻልነው ልዩ ልዩ ሆነን በመፈጠራችን ነው።

ሌላው ክርስቲያን እኔ እንደምናገር ካልተናገረ፤ እኔ እንደማስበው ካላሰበ በማለት የአመለካከት ልዩነቶችን ምክንያት በማድረግ የሚጨቃጨቅና ጠብ የሚፈጥር የአስተሳሰብ ብስለት የጐደለው ሕፃን ነው። ቅናትና ክርክር ሁሉ ምንጫቸው የእድገት ጉድለት ነው። ቅናት መራርነትን ይወልዳል መራርነትም ጥላቻን፥ ጥላቻም በቀልን ያመጣል የመጀመሪያው ነፍሰ ገዳይ ቃየን ወንድሙን ለመግደል የበቃው በቅናት ምክንያት እንደነበር ሊረሳ አይገባውም።

ዲያቢሎስ የእግዚአብሔር ልጆች እርሱን በመዋጋት ፈንታ እርስ በእርሳቸው ሲዋጉ ማየት ደስ ይለዋል። የክርስቲያኖች የእርስ በእርስ ጠብ ዲያቢሎስንና ሠራዊቱን ለመቋቋም የሚያስፈልገውን ኃይል በአጉል ቦታ ማባከን ነው። እሳት የተጠጋውን አንደሚያቃጥል ሁሉ በዚህ ዓይነት ጭቅጭቅና ጠብ የሚጐዳው ክርስቲያን እንጂ የጽድቅ ጠላት ዲያቢሎስ አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ «እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ» በማለት የሚመክረው ለዚህ ነው ገላ.5÷15።

ቅናትና ክርክር፥ ጠብና ጭቅጭቅ ክልጅነት የተነሳ የሚመጡ መሆኑን ካወቅን፤ መፍትሄው የልጅነትን ባሕርይ መሻር ብቻ ነው። የልጅነትን ባሕርይ ለመሻር ክልጅነት መውጣትና ማደግ ይጠይቃል።

12. <u>በቡድን መከፋፈል</u>፤ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የመንፈስ ሕፃንነት ከታየበት መንገድ አንዱ በመሪዎቻቸው ስም በቡድን በመካተት በምዕመናን መካከል መለያየትን ማምጣት ነው። ጳውሎስ የሚከተለውን ጥያቄ ይጠይቃቸዋል፤

«አንዱ እኔ፥ የጳውሎስ ነኝ ሁለተኛውም አኔ የአጵሎስ ነኝ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናቸው አይደለምን?» 1ቆሮ.3÷4

በቡድን የመከፋፈል ችግር ምንጩ መንፈሳዊውን እውነት (የእግዚአብሔር ቃል) በሚገባ ካለመረዳት የተነሳ ነው። ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልእክት መግቢያ ላይ እንኳ ችግሩን አንስቶታል።

«ወንድሞች ሆይ፥ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንተ የቀሎዔ ቤተ ሰቦች አስታውቀውኛልና። ይህንም እላለሁ እያንዳንዳችሁ እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፥ እኔ ግን የኬፋ ነኝ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ። ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለ እናንተ ተሰቀለን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?» ይላል 1ቆሮ. 1÷11-14።

እንደምናየው የቆሮንቶስ ምዕመናን በአራት ቡድኖች ተከፋፍለው ነበር። እነሱም ፦

ሀ) የጳውሎስ ቡድን

ለ) የአጵሎስ ቡድን

ሐ) የኬፋ (የጴጥሮስ) ቡድን

መ) የክርስቶስ ቡድን ናቸው።

የቡድን መንፈስ ብዙ ጊዜ ትልቁንና ዋናውን ነገር ከመመልከት ይከለክላል። ለእግዚአብሔር መንግሥት ከመሥራት ይልቅ ለአንድ ቡድን መሥራትና መድከምን ያስከትላል። የቡድን መንፈስ ፉክክርና ውድድርን ይፈጥራል። የፉክክርና የውድድር መንፈስ ደግሞ የማሸነፍ ፍላጐትን ያስከትላል። የአኛ ቡድን እንዲያሸንፍ ፍላጐታችን ጽኑ ሲሆን በሌሎች ሰዎች ስለሚሠራው የእግዚአብሔር ሥራ ግድ የለሽ ያደርገናል። በጣም በሥጋ የተዋጠ ክርስቲያን ደግሞ የእሱ ቡድን እንዲለማ ሌላው ቢደርቅ ደስ ይለዋል። ይህ ሁሉ ዲያቢሎስን በደስታ ስመፎለል የሚረዳው መልካም ዜና ነው።

ጳውሎስ፥ አጵሎስና ኬፋ በመንፈስ ያደጉና የበለጸጉ መሪዎች ናቸው። ስለዚህ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በቡድን መከፋፈል ምንም አስተዋጽኦ አላደረጉም። በሦስቱም መካከል ምንም ዓይነት መራርነትና ጠብ የለም። መንፈሳዊነት የተጐናፀፉ እነዚህ መንፈሳዊ አባቶች ይቅሩና የክርስቶስ ፍቅር የገባው ማንም እንኳን ጥላቻና ክርስትና አብረው እንደማይሄዱ ያውቃል። ጴጥሮስ በመልእክቱ ጳውሎስን «የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ» ብሎታል። ይህ ከልብ የፈለቀ እንጂ የሽንገላ ቃል አይደለም።

እርግጥ ነው እነዚህ ሦስቱም ግላዊ ባሕርይና ስብዕና (ፐርሰናሊቲ) አላቸው። የእያንዳንዳቸውም አገልግሎትና አጠራር ልዩ ልዩ ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ይህንን ለማስረዳት «እኔ ተክልኩ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር» ይላል። ቀጥሎም በማያያዝ «የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው ነገር ግን እያንዳንዱ፥ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል»ይላል 1ኛ ቆሮ.3÷5-8። ይህንን ቃል በአገልግሎት መስክ ላይ የሚገኙ ሁሉ ደጋግመው ማንበብ አለባቸው። ጥረያችንና አገልግሎታችን አሠራራችን እንደሚለያይ የምንቀበለውም ሽልማት የተለያየ እንደሆነ መማር የምንችልበት ሀሳብ ነው። ነገር ግን ሁላችንም ደግሞ የምንሠራው

ለአንድ መንግሥት ነው።

የወንጌልን ሥራ እንደ እንዲት አገር የመከላከያ ኃይል ልንመለክተው እንችላለን። በአንድ አገር የመከላከያ ኃይል ውስጥ፤ የባህር ኃይል፥ የአየር ኃይል፥ እግረኛ፥ መሐንዲስ፥ ታንከኛ፥ አየር ወለድ .... ወዘተ አሉ። የእነዚህ ሁሉ ሙያቸውና ችሎታቸው ልዩ ልዩ ነው። የክፍል መለዮ (ዩኒፎርማቸውም) ይለያያል። የሚሠሩትም ሥራ የተለያየ ነው። ነገር ግን እንደኛው ክሌላው እበልጣለሁ ብሎ መለየት አይችልም። አንደኛው ክፍል ለሌላው ረዳት እንጂ የባላንጣነት ግንኙነት የላቸውም። ይልቁንም እናት አገር ዋና ዓላማቸው ስለሆነች ሁሉም በየችሎታቸው በመተባበር እናት አገርን ከአጥቂ ለመከላከል በጎበረት ይዋደቁላታል። ከመካከላቸው ይህን ዓላማ የሚረሳ ሰው ቢኖርና የቡድን፥ የወገን ነገር ቢያመጣ ማንንም አይጠቅምም። እንዲህ ያለ ሰው ሁሉንም ቡድን፥ የራሱንም እንኳ ሳይቀር ይጐዳል። እናት አገሩንም ይበድላል። በወንጌል ሥራ ውስጥ ያለው ዓላማ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ነው። ዓላማ አንድ ያደርጋል። የዓላማ እንኳን መልካሙ ይቅርና ከፉው እንኳን ያስተባብራል። ለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሆነ ከታሪክ፥ በእድሜም ካየሁት ብዙ ማስረጃ መስጠት ይቻላል። ነገር ግን አስፈላጊ አይመስለኝም።

የእግዚአብሔር መንግሥት ሥራም የክርስቶስ ዓርማ ያላቸውን ክርስቲያኖች ሁሉ ያስተባብራቸዋል። የተለያየ ችሎታና ስጦታቸውም ለአንድ ዓላማ ይውላል። የቡድን ስሞቻቸውና የማኅበር መለዮአቸው፥ ከሁሉ በፊት ክርስቲያን፤ (የክርስቶስ) መሆናቸውን ሊያዘናጉ አይገባም። ስለዚህ እውነተኛና የበሰለ ትክክለኛ አመለካከት ያለው ክርስቲያን ዓይናቹ የማሕበር መለዮው ላይ ሳይሆኑ ክርስቶስ ላይ ነው። ዓይኑ ክርስቶስ ላይ የቆየ በወንድሞቹ ሁሉ ክርስቶስን ማየት ይችላል። ስለሆነም ለልዩነት ጊዜ የለውም።

ሐዋርያት በመንፈስ ብዙ ያላደጉበት ጊዜ እንደነበረና ክርስቶስም እንዲያድጉ እንደረዳቸው እናውቃለን። የአለማደግ ባሕርይ ታይቶባቸው የነበረው ክመስቀሉ በፊት፥ ኢየሱስን በሚከተሉበት ጊዜ ነበር። በወንጌል እንደምናነበው አንድ ቀን ወደ ኢየሱስ ቀርበው አንድ ሰው በስሙ አጋንንት ሲያወጣ እንዳዩና ነገር ግን ያ ሰው ከእነርሱ ቡድን

ውስጥ ስለሌለ አጋንንት ማውጣት እንዲያቆም እንዳዘዙት ነገሩት (ማር. 9፥38-42)። የማይቃወም፥ ተቃራኒ ያልሆነ ሥራ የሚሠራ የማኅበር አባል ባይሆንም በወንጌል ማኅበርተኛ መሆኑን እንዲያውቁ ጌታ ትምህርት የሰጣቸው በዚህ ጊዜ ነው።

ከመስቀሉ በኋላ በተለይም በመንፈስ ከተሞሉባት የጴንጤቆስጤ ቀን ወዲህ እንዲህ ያለ የልጅነት ባሕርይ በሐዋርያት አልታየባቸውም። ስለዚህ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ምዕመናን በቡድንና በፓርቲ መከፋፈል ከሐዋርያት ፍላጐት ጋር ግንኙነት የለውም። ለዚህ ነው ጳውሎስ በጥያቄ የሚይዛቸው። ከዚህ ቀጥሎ እነዚህን ቡድኖች አንድ በአንድ ለመመልከት እንሞክር።

ሀ) <u>በጳውሎስ ስም የተቋቋመው ቡድን</u>፤ ጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያ ነበር። ደኅንነት ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን በጸጋው ብቻ እንደሆነ ያስተማረ ሐዋርያ ነው። የዚህ ቡድን አባሎች ይህንን ሀሳብ ከራሳቸው ፍላጐት ጋር አዋህደው የነፃነትን ትርጉም እንደፈለጉት አስፋፍተው የተሰበሰቡ ቡድኖች ይመስላሉ። የቡድኑ አብዛኛው አባል ከአሕዛብ ወገን ሊሆን እንደሚችል ብዙ ሰዎች ይገምታሉ።

ለ) <u>በአጵሎስ ስም የተቋቋመው ቡድን</u>፤ አጵሎስ የአሌክሳንደርያ ሰው ነበር። አጵሎስ እጅግ የጠለቀና የመጠቀ እውቀት ነበረው ይባላል። ስለዚህ ምናልባት ምሁራን ነን ባዮች (ኢንተሌክቻልስ) ሳይሆኑ አይቀሩም ክርስርትናን በአእምሮ አውቀት ለመመልከትና ለመወያየት ይህን ቡድን የጀመሩት።

ሐ) <u>በኬፋ ስም የተቋቋመው ቡድን</u>፤ ኬፋ (ጴጥሮስ) ያደገበትን የአይሁድ ባሕልና ልማድ የሚያከር ነበር። ከጴንጤቆስጤ ቀን በኋላ እንኳን ይሄው ባሕልና ልማድ ክርስቲያን ሊያደርገው የሚገባውን ከማድረግ ሊከለክለው ተጽእኖ ፈጥሮበት ነበር። ጳውሎስ ይህንን አይቶ ነው ወንድማዊ ግሣፄና ምክር ያደረገለት። ፍቅር ወንድም ሊሳሳት እያየ ዝም አይልም። ለተሳሳተው ሰው በቀጥታ ምክርን ይሰጣል። ለጴጥሮስ የጳውሎስ ግሣፄና ጌታ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት እንዲሄድ አድርጐ ያስተማረው ትምህርት ከነበረበት የባሕል ተጽእኖ እንዲፈታ ረድቶታል። የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አሥራ

አምስትን ስናነብ ይህንን ማስተዋል እንችላለን።

በቆሮንቶስ በኬፋ ስም ቡድን ያቋቋሙት ክፍሎች አብዛኛዎቹ የአይሁድን ባሕልና ወግ፤ ሥነ ሥርዓታዊውንም የሙሴን ሕግ አየጠበቁ ክርስትናን ለመከተል የወሰኑ ሰዎች እንደነበሩ ይገመታል። እነዚህ ሰዎች የሚወዱትን ትተው ፍጹም መለወጥ ያስቸገራቸው አይሁዶች ናቸው። ይህም ከሆነ በጳውሎስ ስም ከተቋቋመው ቡድን አባላት ጋር ብዙ ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል።

መ) <u>በክርስቶስ ስም የተቋቋመው ቡድን</u>፤ ፈረንጆች «ውሸት በእውነት ጀርባ ላይ ትጋልባለች» የሚሉት አባባል አላቸው። በተለይ ይህ አራተኛው ቡድን ከሦስቱ ይልቅ ትክክለኛውን ቡድን የመሠረቱ ይመስላል። ክርስቲያን ክርስቶስን መላይ ማለት ነው። ስለሆነም ክርስቲያን የማንም ቡድን አባል ሳይሆን በመሠረቱ የክርስቶስ ነው። አነዚህ ሰዎች ሌሎቹን ሦስቱ ቡድኖች ካዩ በኋላ ብልጫቸውን ለማሳየት ቡድኑን እንደ መሠረቱት አልጠራጠርም። ነገር ግን «እኛስ የክርስቶስ ነን» ሲሉና ቡድን ሲያቋቁሙ ሁሳችንም ሊገባን የሚችለውን ትክክለኛ ነገር ማድረጋቸው አይደለም። እንደዚያ የሚሉበትም ዋና ዓላማ ንጹህ አይደለም። እነርሱ «የክርስቶስ ነን» ሲሉ ሌሎቹን ሁሉ፥ ማለት የቀረውን ክፍል ከክርስቶስ ውጭ ለማድረግ ነው። የክርስቶስን ስም የሚጠቀሙበት ሌሎችን ከእነርሱ ለመለየትና ለማግለል ነው።

ሌሎችን ለማግለል የምንጠቀምበት ነገር ሁሉ የኅብረት አንቅፋት ነው። የኅብረትና የአንድነት አንቅፋቶች መንስኤ ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ በዝርዝር ማቅረብ ያስቸግራል። ነገር ግን በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከነበረው መከፋፈል ካስተዋልነውና በልምምድም ካየነው አራት ዋና ዋና የኅብረት አንቅፋቶችን መጥቀስ እወዳለሁ። እነርሱም :-

1. <u>በራስ ብቁ ነኝ ማለት</u>፤ «የማንንም እርዳታ አልፈልግም፤ እኔ ለራሴ ብቁ ነኝ» ብሎ ማሰብ ለኅብረት አንቅፋት ሊፈጥር ይችላል። እግዚአብሔር የክርስቲያኖችን አንድነት የመሠረተው አርስ በርስ ለመረዳዳት በምንችልበት መንገድ ነው። አዲስ ኪዳን

በማያሻማ መንገድ የክርስቲያኖችን አንድ አካልነት ያስተምራል። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ውስጥ ሲጽፍ፥ «እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ አርስ በርሳችንም አያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን» ይላል ሮሜ 12፥5። በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉ፤ የአያንዳንዳቸውም ሥራ ከሌላው የተለየ አንደሆነ፤ የእኛም አገልግሎትና የተሰጠን ፀጋ ልዩ ልዩ ነው። ዓይን እኔ በራሴ ብቁ ነኝ ብላ ልታስብና ሌሎቹን አታስፈልጉኝም ልትል አትችልም። እጅ፥ እግር፥ ጆሮና፥ ሌሎችም ብልቶች ሁሉ ሌሎቹን ብልቶች አታስፈልጉንም ማለት አይችሉም። እግዚአብሔር እነዚህን ብልቶች ሁሉ የአንድ አካል ክፍል አድርጐ ፈጥሯቸዋል። የግድ አንዱ በሌላው ላይ ይመካል። ከብልቶቻችን መካከል አያስፈልገንም ብለን ቆርጠን ልንጥለው የምንችለው ነገር የለም።

አኛ ክርስቲያኖች በሙሉ የክርስቶስ አካል የሆንች የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባል ነን። የአንድ አካል አባል ስለሆንን ከሌላው የአካል ብልት ተለይተን በራሳችን በቂ መሆን አንችልም። የክርስቲያኖች ኅብረት ከሚናጋበት ዋና ምክንያቶች አንዱ በራሴ ብቁ ነኝ ማለት ስንጀምርና ሌላውን አያስፈልገኝም ብለን ቆርጠን ስንጥል ነው። አንዱ በሌላው ላይ ካልተመካና አርዳታ ካልፈለገ ኅብረት የሚባል ነገር የለም። ኅብረት፤ በአካል ምሳሌነት እንደተጠቀሰው በመረዳዳትና በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ ነው።

የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሕፃንነት የተገለጸበት መከፋፈል ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ላይ ያተኰረ ነበር። ስለሆነም 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥14-26 ላይ ስለዚህ ጉዳይ ሰፊ ምክርና ትምህርት ይሰጣቸዋል። በግል ሆነ ተሰባስበን የምናገላቸው የክርስቶስ አካል ክፍሎች ሲኖሩ፤ የቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ኅብረት እናፈርሳለን። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የሚጽፈውን መልእክት ገና ሲጀምር በመካከላቸው መለያየት እንዳይኖር «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አለምናችኋለሁ» ለማለት የተገደደው ለዚህ ነው (1ቆሮ.1፥10)።

2. <u>ፎርሙላ ማውጣት</u>፤ ፎርሙላ በሳይንስና በሌሎችም ነገሮች ውስጥ ጠቃሚ ነው። ጨረቃም ላይ ሲያደርስ ይችላል። በእግዚአብሔር

አሠራር ላይ «መንገዱ ይሄ ብቻ ነው።» ብሎ ፎርሙላ ማውጣት ግን በጣም አደገኛ ነው። ፎርሙላ የተወሰነ ጠባብ መንገድ ነው። የእግዚአብሔርን ሥራዎች ሁሉ በተወሰነ ፎርሙላ መምራት፤ ያንን ፎርሙላ የማይጠቀሙትን ከማግለሉም ሌላ እግዚአብሔርንም የተመጠነ ያደርገዋል። እግዚአብሔር የተወሠነና የተመጠነ አሠራር ሊኖረው አይችልም። አምላክ ስለሆነ የፈለገውን ማድረግ ይችላል። እኛ የምንጠቀምባቸው የአምልኮ ሥርዓቶች ወይም መንፈሳዊ አሠራሮች እግዚአብሔር ሊሰራባቸው ከሚችሉት መንገዶች አንዱ ብቻ እንጂ ሁሉንም ያጠቃለለ አይደለም። ስለዚህ የኔ ብቻ ትክክለኛ አሰራር ነው ማለት አንችልም። ስለዚህ የራሳችንን የአምልኮ ሥርዓቶችና መንፈሳዊ አሰራሮች ብንወዳቸውም የሌሎችን ሰዎች መንገዶች ልክ እንዳይደሉ መቁጠር አይገባንም። በክርስቲያኖች መካከል ላለው አንድነትና ጎብረት እንቅፋት የሚሆነው የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ሲኖር ነው።

3. <u>መራርነት</u>፤ ብዙ ጎብረቶች ከሚፈርሱበት ምክንያቶች አንዱ መራርነት ነው። መራርነት ባለበት ይቅርታ ቦታ የለውም። መራርነት የግል ሕይወትን ከመጉዳቱም ሌላ የሌሎችንም ሰላምና ጤናማ ግንኙነት ያቃውሳል። መራርነት የጎብረት ጠንቅ መሆን የሚችለው ለዚህ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላል። «የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጐድለው ብዙዎችም የሚረክሱበት አንድ መራራ ስር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ ... ተጠንቀቁ» ዕብ. 12፥15-16። ከዚህ ቃል መረዳት እንደምንችለው መራራ ስር በጊዜ ተቆፍሮ ካልወጣ ቀስ በቀስ ማደጉ የማይቀር ነው። የሚያድግም ነገር ያፈራል። ሥሩ መራራ ከሆነ ፍሬውም መራራ ነው። የሚቀምሱትን ሁሉ ይመራል።

" ብዙዎችን የሚያስጨንቅ " የተባለው መራርነት ከሰዎች ልብ ካልተነቀለና ካልወጣ እንደ ተሰቦ ወደ ሌሎችም ሊጋባና ሊሰፋፉ ብሎም አንድነትን ሊያጠፉ ይችላል። መራርነት ቂምና በቀልን ይወልዳል። ከዚህ አይነት የልብ ችግር ውስጥ የሚያደርሰው ለሰዎች እውነተኛን ይቅርታ አለመስጠት ነው። አንድ ጊዜ አንድ ያላመነ ሰው በአንዳንድ ክርስቲያኖች መካከል ያለውን ጊዚ የማይፈውሰው ጭቅጭቅ ካየ በኋላ፣ " ከቤተክርስቲያን ይልቅ ጠጅ

ቤት ብዙ ይቅርታ አለ " ሲል ተናገረ። ይህ በጣም የሚያሳዝን አስተያየት ነው፤ ምክንያቱም እውነተኛው የይቅርታ ቦታ ቤተክርስቲያን መሆን አለባት። ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን " ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? ሰባት ጊዜ ሰባት ነውን? " ሲል በጠየቀ ጊዜ ጌታ " አይደለም ሰባት ጊዜ ስባ እንጂ " ሲል መልሶለታል። እንዲህ ያለውን ወሰን የሌለው ይቅርታ ያስተማረው ለቤተክርስቲያን ነው። ይቅርታ በጎደለው ልብ መራርነት አለ፤ መራርነትም የጎብረትና የሰላም ጠንቅ ከመሆኑም በላይ የክፉት ሁሉ ሥር ነው። በመንፈሳዊ ሕይወት ማደጋችን ከሚታወቅበት መንገድ አንዱ በይቅርታ ሕይወት መሞላት እንደሆነ መዘንጋት የለብንም።

4. <u>የሊቃውንት ቡድን ማሰባሰብ</u> (ኤሊቲሲዝም) የሊቃውንት መኖር አስፈላጊ ነው ነገር ግን ሊቃውንት ሌሎችን የማግለል አላማ ያለው ቡድን ሲፈጥሩ እነርሱንና ሌላውን ምዕመን የሚለያይ አጥር ይሰራሉ። ይህ ለመከፋፈል ምክንያት ይሆናል። በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን " እኛ የአጵሎስ ነን " የሚሉት ወገኖች የዚህ አይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች እንደነበሩ ይገመታል። ሰዎች ራሳቸውን ከሌሎች በላይ አድርገው መመልከት ሲጀምሩ ሰይጣን ደስ ይለዋል ምክንያቱም የዚህ አይነት የትዕቢት ነገር ሀሳቡ ያላቸው ላይ የመንፈስ ውድቀት ማምጣት ብቻ ሳይሆን ማህበሩንም እንደሚከፋፍል ያውቃል። አንዱ ክርስቲያን በሌላው ክርስቲያን ላይ እንዲከፋ የሚያደርግ ምንም አይነት ነገር ለዲያብሎስ ያመቸዋል። ይህንን በመረዳት በትክክለኛ አላማ መሰባሰብ ያስፈልጋል ሌሎችም የምንሰባሰብበት አላማ እንዲገባቸው ማድረግ አለብን። በመሰረቱ የተማሩና የተመረመሩ ሊቃውንት ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ ናቸው በመልካም አላማ ለማስተማርና ለመገንባት መሰባሰቡም ጥፋት የለውም ነገር ግን ለአንድ ክርስቲያን ተገቢ እንደሆነውና መጽሐፍ ቅዱስም

የሚጠይቀውን ትህትና ማጣት ብሎም ከሊቁ ካልሆነ በቀር ከሌላው ጋር አለመደባለቅ ግን ዋና የአንድነትና የኅብረት እንቅፋት ነው።

የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሕፃንነት የተገለፀበት እንደኛው መንገድ ከዚህ በላይ በዘረዘርነው ሁኔታ በቡድን መለያየት ነው። የዚህ ዓይነት የቡድን ስሜት በሚያይልበት ማንኛውም ጊዜና ቦታ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በሚከተሉት መንገድ ትጐዳለች ፦

ሀ) <u>የቡድን መከፋፈልና ክርክር፤</u> ክርስቲያኖች ጠላታቸው ሰይጣን መሆኑን እንዲዘነጉና ከወንድሞቻቸው ጋር በጠላትነት ዓይን እንዲተያዩ ያደርጋል።

ለ) ክርስቲያኖች እርኩሳን መናፍስትን በመዋጋት ፈንታ እርስ በእርሳቸው በመዋጋት ኃይላቸውን እንዲጨርሱ ያደርጋል።

ሐ) የክርስቶስ ወንጌል ሥርጭት ሥራ ይጐዳል። ሰዎች በቃል ስንሰብክ ከሚሰሙት ይልቅ በዓይን የሚያዩትና በተግባር የሚመለከቱት የበለጠ ይነካቸዋል። ስለዚህ የምንናገረውን የማንኖር መሆናችንን ሲያስተውሉ ወንጌላችንን ተቀብለው መዳን ያቅታቸዋል። የዳኑ ካሉም እድገታቸው ይቀጭጫል።

መ) <u>ፍቅር በክርስቲያኖች መካከል ትቀዘቅዛለች፤</u> መነፋፈቅ ይጠፋል። መቀራረብ በመራራቅ ፍቅርም በጥላቻ ትተካለች። ጳውሎስ ስለ ፍቅር የጻፈው ታላቁ ምዕራፍ ለእነዚህ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክት ውስጥ መገኘቱ የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም።

ሠ) ዓለም ስለ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተሳሳተ መልእክት ትሰጣለች። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ነች። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን አንድነት ማየት ያቅታቸዋል።

ረ) የእግዚአብሔር ቃል በትክክል ከመስበክ ይልቅ እንዲበረዝና እንዲሸቃቀጥ ያደርጋል። እንዲህ የሚሆነው እያንዳንዱ ቡድን አባሎችን ለማብዛት ያለው ፍላጐት ዓላማውን እንዲስት ስለሚያደርግ ነው።

ሰ) የክርስቶስ ከመሆን ይልቅ የቡድን አባሎች እንድንሆን ያደርጋል።

የዚህ ውጤት ሁለት ክርስቲያኖች ምንም እንኳ በክርስቶስ አንድ ቢሆኑም የተለያየ ቡድን ውስጥ በመኖራቸው አብረው ኅብረት እንዳያደርጉ ያደርጋቸዋል።

ሸ) <u>እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን</u> (አካል) የሰጠውን ስጦታዎች በሙሉ ከመጠቀም ይከለክላል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ዘጠኝ የፀጋ ስጦታዎች አሉ። 1ኛ ቆሮ. 12፥4-11 ላይ ተዘርዝረዋል። በተጨማሪም በሮሜ 12፥3-9 እንደተፃፈው ተጨማሪ መንፈሳዊ ችሎታዎችን መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ እናውቃለን። እንደዚሁም የአገልግሎት ስጦታዎች የሚባሉት፤ ሐዋርያት፥ አስተማሪዎች፥ ነቢያት... የመሳሰሉት ስጦታዎች አሉ። (ኤፌ. 4፥11 ላይ ተመልከት)

እነዚህ ስጦታዎች ብዙ ጊዜ ሁሉም ለአንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን አይሰጡም። ምናልባት የፀጋ ስጦታዎች በሙሉ የሚሠሩባት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብትገኝ እንኳ የአገልግሎት ስጦታዎች ሁሉ ሊኖሯት አይችልም። የአገልግሎት ስጦታዎች ከፀጋ ስጦታዎች የተለዩ ናቸው። የፀጋ ስጦታዎች ለሰዎች የሚሰጡ መንፈሳዊ ችሎታዎች ናቸው። የአገልግሎት ስጦታዎች ግን «ሰዎች» ናቸው። «እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ሐዋርያትን፥ ነቢያትን፥ አስተማሪዎችን፥ ወንጌላውያንንና እረኞችን ሰጠ» ነው የሚለው። ስጦታዎቹ ሰዎች ናቸው። ስጦታዎቹ የተሰጡት ለአካሉ እንጂ ለአንዲት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ አይደለም። ሁሉም ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ይሰጣሉ ብለን ብናምን እንኳን ስጦታዎቹ ሰዎች ስለሆኑ አንድ ዓይነት አገልግሎት አይኖራቸውም። የሁለት የተለያዩ አስተማሪዎችን ትምህርት ብንመለከት ሁሉም የራሳቸው የሆነ አቀራረብና ቃና ስላላቸው የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን። ስለዚህ አንዱን ትተን ሌላውን መምረጥ አንችልም።

የቡድን መንፈስ ሲኖር የሚፈጠረው አጥር ምዕመናን እነዚህን አገልግሎቶች እንዳይጠቀሙበት ይከለክላል። በዚህ፤ ቤተ ክርስቲያንና ሰጪውንም መበደል ይቻላል።

ከ ሀ እስከ ሸ በተዘረዘሩት ክፍሎች የተገለጹት ችግሮች ዋና

ምንጭ ጠላት ነው። ዲያቢሎስ መከፋፈል ስለሚጠቅመው እነኝህን ነገሮች እንደሚፈጥር አልጠራጠርም። በሁለተኛ ደረጃ ግን እነዚህ ነገሮች የሚመነጩት በመንፈስ ካለማደግና ሥጋዊ ከመሆን የተነሳ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ችግር ምንጩ ብሎ የሚጠቁመው ሕፃንነታቸውን (ሥጋዊነታቸውን) መሆኑ አይካድም።

የአንድነት አርማ

ቡድኖችና ማኅበሮች የአንድነታችን መሠረትና ዓርማ አይደሉም። ቀደም ብለን በዘረዘርነው ትንተና ይህንን ለመረዳት ችለናል። አንድ የምንሆነው በአንድ ማኅበር ውስጥ በመሆን አይደለም። ድርጅታዊ መዋቅሮች የአንድነት መሠረቶች አይደሉም። ለመልካም ዓላማ የማኅበሮች መኖር አስፈላጊ ነው። ሀሳቤ የማኅበር መኖርን ፈጽሞ አይቃወምም። እንኪያስ ምን አንድ አንድንሆን ያደርገናል? የዚህን መልስ ለማግኘት የቆሮንቶስ ክተማ ክርስቲያኖችን ጳውሎስ የጠየቀውን ጥያቄ በድጋሜ እንመልከት፥

> «ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስ ስለ እናንተ ተሰቅሎአልን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን? ... ወንጌልን ልሰብክ እንጂ ለማጥመቅ አልተጠራሁም ...»።

የጠየቃቸው ጥያቄ ዋና ዋናዎቹን የአንድነት መሠረቶች ያጠቃልላል። በዚህ ጥቅስ ክርስቲያንን አንድ የሚያደርጉ አራት የአንድነት መሠረቶች ተጠቅሰዋል። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው :-

ሀ) <u>ክርስቶስ</u>፤ ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ከሁሉም በላይ ዋናውን የክርስትና አንድነት መሠረት መጥቀሱ ነው። ክርስትና ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ዋናው መሠረታችን ሲሆን፤ በቅርብ ይኑሩ በሩቅ፤ የሰውን ፆታ፥ ቀለምና ዘር ሳንለይ ከርስቶሳውያንን ሁሉ (ክርስቲያኖችን) ወንድሞቻችን እንደሆኑ እናውቃለን። ሁሉን አንድ ያደረገና ያዋሀደ እርሱ ብቻ ነው። ከክርስቶስ ሌላ የምንፈጥረው የአንድነት መሠረት ከእግዚአብሔር ቃል የወጣና

አደገኛ ነገር ነው። ስለዚህ ክክርስቶስ ሌላ የአንድነት መሠረት በማንም መመሥረት የለበትም። ክተመሠረተው ሌላ ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይገባም (1ኛ ቆሮ.3፥10-12)።

ለ) <u>መስቀል</u> :- ሐዋርያው ጳውሎስ በቡድን የተከፋፈሉትን የቆሮንቶስ ሰዎች፥ «ጳውሎስ ስለ እናንተ ተሰቅሎአልን?» ሲል ይጠይቃል። የክርስቶስ መስቀል የአንድነት መሠረት ነው። ሁላችንም ወደዚህ መስቀል በቀረብን ጊዜ እግዚአብሔርን አገኘን፤ እርስ በእርስም ተገናኘን። ያንን በክርስቶስ መስዋዕትነትና ደም የፈጠረውን አንድነት ምንም ነገር ሊሸረው አይችልም። ስለሆነም መስቀሉ የወንድማማችነትና እህትማማችነታችን አርማ ነው።

ሐ) <u>ጥምቀት</u> :- ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በማን ስም እንደተጠመቁ ይጠይቃል። «በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?» ይላል። የተጠመቅነው በምንክፋፈልባቸው መሪዎች ስም ቢሆን ኖሮ የክርስቶስ ክመሆናችን በፊት የእነዚህ ሰዎች ወይም ቡድን አንሆን ነበር። የምንጠመቀው በእግዚአብሔር ስም ነው። ጳውሎስ በአንድ ስፍራ «አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።» ይላል ኤፌ.4፥5-6። ስለዚህ ጥምቀት ራሳችንን ክክርስቶስ ጋር የምናመሳስልበት ሥርዓት ነው። ሁላችንም የትኛውም ቦታና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብንገኝም በእግዚአብሔር ስም አንጠመቃለን። ስለዚህ አንዲት ጥምቀት የአንድነታችን ዓርማ ነች።

መ) <u>ወንጌል</u>፤ ወንጌል ሁላችንን ማኅበርተኛ እንድንሆን ታደርጋለች። ክርስቲያኖች ሁሉ አዲስ ለመወለድ የሚችሉት በወንጌል ነው። የወንጌሉ የምሥራች ሁላችንም የተፈታንበት ነው። ወንጌል የአንድነታችንም ዓርማ ነው።

ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ያገኛት በጣም ሕፃን ሆና ነው። እነዚህን የአንድነት መሠረቶች ሁሉ ትተውታል። ሌሎች የአንድነት መሠረቶችንም አቁመዋል። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የጎደላት ስጦታ አልነበረም። ብዙ ስጦታዎች ነበሯት። የችገራቸው

አስተማሪም አይደለም። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አስተማሪ ጳውሎስ ራሱ፥ ለአሥራ ስምንት ወራት መካከላቸው ቁጭ ብሎ አስተምሮአቸዋል። የችግራቸው ምክንያት አለማደግ ነበር። አለማደግ አንዳንድ ጊዜ ከሞግዚቶች የተነሳ መሆን ቢችልም፤ አብዛኛው የመንፈሳዊ እድገት ችግር ከግለሰቡ ፍሳጐትና ውሳኔ የተነሳ የሚመጣ ነው። ስለሆነም እያንዳንዱ ግለሰብ (እያንዳንዱ ክርስቲያን) ስለ መንፈሳዊ እድገቱ ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ አለበት፤ ለእድገቱ እንቅፋት የሚሆኑትን እያስወገደ የሚጠቅሙትን ነገሮች መከታተል አለበት።

በሚቀጥለው ምዕራፍ ለእድገት ስለሚጠቅሙት ነገሮች እንመለከታለን። ነገር ግን እስከ አሁን በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሕፃንነት የራሳችንን ሕይወት ካየንበትና/ያለንበትን ቦታ ካወቅን ችግራችንን ለማስወገድ የሚቀረን ብዙ አይደለም። ችግሩን ያወቀ መድኃኒቱን ይፈልጋል። የልጅነት ባሕርይ መሻር ያለበት ነገር ነው። መሻር የምንችለውም እኛው ራሳችን ነን።

ለእድገት ጠቃሚ ነገሮች

ምዕራፍ 10

ለእድገት ጠቃሚ ነገሮች

ሕይወትን ትርጉም ያለው የሚያደርገው የእድገት መኖር ነው። ልጆች ተወልደው ባያድጉ እጅግ በጣም የሚያሳዝን ይሆናል፤ የወላጆችም ልብ በመራራ ሀዘን ይመታል። መወለድ ደስ የሚለው ማደግ ስላለ ነው።

አድገት ብዙ ነገሮች ላይ ይመካል። የሞግዚቶች እንከብካቤ፥ ጥሩ አመጋገብ፥ ጥሩ የመኖሪያ አካባቢ፥ ... አካላዊ እድገትን የሚረዱ ነገሮች ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ደጋግመን በማነፃፀር ለመመልከት እንደሞከርነው፤ በመንፈሳዊ እድገትና በአካላዊ አድገት መካከል ብዙ ተመሳሳይነት አለ። መንፈሳዊ እድገትም በብዙ ነገሮች ላይ ይመካል። ለመንፈሳዊ አድገት አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ከሌሉ መንፈሳዊ እድገት ሊኖር አይችልም። ለዚህም ጠቃሚ ከሆኑት መካከል ዋና ዋናቹን በዝርዝር እንመልከት :-

1ኛ <u>የእግዚአብሔር ቃል</u>

ሰው ተወልዶ ወደዚህ ዓለም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ለመኖርም ሆነ ለማደግ ምግብ መመገብ አለበት። ያለ ምግብ ለማደግ ቀርቶ ለመኖርም እንኳን አይቻልም።

አካላችን የሚገነባውና የሚያድገው በምግብ ነው። ባዮሎጂስቶች እንደሚሉት ምግብ ሀ) ለሰውነታችን ኃይል ይሰጣል፥ ለ) የሰውነታችንን ሙቀት ይጠብቃል፥ ሐ) ሰውነታችንን ይገነባል። ቀደም ካሉት ምዕራፎች በአንዱ ፈረንጆች «እንደ በላኸው እንዲሁ ነህ» የሚሉትን

አባባል የጠቀስነው ለዚህ ነው።

አንጀራ (ምግብ) ለአካላችን ግንባታ፥ አድገትና በሕይወትም ለመኖር አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግም ሆነ ለመኖር መንፈሳዊ ምግብ ያስፈልገናል። ያለ መንፈሳዊ ምግብ መንፈሳዊነት አይገኝም። በመንፈሳዊ ሕይወት (ክርስትና) ጸንተን መቆምና በእድገት ጐዳና መገስገስ የምንችለው የእግዚአብሔርን ቃል በየጊዜው መመገብ ስንችል ብቻ ነው። ጌታ ኢየሱስ በስይጣን በተፈተነ ጊዜ ከመለሰለት መልሶች መካከል አንደኛው ይህንን ሐቅ ጥርት አድርጐ ያሳየናል፤

«ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በአንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው» ማቴ. 4፥4።

ያለ ምግብ ሕይወት፤ ያለ እግዚአብሔርም ቃል መንፈሳዊነት የለም። በመለኰታዊ ባሕርይ እየገነባንና እያዳበረን ለእግዚአብሔር ያለንን የፍቅር ግለት ጠብቆ፥ በብርታትና በኃይል አንድንራመድ የሚያደርገን የእግዚአብሔር ቃል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ ነፍሳችንን በቃሉ እንመግባለን። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለሁሉ ሰው የሚሆን የተመጣጠነ መንፈሳዊ ምግብ አለ።

ሕፃን ገና ሊወለድ ምግብ ሊያገኝ የሚችለው ከእናቱ ጡት ወይም በጡጦ ተደርጐ ከሚሰጠው ወተት ነው። ለተወሰነ ጊዜ ከዚህ ሌላ ምግብ መውሰድ አይችልም። ከተወለደ ጥቂት ወራት በኋላ ለስላሳ ምግብ መውሰድ ይችላል። በአደገና በጠነከረ ቅጥር ደግሞ ማንኛውንም ጠንካራ ምግብ መመገብ ይችላል።

የእግዚአብሔር ቃል በማንኛውም መንፈሳዊ አድሜ ላይ ለሚገኙ አማኞች የሚሆን የተመጣጠነ ምግብ አለው። ስለሆነም የነፍስን ጥማት አርክቶ ለእግዚአብሔር ያለንን የፍቅር ግለት እየጠበቀ ክርስቶስን አየመሰልን አንድንሄድ ያሳድገናል።

ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልእክቱ ስለ ቃሉ ተመጣጣኝ ምግብነት እንዲህ ይላል፤

«ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ አንደሆነ ለመዳን በአርሱ አንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃሉን ወተት ተመኙ» (1ጴጥ. 2፥2)።

ሕፃን ጠንካራ ምግብ መመገብ ስለማይችል ወተት እንደሚያስፈልገው በመንፈስ ገና የተወለዱ አዳዲስ ክርስቲያኖችም ምስጢሩን ለመረዳት ክባድ ያልሆነውን የመጀመሪያ ትምህርቶችን ከእግዚአብሔር ቃል መማር ይችላሉ። «የቃሉ ወተት» የተባለው ያ ነው። አያደጉና እየጠነከሩ በሄዱ ጊዜ ግን ጠንከር ያለውን ሐሳብ መማርና መቀበል ይችላሉ። በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ጠንካራ ምግብ፥ ክፉና ደጉን ለመለየት የለመደ ልቦና ላላቸው ሰዎች እንደሆነ ተጽፎአል (ዕብ. 5፥12-14)። ስለዚህ በመንፈስ ገና ሕፃን ከሆንበት ጊዜ አንስቶ የብስለት ደረጃ ላይ እስክንደርስ ድረስ የሚረዳንን ምግብ ከቃሉ ማግኘት እንችላለን።

ሰው ምግብ ባይበላ ሰውነቱ ሊጐዳና ወደ ሞትም ሊያዘግም ይችላል። የምግብ አጦት የሚያደርሰውን የረሀብ አልቂት ሁላችንም በዓይናችን ተመልክተናል። የእግዚአብሔርን ቃል የማትመገብ ነፍስ መንፈሳዊ የረሀብ አለንጋ ይገርፋታል። ቃሉን የተነፈገች ነፍስ እየከሳች፥ እየገረጣችና እየተጐሳቆለች ትሄዳለች። ስለዚህ መንፈሳዊ ሕይወታችን እንዲያድግና እንዲዳብር ቃሉን ከመመገብ ሌላ አማራጭ ነገር የለም።

ሰው አንድ ጊዜ ብቻ በበላው አይኖርም። ያለፈው ቀን የተበላው ለዛሬ ስለማይሆን ኑሮ እንደፈቀደልን በየቀኑ የተወሰነ ጊዜ ያህል እንበላለን። ነፍሳችንን የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ የሚኖርብንም እንደዚሁ ነው። በአንዳንድ አማኞች ቤት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ሳይነበብ አዋራ ጠጥቶ ሲቀመጥ እንደማየት አሳዛኝ ነገር ምንም የለም። እንድ ጊዜ በአንድ አገር አንዲት አማኝ ክቤተክርስቲያን ስትመለስ የፀሐይ መነጽርዋ ጠፍቶባት የቤቷ ስርቻ ሁሉ ሳይቀር ፈለገችና ሳታገኘው ቀረች። ስድስት ወራት ከአለፈ በኋላ አንድ ቀን ከራስጌዋ ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ አንስታ ለማንበብ ስትክፍት የጠፋባትን መነጽርዋን አገኘችው። መነጽሩ የጠፋ ቀን ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሷን ይዛ ሄዳ ስለ ነበር የዚያን ቀን መነጽሩን አጣጥፋ ከመጽሐፉ መካከል አስቀምጣው ረስታው ኖሯል። ይህች ቤት መጽሐፍ ቅዱሷን

በየጊዜው የምታነብ ቢሆን ኖሮ ይህን ያህል ጊዜ ሳትቆይና ብዙም ሳትደክም መነጽሯን ወዲያው ልታገኘው ትችል ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል እንደዚች ሴት በየአለቱ አለማንበብ መንፈላዊ ሕይወትን ይጐዳል።

አንዳንድ ጊዜ ከአንዳንድ አማኞች አንደበት «ሥራ ስለ በዛብኝ መጽሐፍ ቅዱሴን ለማንበብ ጊዜ የለኝም።» የሚል ቃል ሲወጣ ይሰማል። በጣም የሚገርመው ጊዜ እንዳጡ የሚናገሩት እነዚህ ሰዎች በቀን ሁለትና ሦስት ጊዜ ለሥጋቸው የሚሆነውን ምግብ ለመብላት ጊዜ ማግኘታቸው ነው። የሆዳቸውን ጉዳይ ካልረሱና ጊዜ ካላጡ ነፍሳቸውንም ለአሥር እና ለአሥራ አምስት ደቂቃ ያህል ቃሉን ለመመገብ ጊዜ ሊያጡ አይገባም። «የሆድ ነገር ቀጠሮ አይሰጥም» ስንል መንፈላዊውንም ነገር ለነፍሳችን ለመመገብ ጭምር ቢሆን ክጉዳት ላይ አንወድቅም።

የእግዚአብሔር ቃል ለቀመስው ከማርና ከማር ወለላ ይልቅ ጣፋጭ ነው (መዝሙር 19፥10)። ነፍሳችንን ሁልጊዜ ይህንን ጣፋጭ ምግብ ብንመግባት መንፈላዊ ሕይወታችን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መንገዶች እየተገነባ ማደግ ይችላል።

ሀ) <u>እምነታችንያድጋል</u>፤ አንዳንድ ሰዎች የመንፈላዊ እንድገትን ምንነት መግለጽ ሲፈልጉ «በእምነት ማደግ» የሚለውን ቃል መጠቀም ይመርጣሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ከአንድ የበለጠ እምነት እንዳለ ያስተምረናል። ለመዳን የሚሆን እምነት አለ፤ የፀጋ ስጦታ የሆነና በእግዚአብሔር ላይ ጽኑ ትምክህትን፥ መተማመንን የሚጨምር እምነትም አለ። ስለ እምነት ዓይነት ለመዘርዘርና ለመጻፍ ዓላማ የለኝም። ይሁን እንጂ ስለ የትኛውም የእምነት ዓይነት ብናስብ፥ እምነት የሚዳብረውና የሚያድገው በእግዚአብሔር ቃል ብቻ እንደሆነ ማሳወቅ አወዳለሁ። ቃሉ የእምነት ምንጭ መሆኑን ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ውስጥ እንደሚከተለው ይጽፍልናል፤

«እምነት ከመስማት ነው። መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሮሜ 10፥17)።

የእግዚአብሔርን ቃል የሚመገብ ግለሰብ እምነተ ጠንካራ ነው፤ እግዚአብሔርንና ሥራውን በሚመለከት መንገድ ፍርሃትና ጥርጥር

የለውም። በትምህርት ነፋስም ወዲያና ወዲህ አይፍገመገምም። እንደ ጳውሎስ «ያመንሁትን አውቃለሁ!» ብሎ ባመነበት ይፀናል (2ጢሞ. 1፥12)። የእግዚአብሔር ቃል በነገሠበትም አብያተ ክርስቲያናት እምነተ ጠንካሮች ምዕመናን ይኖራሉ።

የእግዚአብሔር ቃል ጽኑ ነው። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከቃሉ በስተኋላ ይገኛል። የተናገረውንም ያደርጋል። ጌታችን፤ «ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም» ብሏል (ማቴ. 24፥35)። ስለዚህ ሕይወታችን መቆም የሚገባው በእዚህ መሠረት ላይ ነው። መንፈላዊ ሕይወታችን በየጊዜው መመገብ የሚገባውና መፋፋት የሚችለውም በዚህ ነው። ስለሆነም እምነት ገንቢ የሆነውን ቃል ነፍሳችንን ከመመገብ ቸል ልንል አይገባም፤ እያንዳንዳችን ለራሳችን ኃላፊነት አለብንና።

ለ) <u>ትኩረትንይሰጠናል</u>፤ የክርስትና ግብ ክርስቶስን መምሰል ነው። ክርስቶስንም ለመምሰል ክርስቶስን ማየትና ማወቅ ይጠይቃል። የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብ ሀሳባችንና አእምሮአችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያተኩራል። ስለዚህ እውነት ጌታ ራሱ ነግሮናል። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) እንዲህ ተጽፏል፤

«እናንተ በመጽሐፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው» (ዮሐንስ 5፥39)።

ጌታ ይህንን ቃል ሲናገር፤ የእግዚአብሔር ቃል የሚመሰክረው ስለ እርሱ እንደሆነ ለማስተዋል የሚረዳ ቃል ነው። ስለዚህ ቃሉን በማንበብ በኢየሱስ ላይ ማተኮር ይቻላል።

ናፖሊዮን በጦር መሪነት ችሎታው ያገኘውን ስኬት ያደንቁ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች አንድ ጊዜ ወደ እርሱ ቀረቡና፥ «እንዲህ ታላቅ መሪ ሊያደርግህ ያበቃህ ምስጢር ምንድነው?» ሲሉ እንደጠየቁት ይነገራል። ናፖሊዮንም ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ባጭሩ፥ «ትኩረት ነው!» ሲል መለሰላቸው። ናፖሊዮን በአንድ ጊዜ አንድ ነገር ላይ ብቻ ማተኮር የሚወድ ሰው ነበር ይባላል። ስለዚህ ጉዳይ ራሱ ናፖሊዮን ሲናገር እንዲህ ይላል፥ «አእምሮዬን የምቆጥረው ብዙ መሳቢያዎች

እንዳሉት የልብስ ሳጥን ነው። ክብዙዎቹ መሳቢያዎች መካከል አንዱን ብቻ እስብና እከፍታለሁ። በአንድ ጊዜ ሁሉንም አልከፍትም። በዚያ በከፈትኩት በአንድ መሳቢያ ውስጥ ያሉኝን ነገሮች አንድ በአንድ ካየሁ በኋላ የፈለግሁትን አድርጌ ስጨርስ መልሼ እዘጋውና ሌላውን መሳቢያ ደግሞ አክፍታለሁ። አሁንም እንደ በፊቱ በዚያ ውስጥ ያሉት ጉዳዮች ላይ አተኩሬ ጉዳዩን ስጨርስ ይህኛውንም ዳግሞ እዘጋና እንደ ገና ሌላ እከፍታለሁ። በዚህ ዓይነት በአንድ ጊዜ አንዱ ላይ ብቻ አተኩሬ ስጨርስ ቀኑ ይመሸና ሁሉንም ዘግቼ ምንም ሀሳብ ሳልይዝ ወደ አልጋዬ እሄድና ፀጥታ የሰፈነበትን ጣፋጭ እንቅልፌን እለጥጣለሁ።»

ናፖሊዮን ታሪክ የሚጠቅሰው ብቻ ሳይሆን ታሪክ ሠርቶ ያለፈም ሰው ነው። ለታሪክ ሠሪነት ካደረሱት ምክንያቶች አንዱ ይህን የመሰለ ችሎታው ነው።

አብዝተን የምናየውና ዓይናችን የሚያተኩርበት ነገር ሕይወታችንን የመሳብ ኃይል አለው። ለዚህ ጥሩ መረጃ የማገኘው በልጅነት ዘመናችን የነበረውን ሁኔታ መለስ ብዬ በትዝታ ዐይን በምቃኝበት ጊዜ ነው። ከሰፈራችን ልጆች መካከል እንዳንዶቹ አበክረው ፒያሳ መሄድና ፊልም ቤት መግባት ይወዱ ነበር። የዚያን ጊዜ ፊልም ቤቶች በብዛት የሚያሳዩት ሲኒማ ስለ አሜሪካን እረኞች (ካው ቦይስ) የተሠራውን ፊልም ነበር። ታዲያ እነዚያ ሲኒማ ቤት መግባት የሚያዘወትሩት ልጆች፥ የቻሉት አዲሱን ገዝተው ያልቻሉትም የአባቶቻቸውን አሮጌ ባርኔጣ ይወስዱና ጉንና ጉኑን ቆልመም አድርገው ዘመናዊ (ቴክስ) በመምሰል በአለባበስና በአረማመዳቸው ሁሉ የአሜሪካንን አረኞች እየመሰሉ በመካከላችን ይንጐራደዱ ነበር። ለው አብዝቶ በሚያየው ነገር ይሳባል።

ዛሬ ሰለጠኑ በሚባሉት የምዕራብ ክተሞች ውስጥ ብዙ ለማመን የሚያስቸግሩ የወንጀል ዓይነቶች ይፈጸማሉ። ወጣቶች አእምሮአቸው ሱስ በሚያስይዝ ዕጽ (ድራግ) አየላሸቀ ክስብዓዊነት የወጣ አስነዋሪ ተግባሮችን ያደርጋሉ። ታዲያ ብዙ የሥነ አእምሮ ሊቃውንት የችግሩን ምንጭ ሲጠቁሙ ወጣቶቹ እንደዚህ ሊበላሹ የቻሉት ክጮርቃነት እድሚአቸው ጀምሮ የሚያዩዋቸው የቴሌቭዥንና የሲኒማ ቤት ፊልሞች

እንደሆኑ ይናገራሉ። ስለሆነም አዘውትረን የምንመለከተው ነገር የባሕርይ ስበት እንደሚያመጣ የታመነበት ነገር ነው።

ይህንኑ ሐሳብ የሚያስረዳ የአንድ ቤተሰብ ታሪክም አንብቤአለሁ። አንዲት ሴት ሦስት ወንድ ልጆች ነበሯት። ይህች ሴት እነዚህ ልጆችዋ ሲያድጉ አንዱ መሐንዲስ፥ ሁለተኛው ጠበቃ፥ ሦስተኛው ነጋዴ እንዲሆኑላት ትፈልግ ነበር። ልጆቹ ለአካለ መጠን እስከ ደረሱ ድረስ በየጊዜው የምታስጠናቸውና እእምሮአቸው ውስጥ የምታስገባው ይህንን ምኞቷን ነበር። ነገር ግን ልጆቹ ባደጉ ጊዜ እንደ እናትየው ፍላጐት ሳይሆን ሦስቱም መርከበኞች ሆኑ። የእናትየው ምኞት ያልተሳካውና ሦስቱም መርከበኛ መሆን የቻሉበት ምክንያት ከምግብ ቤታቸው ፊት ለፊት እያዩ ያደጉት አንድ ሥዕል ስለ ነበር ነው። ሥዕሉ፥ መርከበኞች ከመድረኩ ተደርድረው እንደቆሙ፥ ባሕር ሰርጉዶ የሚሄድ የአንድ መርከብ ምስል ነበር። እነዚያ ልጆች ለመመገብ ጠረጴዛ ላይ በተቀመጡ ቅጥር ዓይናቸው የሚያርፈው በዚያ ላይ ነበር። ሥዕሉ የሚፈጥረው ሀሳብ በመንፈሳቸው ስለተሰረፀ ውሳኔያቸው ወደ መርከበኛነት እንዲያዘነብል ሳበው።

የምናተኩርበት ነገር የባሕርይ ስበት ባይኖረው ኖሮ የዕብራውያን ጸሐፊ በመልእክቱ ውስጥ ደጋግሞ፥ «የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ።» ሲል ባልመከረንም ነበር (ዕብ. 3፥1)። የተጠራነው «የልጁን መልክ» እንድንመስል ከሆነ ልጁን ለመምሰል የዓይኖቻችን በልጁ ላይ ማተኮር በጣም አስፈላጊ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዲህ ይላል፤

«እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይክደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያንን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን» (2ቆሮ. 3፥18)።

ሐዋርያው ማስተማር የፈለገው በፀጋ የዳኑ ክርስቲያኖች እንደ ብሉይ ኪዳን ሰዎች የጌታ ክብር በመጋረጃ እንደማይሸፈንባቸውና ኅሊናውን በግልፅ እይተው እንደ መስተዋት መልሰው ያንን ያዩትን

መልክ መፈንጠቅ እንደሚችሉ ነው። የክርስቶስን ክብር ማየትና ያንን ያየነውንም ሌሎች በእኛ ሕይወት ውስጥ እንዲያዩት ክብሩን መልለን ማንጸባረቅ እንችላለን ማለቱ ነው። ይህንን የክርስቶስን መልክ ደጋግመን ባየን ቊጥር ስለ እርሱ ቀደም ብለን ያላየነውን አዲስ ነገር እንመለከታለን። እርሱ ላይ ስናተኩር ስለ እርሱ ያለን እውቀት ይጨምራል። ይህም ባሕሪያችንን ይስባል። ለዚህ ነው ዮሐንስ በመልእክቱ፤

> «ወዳጆች ሆይ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም፤ ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለን፤ እርሱን እንድንመስል እናውቃለን» የሚለው (1ዮሐ. 3፥2)።

ስለማየት ስንናገር አየት አርገው መለስ ማለትን ሳይሆን ፍዝዝ ብሎ ስለ መመልከት መናገራችን ነው። ድሮ የባላገር ሰዎች ክተማ መጥተው ፒያሳ ላይ አሻንጉሊት ሊመለክቱ እዚያው ፈዘው ይቀሩ ነበር። ዓይናችንን በክርስቶስ ላይ ስለ ማድረግ ስንገልጽ ልክ እንደ እነርሱ ፍዝዝ ብለን ነፍላችን በእርሱ መወሰድና መመሰጥ እንዳለባት ማሳሰባችን ነው። ዓይናችን ክእርሱ ካልተነሳ ሁልጊዜ ስለ እርሱ አዳዲስ ነገሮች መማርን እናቆምም። አዳዲስ ነገሮችን ማወቃችን ደግሞ ለእድገታችን አስፈላጊ ነው። ብዙ ጊዜ አዲስ ነገር የማይማሩና የማይለማመዱ፥ ሁልጊዜ የድሮውን ብቻ ማውራት የሚወዱ ክርስቲያኖች ቢኖሩ የችግራቸው ምክንያት እስክ አሁን ድረስ የተመለከትናቸውን ነገሮች ካለማድረጋቸው የተነሳ ነው። ክርስቶስ ላይ ማተኮሩን ያላቆመ አማኝ ሕይወቱ በየጊዜው እድገትን ያላያል። እንደ እውነቱ ከሆነ ሰለሞን፥ «ያልሞተ ውሻ ክሞተ አንበሳ ይሻላል» መክብብ 9፥4 እንዳለው ሁሉ ዛሬ የማይኖሩትን ያለፈ ጀብዱ ከማውራት ዝም ማለቱ ይመረጣል። ይህንን ለማለት የምደፍረው በክርስትና ሕይወት መቆየትን ለማናናቅ ወይም ለማቃለል አይደለም። ነገር ግን ክርስቲያን ለጌታ ያለው ፍቅር ትኩስ መሆን እንዳለበት ለማሳሰብ ነው።

ዓይኖቻችን ኢየሱስ ላይ ያትኩሩ ስንል ምን ማለታችን ነው? ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ ዓይናችን ማየት ስለማይቻል ይህ እንዴት ይቻላል ብሎ ግራ የሚገባው ሰው ቢኖር መልሱ፥ ኢየሱስን ማየት

የምንችለው ቃሉን በመመልከትና በማንበብ ነው። በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ገጾች ውስጥ ሰጥላ መልከ ሆነ በቀጥታ የተጻፉት ነገሮች ሁሉ የሚጠቁሙት ወደ ኢየሱስ ነው። ስለዚህ እርሱ ላይ በማተኩራችን በባሕርይ እርሱን ወደ መምሰል እንድንሳብ የእግዚአብሔርን ቃል በየጊዜው እናንብበው።

ሐ) <u>አቅጣጫ የሚመራ ካርታ ይሆንልናል</u>፤ በምዕራቡ አገር ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ ለመሄድ ካርታ (ማፕ) መመልከት የተለመደ ነገር ነው። ካርታ ካሰቡበት ለመድረስ ይረዳል፤ ትክክለኛውንም አቅጣጫ ያላያል። ክመስመር ወጥተው አቅጣጫቸውን የሳቱትም ተመልሰው ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዲይዙ ያደርጋል። ካርታ (ማፕ) ወይም ኮምፓስ ባይኖር በሰማይ የሚበሩት አውሮፕላኖች በባሕር ላይ የሚሄዱትም መርከቦች ያለምንም ችግር ወደ አቅጣጫቸው ማምራት አይችሉም ነበር።

የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) በመንፈሳዊ ጉዞአችን የሚመራን ካርታ ነው። ይህንን ካርታ በየጊዜው የሚመለከት፥ አቅጣጫ ሳይስት የዘላለም ቤቱ እንደሚደርስ አያጠራጥርም። ለዚህ ነው ዳዊት፥ «ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴም ብርሃን ነው» ያለው (መዝ. 119፥105)። ያለ ብርሃን በጨለማ የሚጓዝ ሰው እንቅፋት ይመታዋል። በብርሃን የሚመላለስ ግን ማየት ስለሚችል እንቅፋቶቹን ሁሉ ተራምዶ ያልፋል። የእግዚአብሔር ቃል ዓይንንም ያበራል (መዝ. 19፥8)። ስለሆነም አጥርቶ የመመልከት ችሎታ ስለሚሰጠን ከመደናቀፍ ያድነናል።

ክርስቲያን ጉዞውን ለማደናቀፍ የሚፈልግ ጠላት አለው። ይህም ጠላት ዲያብሎስ ነው። ዲያብሎስ የጀመርነውን መንፈሳዊ ጉዞ በድል እንዳናበቃ እያደባ ወጥመዱንና አሽክላውን ይዘረጋብናል። እኛ ይህንን ወጥመዱን የምናፈርሰውና አሽክላውን የምንሰባብረው የእግዚአብሔር ቃል በጉዞአችን ሁሉ የሚመራን ካርታ ሲሆንልን ነው።

መ) <u>ሕይወታችንን ያፀዳል</u>፤ ጽዳትና ንጽህና ከጤንነትና ከደስተኝነት ጋር ዝምድና አላቸው። የንጽህና ጉድለት በሽታን ያመጣል፥ ስለምንፀዳዳበት ውኃ እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን።

አንደዚሁም በሥጋ ስላለንና ገና አንደ መልአኮች ስላልሆንን መንፈሳዊ ሕይወታችንን ቆሻሻ ሊነካውና አእምሮአችንም በመጥፎ ሀሳብ ሊረከስ ይችላል። በዚህ ጊዜ መጽዳት የምንችለው በአግዚአብሔር ቃል ነው። (መዝ. 119፥9) ላይ የሚከተለውን ቃል እናነባለን፥ «ጕልማሳ መንገዱን በምን ያነፃል? ቃልህን በመጠበቅ ነው» ይላል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን፥ «አናንተ ስለነገርኳችሁ ቃል ንጹሐን ናችሁ» ብሏቸዋል (ዮሐ. 15፥3)። የእግዚአብሔር ቃል ወደ ንስሐ ይመራናል። በቃሉ መንፈሳዊ ጤንነታችን ከተጠበቀ አድገታችን አይገታም።

ሠ) <u>መስተዋትነው</u>፤ የመስተዋትን ጥቅም ለመግለጽ መሞከር አስፈላጊ ነው ብዬ አላምንም፤ ሁላችንም በየዕለቱ እንጠቀምበታለን። ያዕቆብ በመልእክቱ የእግዚአብሔር ቃል ልክ አንደ መስተዋት ሆኖ እንደሚያገለግለን ያስተምረናል (ያዕቆብ 1፥23-25)።

እንደ መስተዋት ስለ እኛ ሕይወት ትክክለኛውን ነገር ቁልጭ አድርጐ የሚያሳየን የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስለሆነም መስተዋት በየዕለቱ ማየት አንደሚያስፈልገን ቃሉንም በየቀኑ ማንበብ አለብን። ቃሉን ከማንበብ ተግሳጽን፥ ምክርን፥ መጽናናትን አናገኛለን።

ረ) <u>ጠላትን የምንወጋበት ሰይፍ ነው</u>፤ ክርስቲያን ጠላት እንዳለው ቀደም ብለን ገልጸናል። የክርስቲያን ጠላት ዲያብሎስ፥ ክፉ በማድረግ የብዙ ሺህ ዓመታት ልምምድ ያለው ነው። በተፈጥሮውም አንደ እኛ በሥጋና በአጥንት የተወሰነ አይደለም፥ መንፈስ ነው። ፈቃዱን የሚፈጽሙለት የክፉት ሠራዊቶችም አሉት።

ይህንን በመገንዘብ ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶን ክርስቲያኖችን መጋደላቸው ከደምና ከሥጋ ጋር ስላይደለ በራሳቸው ኃይል ሰይጣንን ስለማያሸንፉት የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ እንዲለብሱ ይጠይቃቸዋል። ሰይጣንንና ሠራዊቱን መዋጋት የሚቻለው የእግዚአብሔርን የጦር ትጥቅ ስንታጠቅ ብቻ ነው። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች መታጠቅ ያለባቸው የጦር ትጥቅ ምን ዓይነት አንደሆነ አንድ በአንድ ይዘረዝርላቸዋል (ኤፌ. 6፥11-18)። በዚህ የጦር ትጥቅ ዝርዝር ውስጥ የቀረቡት ሁሉ ክአንዱ በቀር

የመከላከያ ትጥቆች ናቸው። ጠላትን ለማጥቂያ እንድንጠቀምበት የተሰጠን መሣሪያ አንድ ብቻ ነው። ይህም «የመንፈስ ሰይፍ» የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ዲያቢሎስን መግጠምና ማሸነፍ የምንችለው በዚህ ቃል ነው (ራዕይ 12፥11)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን ሰይጣን በተፈታተነው ጊዜ ያሸነፈው በእግዚአብሔር ቃል ነው (ማቴ. 4፥1-11)።

የእግዚአብሔር ቃል ሰይጣንን እስከ መሸገበት ምሽግ ድረስ አባሮ የሚመታው ሰይፍ ነው። ሰይጣን ምሽግ የሚሠራው የት ነው? 2ኛ ቆርንቶስ 10፥4-5 ላይ የሚከተለውን እናነባለን፥ «የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው። የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም አውቀት ላይ የሚነሳውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን። ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን።» ምሽግ፥ ጠላት ተጠናክሮ የሚቀመጥበትና ከዚያ ሆኖ ሌላውን ሰው ለማጥቃት ቀስቱን አቅመዝምዞ የሚወረውርበት ቦታ ነው። ከዚህ በላይ ባየነው ጥቅስ የሰው አእምሮ፥ የሰው አሳብ ጠላት የሚመሸግበት ምሽግ እንደሆነ እናያለን። ለአግዚአብሔር ባልተሰጠ አእምሮ ጠላት ይጠቀማል። በእርግጥ ልብ ብለን ብናስተውል፤ ሰይጣን የሚዋጋው ታንክ አስልፎ ሳይሆን አሳብ ይዞ ነው። ስለዚህ አእምሮን ለመያዝ የሚያደርገው ፍልሚያ ትልቅ ነው። ክፉ ሥራውን እንዴት እንደሚያከናውን አስቲ እናስብ። እንዳንድ ጊዜ ሰይጣን ሰዎችን በእጃቸው ወንጀል እንዲፈጽሙ ያደርጋል። ስለሆነም ሰይጣን የመሸገው በእጃቸው ውስጥ ነው ማለት አይደለም። እጅ የወንጀል ተግባር እንዲሠራ ትዕዛዝ የመጣለት ከአእምሮ ነው። በምላስ ሰዎችን ማረድና መግደል ይቻላል። ስለሆነም ሰይጣን በምላስ ውስጥ ይመሸጋል ማለት እንችልም። ምላስ ትዕዛዝ የምትቀበለው ከአእምሮ ነው። የሰውነታችን ብልቶች ሁሉ የሚታዘዙት በአእምሮ ነው። ሰይጣን አእምሮ ውስጥ ለመመሸግ የሚታገለው ለዚህ ነው።

በተግባር የምናደርገው ማንኛውም ነገር ከአእምሮ ውስጥ የመነጨ ሀሳብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «ሰው እንደሚያስበው ነው» ይላል (ምሳሌ 23፥7)። ሀሳባችንን በመለወጥ ሕይወታችንንም መለወጥ ይቻላል። የእግዚአብሔር ቃል አእምሮን የሚማርክ መሣሪያ ነው።

በዚህ ቃል በእግዚአብሔር ላይ የሚነሳውን ከፉ ሀሳብ ሁሉ እናፈርሳለን። ስይጣን የመሸገበትንም ምሽግ አስለቅቀን እግዚአብሔር እንዲነግሥበት እናደርጋለን።

ሸ) <u>በእግዚአብሔር በጐ ፈቃድ ውስጥ እንድንሆን ያደርጋል</u>፤ የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) የተሰጠበትን ዓላማ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት፤

«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጐ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል» ይላል 2ጢሞ. 3፥16-17። ከዚህ ጥቅስ የሚከተለውን እንማራለን፤

ሀ) መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በሰዎች ቢሆንም ደራሲው መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለሆነም ከማንኛውም ዓይነት ተራ መጻሕፍት የተለየና የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ እንደሆነ ተጠቅሶአል። ቃሉን በጽሑፍ እንዲያሰፍሩ ጸሐፊዎቹን የቀሰቀሰና የገፋፋቸው፤ የሚጽፉትንም የሰጣቸው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ደራሲው እርሱ ነው (2ኛ ጴጥ. 1፥21)።

ለ) ይህን ቃል በማንበብ የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጐ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆናል። በዚህ ቦታ «ፍጹም» የሚለው ቃል የቀረበው «ብቁ» ለማለት ነው። ቃሉ ብቃት የሚሰጥ ከሆነ ለአድገት አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ሐ) «ለበጐ ሥራ ሁሉ ያዘጋጃል» የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን በጐ ፈቃድ ያመለክታል። አንድ አማኝ የእግዚአብሔርን በጐ ፈቃድ ለማድረግ የሚችለው ሕይወቱ በእግዚአብሔር ቃል ሲገነባ ነው።

መ) ለትምህርት ይጠቅማል፤ ትምህርት እውነትን የምናውቅበት ነው። ስለ እግዚአብሔር እውነቶች መሠረታዊ ትምህርት (ዶክትሪን) የምንቀስመው ከዚህ መጽሐፍ ነው። ማወቅ (መማር) መልሕቁን እንዳጣለ መርከብ በአመንነውና በተቀበልነው እውነት ላይ

ነፍሳችን ተደላድላ እንድትቆም ይረዳል። በዚህ ቃል ትምህርት የማትቆም ነፍስና ያለ ኮምፓስ የሚበር አውሮፕላን አንድ ናቸው። ጉዞ መጀመራቸውን እንጂ ለመድረሳቸው አስተማማኝ ነገር የላቸውም።

ሠ) ለተግሣጽ ይረዳል፤ ሰለሞን «ተግሣጽን የሚወድ በሕይወት መንገድ ይሄዳል፤ ዘለፋን የሚተው ግን ይስታል» ይላል (ምሳሌ 10፥17)። የእግዚአብሔር ቃል ጥሩ ምክርና ተግሣጽ ይሰጠናል።

ረ) ልብን ለማቅናት ይጠቅማል፤ ከመስመር ስንወጣ ወደ ቀናው መንገድ የሚመልሰን የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ሰ) በጽድቅ ላለው ምክር ሁሉ ይጠቅማል፤ የሰውን አስቸጋሪ ባሕርይ የሚያርቅና የሚለውጥ ምክር ማግኘት የምንችለው ከእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህ ቃል ሕይወታችንን ይቀርጸዋል። በእግዚአብሔር በጐ ፈቃድም እንራመዳለን። ለአማኝ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ልክ አንድ ኮምፒዩተር ውስጥ ልዩ ልዩ ዝርዝሮችን (ዳታ) እንደመጨመር ነው። ኮምፒዩተር ሠርቶና አሳምሮ የሚሰጠው ጽሑፍ አስቀድሞ እንደስጡት ነገር (ኢንፑት) ነው። በእግዚአብሔር ቃል ሕይወታችን (በቃሉ የተሞላ) ፕሮግራም ሲሆን በበጐ ፈቃዱ መመላለስ ቀላል ይሆንልናል።

ብዙ ዕውቀት፥ መንፈሳዊ ብልጽግናና በረከት ልናገኝበት የምንችለውን ቃሉን ካለማንበብ የተነሳ በጉዞአችን መጨረሻ በፅፀት እንሞላለን። ይህ ሁናቴ የዐረቢያን በረሀ አቋርጠው ይጓዙ የነበሩ ሦስት መንገደኞችን ጥንታዊ አፈ ታሪክ ያስታውሰኛል። እነዚህ ሦስት መንገደኞች በድቅድቅ ጨለማ በረሀ አቋርጠው ሲሄዱ ከአንድ የደረቀ ወንዝ ይደርሳሉ። የደረቀውን ወንዝ አቋርጠው ለማለፍ ሲሉ ከጨለማ ውስጥ «ቁሙ!» የሚል ድምፅ ይሰሙና ይቆማሉ። ከዚያም፥ «ከእነዚህ የወንዝ ጠጠሮች የፈለጋችሁትን ያህል በኪሳችሁ ጨምሩ!» የሚል ትዕዛዝ ይሰማሉ። እነሱም ጐንበስ ይሉና እያንዳንዳቸው አንዳንድ ጠጠር ብቻ በኪሳቸው ይጨምራሉ። የስሙትም ድምፅ፥ «በሉ ካሰባችሁበት በደህና ያድርሳችሁ። ነገ ጥዋት ሦስታችሁም በአንድ ጊዜ በጣም ደሰ ይላችኋል፤ በጣም ደግሞ ታዝናላችሁ» ይላቸውና

ያስናብታቸዋል። በማግስቱ ጥዋት ካስቡበት ክተማ ሊደርሱ ሦስቱም በኪሳቸው የነበረውን ጠጠር አውጥተው ቢመለክቱ ወርቅ ሆኖ ስላገኙት በደስታ ተሞሉ። ነገር ግን አንድ አንድ ብቻ በማምጣት ፈንታ ብዙ ጠጠሮች ቢይዙ ኖሮ ሊኖራቸው ይችል የነበረውን ብልጽግና ደግሞ በማስብ በሀዘንና በፀፀት ተቃጠሉ።

እስከ አሁን እንደተመለከትነው የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠን መንፈሳዊ ብልጽግናና በረክት ብዙ ነው። በክርስቲያናዊ ባሕርይ መዳበር የምንችለው በዚህ ቃል ነው። ይህንን እድል ላንጠቀምበት ብንቀር በሕይወታችን መጨረሻ ላይ እንደ ሦስቱ መንገደኞች ስለ አመለጠን እድል መጸጸታችን አይቀርም። ከእንደዚህ ያለ ፀፀት ለመዳን ከፈለግን መጽሐፍ ቅዱሳችንን ዘወትር እናንብበው።

2ኛ <u>ጸሎት</u>

ክእግዚአብሔር ቃል ጋር ለእድገት ከሚረዱን ነገሮች አንዱ ጸሎት ነው። ጸሎትና ቃሉ ላይለያዩ አብረው የሚሄዱ ናቸው። ለጸሎት የግድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከቃሉ ማወቅ ይጠይቃል። የእግዚአብሔርንም ቃል በፀሎት አንዲሠራ ካላደረግነው አይዋሀደንም። በሥጋዊው ሕይወታችን መመገብ አስፈላጊ የሆነውን ያህል መተንፈስም አስፈላጊ ነው። አዲስ አየር መቀበል፤ በሳንባችን ውስጥ ያለውን የሠራ አየር ደግሞ ማስወጣት ለጤንነት አስፈላጊ ነው። ጸሎት በመሠረቱ ክእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ቢሆንም፥ የሕይወታችንን ሸክም አራግፈን አዲስ ብርታትንና ኃይልን የምንቀበልበት ነው። መተንፈስ ባይኖር መኖር እንደሌለ ያለ ጸሎት የክርስትና ሕይወትን መኖር አይቻልም።

በጸሎት ለእግዚአብሔር የልባችንን ሐሳብ ሁሉ እንነግራለን። በጸሎት እግዚአብሔርም ለልባችን ይናገራል። ስለሆነም ጸሎት ክመንፈሳዊ አባታችን ጋር የምንነጋገርበት፥ ድምጹንም የምንሰማበት መንገድ ነው። እግዚአብሔር በማንኛውም ሰዓት በጸሎት ብንጠራው እንደሚሰማን በቃሉ ተስፋ ሰጥቶናል (ኤር. 33፥3፤ መዝ. 65፥2)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳ በሥጋ በነበረበት ጊዜ ክአባቱ ጋር የነበረውን ግንኙነት የጠበቀው በጸሎት ነው። አዘውትሮ መጸለይ ልማዱ እንደነበር በወንጌሎች ተጽፏል (ሉቃስ 22፥39)። ብዙ

የእግዚአብሔር ሰዎች የድል ምስጢር ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው የጸሎት ግኑኝነት ጥብቅ በመሆኑ እንደሆነ ብሉይና አዲስ ኪዳን ያስተምራሉ።

እግዚአብሔር ሰዎችን ሊናገርበት የሚችልባቸው ብዙ መንገዶች አሉት። በቃሉ፥ በሕልም፥ በራዕይ፥ በነቢያትና በሌሎችም ብዙ መንገዶች እግዚአብሔር ሰዎችን መናገር ይችላል። ሰዎች ግን ለእግዚአብሔር መናገር የሚችሉት በአንድ መንገድ ብቻ ነው። ከጸሎት ሌላ ለእግዚአብሔር መናገር የምንችልበት መንገድ የለም። ስለሆነም አባቶቻችን «አንድ ዓይን ያለው በጠጠር አይጫወትም» እንዲሉ ክርስቲያን የጸሎት ግንኙነቱን ችላ ማለት ወይም ማቋረጥ የለበትም። ለክርስቲያን አለመጸለይ ኃጢአት ነው (1ኛ ሳሙ. 12፥23)። ክርስቲያን መጸለይን እንዳያቆም የታዘዘው ለዚህ ነው (ሉቃ. 18፥1፤ 1ተስ. 5፥17)።

ስለ ጸሎት ምንነትና ጥቅም ለመዘርዘር ሌላ አንድ መጽሐፍ ስለሚጠይቅ በዚህ ክፍል ውስጥ ስፊ ማብራሪያና ትምህርት ለመስጠት ዓላማዬ ባይሆንም፥ ክዚህ በታች በዝርዝር የማቀርባቸው ነጥቦች ሁሉ ፀሎት በእንዴት ያለ መንገድ እድገታችንን ሊረዳ የሚችልበት ሃሳብ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው።

ሀ) በጸሎት እግዚአብሔርን መምሰል እንማርበታለን። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ጊዜ ደጋግመን የመንፈሳዊ አድገት ግቡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል እንደሆነ ተመልክተናል። ለመምሰል የምንፈልገውን በቅርብ ማወቅ አስፈላጊ ነው። በቅርብ የማናውቀውንና ስለ እርሱ ምንም ነገር የማናውቀውን ሰው መምሰል አስቸጋሪ ነው። በጸሎት ክእርሱ ጋር በመነጋገር ጊዜ እናጠፋለን። በሥጋ ከወለዱን ወላጆቻችን ጋር በየጊዜው በመነጋገር ያላለፍነው ጊዜ ሐሳባቸውን ለማወቅ፥ ምክራቸውን ለመስማት፤ ማነጋገራቸውን ለመረዳትና ምላሌነታቸውን ለመከተል ረድቶናል። ልክ እንደዚሁ ከእግዚአብሔር ጋር የምናሳልፈው ጊዜ የሰማዩ አባታችንን ባሕርይ እንድናውቅና እርሱን መምሰል እንድንችል ይረዳናል።

ለ) በጸሎት የእግዚአብሔርን ምስጢር እናውቃለን። ዮሐንስ ራዕዩን መቀበል የቻለው፤ ዳንኤልም ስባቢሎን ጠቢባን ሁሉ ያስቸገረውን፤ የናቡከደናፆርን ሕልም ፍቺ ያወቀው፤ የጸሎት ሰዎች በመሆናቸው ነው። አነዚህ ሰዎች፥ በመንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር ያልተቋረጠ ግኑኝነት እንደነበራቸው በመጽሐፍ ውስጥ አናነባለን (ዳን. 2፥17-24፤ ራዕይ 1፥9-10)።

እኛ ሁሉን የማወቅ ችሎታ የለንም። እግዚአብሔር ግን ሁሉን አዋቂ ነው። ስለሆነም ከእርሱ ጋር ባለን የጸሎት ግንኙነት ለኑሮአችንና ለሕይወታችን ጠቃሚ እውቀት እናገኛለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸውን የምናነበው የአግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ምስጢር ያወቁት በጸሎት ላይ እያሉ ወይም የጸሎት ሕይወታቸው የተጠበቀ በመሆኑ ነው።

ሐ) ጸሎት የሰማይን ደጆች የሚከፍት ቁልፍ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ከርስቶስ በወንጌል ውስጥ፥ «ለምኑ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ ታገኙማለችሁ፤ መዝጊያውን አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤ የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል» ብሏል (ማቴዎስ 7፥7-8)። ስለዚህ ጸሎት ከእግዚአብሔር የምንጠይቀውን እንድንቀበል ስማያትን የምንከፍትበት ቁልፍ ነው።

መ) ጸሎት በእግዚአብሔር ላይ መመካትንና መተማመንን ያስተምረናል። የከርስትና ሕይወትን ከሚጐዱት ነገሮች እንዱ ጥርጥር ነው። ጥርጥር ፍርሀትንና ጭንቀትን ያስከትላል። ነገር ግን ለጸሎት በምንበረከከበት ጊዜ እግዚአብሔር በመንፈሱ ከሚያደርግልን አስደናቂ ነገሮች ውስጥ እንዱ በእርሱ መተማመንን መፍጠር ነው። በቃሉ «እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ነገር ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት» እንደሚል (1ጴጥሮስ 5፥7) ጭንቀታችንን ለእርሱ ስጥተን በእርሱ መተማመንን እንማራለን። ይህ ለጤናማ መንፈሳዊ እድገት ጠቃሚ ነው።

ሠ) በጸሎት ኃይልን እንቀበላለን፥ ብዙ ጊዜ መንፈሳዊ ኃይል ያላቸው ሰዎች ሁሉ የጸሎት ሰዎች ናቸው። ጸሎት ከኃይል ምንጭ ከሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያገናኘናል። ሐዋርያት ኃይልን የለበሱት በጸሎት ውስጥ እያሉ ነው። ዲያብሎስም ይህን ስለሚያውቅ ከሌላው ጊዜ ይልቅ ከርስቲያን ለጸሎት ሲንበረከክ ጉልበቱ ይርዳል። ምክንያቱም በድካም የተንበረከከው ከርስቲያን ከተንበረከከበት ሲነሳ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ተውሶ እንደሚነሳ ስለሚያውቅ ነው። ዲያብሎስ ከሌሎች ነገሮች አስበልጦ ጸሎትን ለማስናከል የሚደከመው ለዚህ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን የምንቀበለው በጸሎት ነው (ሉቃ. 11፥13)። የእግዚአብሔርንም ሥራ መሥራት የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። የእግዚአብሔርን ሥራ ያለመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሥራት የሚፈልግና የጀርባ አጥንት የሌለው ስው አንድ ናቸው መቆም አይችሉምና። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናያቸው ግላዊና የማሕበር መንፈሳዊ መነቃቃት በሙሉ ለጸሎት የተሰጡ መልሶች ናቸው (2ዜና 7፥14)።

ከላይ ከዘረዘርናቸው ሌላ በጸሎት ትህትናን እንማራለን፤ ትዕግሥትን እንለማመዳለን፤ ፍቅራችን ትኩስ ሆኖ እንዲቆይ እንጠብቃለን፤ እነዚህ ሁሉ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ብልጽግና ጠቃሚ ነገሮች ናቸው።

3ኛ <u>የመንፈስቅዱስሙላት</u>

«መንፈሳዊ» የሚለው ቃል ራሱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተያያዘ ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊነት የለም። መንፈሳዊ ሕይወት ያገኘነው ከቃሉና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም በመወለዳችን ነው። ከርስቲያን ከዳነ በኋላ አካሉ የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ ይሆናል (1ቆሮ. 6፥19)።

መጽሐፍ ቅዱስ በደህንነት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚኖረን ያስተምራል። ነገር ግን ከርስቲያን ስለ መንፈስ ቅዱስ ያለው ልምምድ በዚያ ብቻ ማብቃት እንደሌለበት ደግሞ ይነግረናል። ከዳንን በኋላ እያንዳንዳችን በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ልምምድ ሊኖረን ይገባል። እንዲያውም በአንድ ስፍራ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እንደ ሌሎቹ

የእግዚአብሔር ትዕዛዞች ሁሉ ለእማኞች የተሰጠ ትዕዛዝ ሆኖ እናያለን። ትዕዛዙ ያለው ኤፌሶን 5፥18-20 ላይ ነው። «በመንፈስ ተሞሉ . . .» ይላል።

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የክርስትናን ሕይወት ልንኖርበት የምንችልበትንና ወንጌልን የምናገለግልበትን ኃይል ከመስጠቱም ሌላ ሕይወታችን በመንፈስ ቁጥጥር ሥር እንዲውል ያደርጋል። በመንፈስ ተሞሉ የሚለው ትዕዛዝ በተሰጠበት ቦታ «በወይን ጠጅ እትሞሉ» የሚል ቃል አብሮ ተጽፏል። በወይን ጠጅና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ምንም ተመሳሳይነት የለም። ሐዋርያው ሁለቱን በማነፃፀር ያቀረበበት ዋና ምክንያት ሁለቱም የእንድን ሰው ድርጊት የመቆጣጠር ችሎታ ስላላቸው ነው። በአልኮል የሚሞሉ ሰዎች በአልኮል ቁጥጥር ሥር ይውላሉ። ስለዚህ ከሚናገሩት ንግግር እስከ ድርጊታቸው ድረስ ሕይወታቸው በቁጥጥር ሥር ውሎ የሚታዘዘው ለአልኮል ኃይል ነው። ይህንን በማወቅ ሕብረተሰቡ ሰዎች ጠጥተው ወንጀልን በሚፈጽሙበት ጊዜ ድርጊቱን የፈጸሙት በአልኮል ኃይል እንደሆነ ያወራሉ። በአልኮል ቁጥጥር ሥር የዋለ ንግግሩ፥ እርምጃው፥ አስተሳሰቡ እንኳ ሳይቀር ይለወጣል። በአገራችን የታወቀውን ካቺካላ እንዳንድ ሰዎች «ሞኝ አንግሥ» የሚሉት ስለዚህ ነው። አልኮል በቁጥጥሩ ሥር የማድረግ ኃይል አለው።

መንፈስ ቅዱስ ከወይን ጠጅ ጋር የተነፃፀረበት መንገድ ይህ ሲሆን፤ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትም እንደዚሁ ሕይወታችን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ያደርጋል። መንፈስን ስንሞላ መንፈሳዊ እርምጃችን ሁሉ ይቀየራል፤ ድርጊታችንም ሁሉ ይለወጣል። በመንፈስ ተሞሉ የሚለው ቃል ከተጻፈበት ቁጥር ቀደም ብሎም (ኤፌሶን 5፥16-18) ላይ የሚከተለው ምክር ቀርቦልናል፥ «ነገር ግን አላለሁ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙ ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና አነዚህ እርስ በእርሳቸው ይቀዋወማሉ። ስለዚህ የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።»

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ፦

ሀ) የሥጋ ሥራ እንዳይገዛን ያደርጋል (ገላትያ 5፥16)።

ለ) የመንፈስ ፍሬዎች በሕይወታችን እንዲዳብሩ ይረዳል።

ሐ) ከዚህ በፊት እንዳየነው ኃይልን እናገኛለን። ኃይልን መልበሱ ለመቆምም ሆነ በእድገት ጐዳና በድል ለመሄድ ለሌሎችም የወንጌሉን ብርሃን ለማብራት አስፈላጊ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በመንፈስ በመሞላትና በመጠመቅ ምሳሌነትን ትቶልናል (ማቴ. 3፥16)።

መ) መንፈስ ቅዱስ ጸሎታችንን ያግዛል (ሮሜ 8፥26)። ይሁዳም በመልእክተ በመንፈስ ጸልዩ ሲል ይመክረናል (ይሁዳ 20)።

ሠ) በመንፈስ መሞላት ዘጠኙ የፀጋ ስጦታዎች በሕይወታችን እንዲሠሩ ያደርጋል።

ረ) መንፈስ ቅዱስ የእሳትነት ባሕርይ ስላለው «የመንፈስ ኃጢአት» በመባል የሚታወቁትን እንደ ትዕቢት፥ ኩራት፥ ምኞት የመሳሰሉትን ኃጢአቶች ከውስጣችን ያቃጥላል። መንፈስ ቅዱስ በጌታ ላይ ሲወርድ በእርግብ አምሳል ነበር (ማቴ. 3፥16-17)። በጌታ ኢየሱስ ሕይወት ውስጥ መወገድ የሚገባቸው ይህንን የመሰሉ ባሕሪያት ስለሌሉ መንፈስ ቅዱስ በርሱ ላይ በእሳት መልክ አልወረደም። ነገር ግን በሐዋርያት ላይ በወረደ ጊዜ የመጣው በእሳት መልክ ነበር (የሐዋ. 2፥3)። ምክንያቱም ከሰዎች ውስጥ መቃጠልና መንጻት የሚገባው ነገር አለ።

መጥምቁ ዮሐንስ በእርሱና በጌታ አገልግሎት መካከል ያለውን ልዩነት ሲገልጽ «እኔ በውኃ እጠምቃችኋለሁ። ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ ይበረታል። እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል» ይላል (ማቴ. 3፥11)። ይህ ቃል ስለ መንፈስ ቅዱስ የእሳትነት ባሕርይ ቀደም ሲል ያቀረብነውን ሀሳብ ይደግፋል።

መንፈስ ቅዱስ ከሥላሴ አንዱ ነው። ስለሆነም ወደ አማኝ ሕይወት በኃይል በሚመጣበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ክብርና ልዕልና ይዞ ይመጣል። በብሉይ፤ እግዚአብሔር በእሳት መልክ ተገልጿል። የዕብራውያን ጸሐፊም፥ «አምላካችን በእውነት የሚያቃጥል እሳት ነው» ይላል (ዕብ. 12፥29)።

በመንፈስ ስንሞላ ወደ እኛ የሚመጣው ይህ የአላት ክብር የሚያጠፋ ሳይሆን የሚያለማ ነው። አላት አንድን ነገር ከነበረበት ወደ ሌላ ነገር (ለምሳሌ አንጨትን ወደ አመድነት) ይለውጣል። ብረትንም በማቅለጥ ከነበረበት ቅርጽ ወደ ሌላ ቅርጽ ይቀይራል። መንፈስ ቅዱስ የእኛንም ሕይወት እንደዚህ የመለወጥ ኃይል አለው። የኃይልና የግለትም ምንጭ ስለሆነ የፍቅራችንን ሙቀት የሚጠብቅ እርሱ ነው።

4ኛ <u>አምልኮ</u>

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው በውስጡ ያለው ነፍሱና መንፈሱ እርሱን ለማምለክና ለማክበር እንዲጠሙ አድርጎ ነው (መዝ. 42፥1-2)። ስለዚህ አምልኮ ክሕይወት (ከመኖር) ተለይቶ መታየት የለበትም።

ቀደም ሲል ጸሎት ለእድገት እንድሚጠቅም ጠቅሻለሁ። እንዲሁም ጸሎት ከአምልኮ ተለይቶ ሊታይ ስለማይችል የሰው ነፍስ እግዚአብሔርን ለማምለክ እንድትዘጋጅ ያደርጋታል። ነፍላችን እግዚአብሔርን ማምለክ ስትችል ትለመልማለች። ስለሆነም ጌታን በማምለክ የምናጠፋው ጊዜ ሁሉ በከንቱ አይደለም። አምልኮ በመንፈስ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ስለሚያደርሰን አምላካዊ ክብሩንና ሞገሱን እንድናውቅ ስለሚያደርግ ለመንፈሳዊ እድገታችን ጠቃሚ ነው።

5ኛ <u>ጊዜ</u>

ለእድገት ጊዜ ያስፈልገዋል። ወዲያው ተወልዶ ወዲያው ያደገ ማንም የለም። በመንፈሳዊ ሕይወትም ዳግም እንደተወለደ ወዲያው ወደ መንፈሳዊ ብስለት የደረሰ ማንም የለም። ምንም ዓይነት እድገት ጊዜ ይወስዳል። በተለይም መንፈሳዊው እድገት የቃሉን እውቀትና ያወቁትንም ልምምድ ማድረግ ጭምር ስለሚጠይቅ በአንድ ጊዜ አይገኝም። እድገት በጊዜ ውስጥ ስናልፍ የሚመጣ ነገር ነው። ጢሞቴዎስ የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን በሚመርጥበት ጊዜ አዲስ ክርስቲያን እንዳይሾም መመሪያ የተሰጠው ለዚህ ነው።

ጊዜ ለእድገት አስፈላጊ ነው ስንል እንዳንላላት መጠንቀቅ ያለብን ነገር አለ። መንፈላዊ ብስለት ጊዜ ያስፈልገዋል ማለት፥ ብስለት ዓመት

የመቁጠር (ካለንደር) ጉዳይ ነው ማለት አይደለም። በተጨማሪም፥ ጊዜ፥ ከሚረዱት ነገሮች አንዱ እንጂ በራሱ ብቻ ሊያሳድግ የሚችል ነገር አይደለም። ለማደግ ጊዜ መውሰድና፤ ምንም ያልተጠቀምንበትን ዓመታት መቁጠር የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አንድ ሰው ክዳነ አሥር ወይም አሥራ አምስት ዓመት ሊሆነውና ምንም መንፈሳዊ እድገት ላይታይበት ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ክዳነ ብዙ ጊዜ ያልሆነው አዲስ ክርስቲያን አስደናቂ የእድገት ግስጋሴ ሊታይበት ይችላል። ጊዜ የሚጠቅመው ለሚጠቀምበት ብቻ ነው።

የሰዎች ሁሉ የአካል እድገት የተለያየ ሊሆን የሚችለው ሁላችንም በአንድ ቀን እኩል ስላልተወለድን ብቻ ላይሆን ከምንመገበው ምግብ፥ ከምናገኘው እንክብካቤና ክጤንነታችን የተነሳ የእድገታችን መጠን ይለያያል። በመንፈሳዊም በኩል ልክ እንደዚሁ ነው። ለምሳሌ ከአዲስ አበባ አቃቂ ደርሶ ለመመለስ ለሁለት ሰዎች አንድ ዓይነት የሞተር ቢስክሌት ቢሰጣቸው፤ በተሰጣቸው የሞተር ቢስክሌት ዓይነትና አዲስነት ምንም ልዩነት ባይኖር፤ ሁለቱ ሰዎች አቃቂ ደርሰው ሊገቡ የሚችሉበት ጊዜ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ልዩነቱ የሚመጣው ከጊዜ አጠቃቀማቸው ማለትም በሰዓት ምን ያህል ኪሎ ሜትር ለመንዳት በመቻላቸውና ከአነዳድ ችሎታቸው የተነሳ ነው። አንደዚሁ በአንድ ጊዜ ወደ ጌታ በመጡ ሰዎች መካከል እንኳን ለሕይወታቸው ከሚያደርጉት ልዩ ልዩ ነገሮች የተነሳ እድገታቸው ሊለያይ ይችላል። ጊዜ አስፈላጊ ቢሆንም በራሱ ብቻ አይጠቅምም ለምሳሌ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች አንደነበሩ በግልጽ የምናነበው ነገር የለም። ይልቁንም አማኞቹ እርስ በእርስ እየተጣሉ ፍርድ ቤት የሚካሰሱ መሆናቸው ሲሰማ ሐዋርያው ጳውሎስ ተገርሞ «በመካከላችሁ ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን?» ይላል (1ቆሮ. 6፥5)። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ገና የዳኑ አዲስ ክርስቲያኖች አልነበሩም። በመካከላቸው አንድ ሽማግሌ የሚሆን አስተዋይ ሰው መጥፋቱ ጊዜ በራሱ ብቻ ለእድገት እንደማይጠቅም መረጃ ይሆናል። ሆኖም ጊዜን በጥቅም ላይ ካዋሉት ለእድገት የሚጠቅም መሆኑ የማይካድ ሐቅ ነው።

ጊዜና እድገት ያላቸውን ግንኙነት ያጤንኩት ገና ልጅ ሆኜ ነው።

ከአዲስ አበባ ከተማ ወጣ ብሎ እናቴ አንድ ርስት ነበራት። በዚያ ቦታ ሦስት ትላልቅ ዛፎች ነበሩ። ወደዚያ በሄድን ቁጥር እነዚህን ዛፎች መመልከት እወድ ነበር። በጣም የሚደንቀኝ የቁመታቸው ትልቅነትና ግዙፍነት ነበር። ዛፎቹ የተተከሉት በቅድመ አያቴ እንደነበረ እናቴ ስለ ነገረችኝ፥ በማያቸው ጊዜ በጣም ይገርመኝ ነበር። እኔ ቅድመ አያቴ ቀርቶ አያቴም ላልወለድ ማይጨው ላይ ስለ ሞቱ አላውቃቸውም። እነዚያ ዛፎች ግን ብዙ ዘመን ስለ ኖሩ አያቴንና ቅድመ አያቴን የሚያውቁ ይመስለኝ ነበር። በጊዜ ተጠቅመው ስላደጉ። አንደዚሁ እኛም ጊዜን ከተጠቀምንበት አናድጋለን። ለማደግ የምንፈልገው የሽምበቆ ያህል ቢሆን ስድስት ወር፤ የጐመን ያህል ቢሆን አንድ ክረምት ብቻ ይወስድብናል። ነገር ግን ለወፎች ማረፊያ ለሰዎችም ከጥላቸው ሥር ቁጭ ብለው የማውጊያ ቦታ የሆኑትን እነዚያን ሦስት ዛፎች ያህል ማደግ ከፈለግን ጊዜ ያስፈልገናል።

6ኛ <u>መንፈሳዊ አካባቢ</u>

ጥሩ አካባቢ ለዕፅዋት አድገት አስፈላጊ እንደሆነ እናውቃለን። ለሰው ልጆችም ጤናማ አድገት የአካባቢው ንጽህና አስፈላጊ ነው። የቆሻሻ መጣያና የጤና ጠንቅ የሆኑ ጀርሞች በቀላሉ ሊተላለፉ በሚችሉበት አካባቢ የሚያድጉ ሕፃናት ሕይወታቸው በበሽታ ምክንያት ቶሎ ሊቀጭ ይችላል። በተጨማሪም ሕፃናት የሚያድጉበት አካባቢ ሁከት፥ ረብሻ፥ ስካርና ወንጀል የተለመደበት ቢሆን የብዙ ታዳጊ ሕፃናት ሕይወት ሊበላሽ ይችላል።

በመንፈሳዊ ሕይወትም መልካም አካባቢ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ለጓደኝነት የምንቀርባቸውና አብረን የምንውላቸው ሰዎች፤ የምንሰበሰብበት ማኅበረ ምዕመናንና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖቻችን መንፈሳዊ አካባቢዎቻችን ናቸው። እነዚህ ሁሉ ለእድገታችን አስፈላጊዎች ናቸው።

ወደ መልካሙ የሚስቡንና ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን ስናገኝ ለመንፈሳዊ እድገታችን ምቹ ሁኔታ ይፈጥሩልናል። ነገር ግን መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚያደክም ስበት ያላቸው ሰዎች ሲያጋጥሙን ጎጂነታቸውን አውቀን መሸሽ አለብን፥ «ከፉ ባልንጀርነት መልካሙን

አመል ያበላሻል» (1ቆሮ. 15፥33)። መጽሐፍ ቅዱስ ለጓደኝነትና ለኅብረት የምንጠጋቸውን ሰዎች በሚመለክት መንገድ ብዙ ምክር እንደሚሰጥ አንርሳ (መዝ. 1፥1፤ 2ኛቆሮ. 6፥14-16 መዝ. 133፥1-3)።

7ኛ <u>ሕይወትንበየጊዜውመመርመር</u>

አንድ ሕፃን ከተወለደ በኋላ ወላጆቹ ከሚያደርጉለት ጥንቃቄ ውስጥ አንዱ ጤንነቱን በየጊዜው ማስመርመርና ክትባት እንዲወስድ ማድረግ ነው። ይህ ሁሉ የሚደረገው በሽታ ከመያዙ በፊት በጊዜ እንዲታይና ጤንነቱ እንዲጠበቅ ነው። ጤንነትን መመርመር ለህፃናት ብቻ ሳይሆን ለአዋቂዎችም አስፈላጊ ነው። በአገራችን ይህ ብዙ ባይለመድም፥ በሽታ ተይዘው በአልጋ ከመተኛት በፊት ጤንነትን መመርመሩ በጣም ጠቃሚ ነው። በምዕራቡ አገር የጤንነት ምርመራ ማድረግ በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ ተለምዷል።

መንፈሳዊ ሕይወትም ልክ እንደ አካላችን ጤንነት በየጊዜው ምርምራ ያስፈልገዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ በጻፈው መልእክቱ እንዲህ ይላል፥ «ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና። ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል። ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር፤» (1ኛ ቆሮ. 11፥29-31)። በዚህ ክፍል የራሳችንን ሕይወት መመርመርና መፈተን እንደሚገባን እናያለን። ሕይወትን ካለመፈተንና ካለመመርመር የተነሳ ኃጢአታቸውን ማየትና ንስሐ መግባት ስላልቻሉ ከቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መካከል ብዙዎች ሀ) በድካም የወደቁ፤ ለ) የታመሙ፤ ሐ) የሞቱም እንኳ እንዳሉ እናያለን። ሕይወትን በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መመርመር ከዚህ አደገኛ ሁኔታ ይጠብቃል። በተጨማሪም 1ኛ ቆሮ. 10፥12 ላይ «የቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል። ስለሆነም ራስን በመመርመር ንስሐ መግባትና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት በመጠበቅ መጓዝ አለብን። ዳዊት እንዳለው፥ «አቤቱ መርምረኝ፥ ልቤንም እወቅ፤ ፈትነኝ፤ መንገዴንም

እወቅ፤ በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ፤ የዘላለምንም መንገድ ምራኝ» በማለት መጸለይ አለብን (መዝ. 139፥23-24)። ለማደግ የምንችለው በጤንነት ስንመላለስ ነው።

8ኛ <u>ሥጋን ማክሰት</u>

ክርስቲያን ሦስት ጠላቶች አሉት። እነርሱም ሀ) ሥጋ፤ ለ) ዓለም፤ ሐ) ሰይጣን ናቸው። እነዚህ ሦስቱ ጣምራ ጠላቶቹ መንፈሳዊነቱን ይፃረራሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ‹ሥጋ› የሚለው ቃል ያለው ትርጉም ብዙ ዓይነት ነው። በአብዛኛው ስው ሥጋ በመባል የሚታወቀው የሰዎችንና የእንስሳትን አጥንት ያለበስውና በቆዳ የተሸፈነው ስውነት ነው። ነገር ግን በተጨማሪ ‹ሥጋ› የሚለው ቃል ዝምድናን ለመግለጽ እንጠቀምበታለን፥ ከዚያም በላይ ሕያዋን የሆኑትን የሰዎች ዘር በሙሉ «ሥጋ ለባሽ» በማለት እንጠራቸዋለን (1ኛ ቆሮ. 1፥26፤7፥28፤ ገላ. 1፥16፤ ሮሜ 4፥1፤9፥3-5)።

«የነፍሳችን ጠላት ነው» የምንለው ሥጋ የነፍሳችን ማደሪያ የሆነውን አካላችንን አይደለም እንደዚያ የመሰላቸውና መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ቦታ «ብልቶቻችሁን ግደሉ» (ቈላ. 3፥5፤ ሮሜ 8፥13) የሚለውን ያነበቡ ሰዎች መንፈሳዊ የሚያደርጋቸው መስሏቸው አካላቸውን ያጐሳቈሉና የጐዱ አሉ። ዛሬም በዚሁ አስተሳሰብ አካላቸውን የሚቀጡ አሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ ገላትያ 5፥24 ላይ «የክርስቶስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱ ጋር ስቀሉ» ብሎ ሲናገር ራሳቸውን በእንጨት ላይ የሰቀሉ ሰዎች አሉ ማለቱ አይደለም።

ለመንፈሳዊ ሕይወት ተቃራኒ ስለሆነው ሥጋ ስንናገር አካላችንን መጥቀሳችን ሳይሆን ከመንፈስ ክልል ውጭ ስለሆነው የልብ ምኞትና ሐሳብን ሁሉ ስለሚያጠቃልለው ውስጣዊ የሕይወት ክፍል መናገራችን ነው። በመንፈስ ክልል መኖርና በሥጋ መኖር ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። በዚህ ሥጋ በምንለው ከመንፈሳዊ ክልል ውጭ በሆነው የልብ ምኞትና ፍላጐት መካከልና በዳግም ልደት ባገኘነው አዲስ ሕይወት መካከል የማያቋርጥ ትግል አለ (ገላ. 5፥16-24)። ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይቀዋወማሉ። የሥጋ ፍላጐትና ምኞት

ኃጢአት የሆኑትን ነገሮች አንድነሥራ ይገፋፋል። በገላትያ መልእክት ሥጋ የሚያሠራን ኃጢአታዊ ተግባሮች አንድ በአንድ ተዘርዝረዋል። በዚያው አንጻር ደግሞ በመንፈስ ክልል ውስጥ ብንመላለስ መንፈስ በሕይወታችን ሊፈጥራቸው የሚችለው ፍሬዎች ምን ምን እንደሆኑም ተጽፏል። የሥጋ ሥራዎችንና የመንፈስ ፍሬዎችን አንድ በአንድ በማነጻጸር ብንመለከታቸው በመካከላቸው ትልቅ ቅራኔ እናያለን።

መጽሐፍ ቅዱስ «ስቀሉ» «ግደሉ» የሚለው የዚህ ዓይነት ምኞትና ተግባር ምንጭ የሆነውን ሕይወት ነው። ይህ ሕይወት ለእግዚአብሔር የማይገዛ ነው (ሮሜ 8፥7)።

ዳግም በምንወለድበት ጊዜ አዲስ ሕይወት በውስጣችን ይፈጠራል። ነገር ግን ደግሞ በዚህ ሕይወት እስካለን ድረስ ሥጋ ከእኛ ጋር መኖሩን የማያቆም። ስለሆነ ትግሉና ጦርነቱም አይቋረጥም። ስለዚህ ነው አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን እስከ መጨረሻው ድረስ የሥጋ ፍላጐታችን በመንፈስ ቁጥጥር ሥር እንዲውልና እንዲሸነፍ ማድረግ የሚገባን።

ከአንድ ከፍተኛ መንፈሳዊ ልምምድ በኋላ ሥጋ ከእኛ ፈጽሞ የተወገደ እየመሰለን ልንሳሳት እንችላለን። አንድ ጊዜ በጣም ልጆች ሆነን የሁለት ሳምንት ኮንፍራንስ ለመካፈል ወደ ከፋ ጠቅላይ ግዛት ሄድን። አብዛኛዎቹ የኮንፍራሱ ተካፋዮች ከአዲስ አበባ የሄድን ወጣቶች ነበርን። በዚህ ኮንፍራንስ ላይ የምስክርነት ጊዜ ሲሰጥ ከጓደኞቻችን አንዱ ለመመስከር ተነሳና እንዴት እንደዳነና እንደተለወጠ፤ የውኃ ጥምቀትም እንደወሰደ በመግለጽ «ከአንግዲህ ወዲህ ሥጋ ሞቶአል። ነፃ ነኝ» ሲል አወጀ። የዚያን ጊዜ በአድሜ በሰል ያሉት የሚሲዮን ጠቢያው ኃላፊ ብድግ አሉና ያንን ወንድማችንን በስም ጠርተው በፈረጅ አማርኛ «ቆይ፥ ቆይ፥ ቀስ በል። ሥጋ ሞቷል ብለህ አትቸኩል። አንዳንድ ጊዜ እየመጣ ጤና ይሰጥልኝ ይልሃል!» አሉ። በጊዜው የሰውዬውን ንግግር ማንኛችንም አልወደድነውም። ነገር ግን ከቆየን በኋላ በሥጋና በመንፈስ መካከል ያለው ትግል በዚህ ሕይወት እስካለን ድረስ የሚቀጥል መሆኑን ስንረዳ፤ የእኚያን ሚስዮናዊ እርማት መቀበል ቻልን።

በሥጋና በመንፈስ መካከል የማያቋርጥ ጦርነት መኖሩ የታወቀ

ነው። በዚህ የመንፈስና የሥጋ ጦርነት ላይ ማሸነፍ የሚችለው እኔና እናንተ አንዲያሸንፍ የምንፈልገውና የምንረዳው ነው።

መንፈስ ሥጋን እንዲያሸንፍ የምንፈልግ ከሆነ በሁለት መንገድ ሥጋችን እንዲሸነፍ ማድረግ እንችላለን። ይህም በአንድ ወገን ሥጋን በማክሳት በሌላ ወገን መንፈስን በማጠናከርና በማወፈር ነው። ሥጋ እንዴት ይክሳል? እንል ይሆናል። እንድ የትግል ተጫዋች ጡንቻውን የሚያበረታና ኃይል የሚሰጠው ምግብ ካላገኘ፤ በሞራልም ካልተበረታታ የድሉን ዋንጫ አያገኝም። ሥጋም የሚፈልገው ነገር አለ። የሚፈልገውን ነገር ስንነሳው ይክሳል። አንዳንድ ክርስቲያኖች ተሸናፊ ሕይወት የሚኖሩት ይህንን ካለመረዳትና ካለማወቅ የተነሳ ነው። ለምሳሌ የሥጋን ስሜት የሚቀስቅሱ መጻሕፍትና ሲኒማዎች ሌሎችም የማይጠቅሙ ነገሮችን ነገሮችን መከታተል ሥጋን ይቀልበዋል፤ በውስጣችንም አያየለ እንዲሄድ ያደርገዋል። ሥጋ ፍላጐቱን ከተከለከለ ግን ይክሳል። መንፈስን ለማዳበር ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለመንፈሳዊ ሕይወት ይጠቅማሉ ያልናቸውን ነገሮች ሁሉ ማድረግና መከታተል ነው። ሥጋ ከስቶ ከቀረ መንፈስ ሁልጊዜ አሸናፊ ይሆናል። የምናከሳው ሥጋን በመሆን ፈንታ መንፈስን ከሆነ ግን መንፈስ በሥጋ ይዋጣል። በመንፈሳዊው ሕይወታችንም ደካሞችና ተሸናፊዎች እንሆናለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ ገላትያ 5፥16 ላይ የሚከተለውን ይመክረናል፥ «የሥጋን ምኞት እንዳትፈጽሙ በመንፈስ ተመላለሱ»። የሥጋን ምኞት የማንፈጽመው በመንፈስ ስንመላለስ ነው። በመንፈስ ለመመላለስ በመንፈስ ቁጥጥር ሥር መሆን አለብን። ስለዚህ ክርስቲያን ይህንን አውቆ በሥጋና በመንፈስ መካከል ያለውን ፍልሚያ ለመወሰን ራሱን ከመንፈስ ፍላጐት ጋር ማስተባበር አለበት። ይህ ለእድገታችን አስፈላጊ ነው።

9ኛ <u>የሞግዚቶች እንክብካቤ</u>

ለሕፃን እድገት የሞግዚቶች ጥሩ እንክብካቤ አስፈላጊነት ሳይጠቀስ መታለፍ የለበትም። ሕፃናት ምንም ነገር አያውቁም። ስው ካልረዳቸው በቀር የሚጎዳቸውን ነገር እንኳ አይለዩም። ሞግዚቶች ካልመገቧቸውም

አይበሉም።

በሕፃንነት ዘመን የሚደርስ ችግር ጠባሳ ሆኖ ይቀራል። በእኛ አገር ባህላችን ስለማይፈቅድ በልጅነቱ ዘመን ለደረሰበት ችግር በአደባባይ ወላጆቹን የሚወቅስና የሚያሳቅል ልጅ የለም። በምዕራብ አገሮች ግን ብዙ የመንፈስ መታወክ ያለባቸውና ልዩ ልዩ ችግር ያላቸው ወጣቶች ስሁሉ ነገር የሚወቅሱት ወላጆቻቸውን ወይም አሳዳጊዎችቸውን ነው። እንዲህ ካሉ ወጣቶች ብዙዎቹን የማናገርና የመምከርም ዕድል አጋጥሞኛል። ወቀሳቸውና ማሳቀላቸው ቢያስደነግጥም ወላጆች ወይም ሞግዚቶች ለታዳጊ ሕፃናት ማድረግ የሚገባቸው ጥንቃቄ ከፍተኛ እንደሆነም የሚያሳስብ ነው።

በመንፈሳዊ ሕይወትም ሕፃናት በሆንበት ጊዜ የሚደረግልን እርዳታ በእድገታችን ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣል። ስለዚህ ተመጣጣኝና ሚዛናዊ የሆነ ትምህርት የምንማርበትን ቤተክርስቲያንና መጋቢዎች ማግኘት ለእድገታችን አስፈላጊ ነው። እንደብልሃተኛ አናፂ በተመሠረተው መሠረት ላይ ሕይወታችንን የሚያንጹና የሚገነቡ ሰዎች ማጣት እድገታችንን ሊያዘገየው ወይም ሊያቀጭጨው ይችላል። ስለሆነም ለእድገታችን የሚጠቅሙንን ነገሮች ስንፈልግ ይህንንም አብረን ማሰብ ይገባናል።

በዚህ ምዕራፍ ከአንድ እስከ ዘጠኝ ተራ ቁጥር ድረስ ከዘረዘርኳቸው ነገሮች ሌላ ብዙ እድገታችንን የሚጠቅሙ ነገሮች አሉ። በዚህ ክፍል ያቀረብኩት ይጠቅማሉ ብዬ ያሰብኩትን ዋና ዋናዎቹን ብቻ ነው።

ይህንን ምዕራፍ ከመጨረሳችን በፊት ማሳሰብ የምፈልገው ነገር አለ። ይህም ሚዛን መጠበቅ አስፈላጊ እንደሆነ ነው። ይጠቅማሉ ብለን ከተማርናቸው ነገሮች በአንዱ ብቻ ማመዘን ሊጠቅመን አይችልም። አንዱን መርጠ የተቀሩትን መተው ጉዳት ሊኖረው ስለሚችል የሁሉንም ሚዛን መጠበቅ አለብን። ማደግ ያሳብን «በነገር ሁሉ» ነው ከተባለ የተመጣጠነ ሚዛናዊ አጠቃቀም ያስፈልገናል። ሚዛን ባንጠብቅ ወደ እንድ እቅጣጫ ብቻ እናዘነብላለን፥ ከተፈለገው ግብም አንደርስም።

ሚዛን መጠበቅ የእከሮባት እስፖርት ስሚያሳዩ ሰዎች እንዴት አስፈላጊና ጠቃሚ እንደሆነ መረዳት አያዳግትም። በአንዲት መስመር

ላይ የምትገለባበጠዋ ስፖርተኛ ያንን አስደናቂ አክሮባት ለማሳየት የምትችለው የሰውነቷን ሚዛን መጠበቅ ስለቻለች ነው። በአንድ አቅጣጫ ብታዘነብል ወድቃ መስበር ትችላለች። አንደዚሁ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ሚዛንን መጠበቅ ወደ አንድ አቅጣጫ ከማዘንበል ይጠብቀናል።

የመንፈሳዊ ሕይወት እንቅፋቶች

ምዕራፍ አሥራ አንድ

የመንፈሳዊ ሕይወት እንቅፋቶች

ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ መኖሩን የሚቀናቀን ጠላት አለው። ለአዝዕርትና ዕፅዋት ልዩ ልዩ በሽታና ትላትል ጠላቶቻቸው ናቸው። እንስሳትንም ልዩ ልዩ አውሬዎች ይገድሏቸዋል። ሰውም በሽታን የመሰለ ጠላት አለው።

ለመንፈሳዊ ሕይወት ዋናው ጠላት ዲያብሎስ ሲሆን ሌሎችም እንቅፋቶች ደግሞ አሉ። ከእነዚህም እንቅፋቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፦

1. <u>ጋጢአትን መለማመድ</u>፤ ክርስቲያን ጋጢአትን መጥላት አለበት። ለጋጢአት ያለን አመለካከት ቀላል ከሆነ መንፈሳዊነታችንን ክአደጋ ላይ እንጥላለን።

ክርስቲያን ሰው ስለ ሆነ ተሸንፎ ጋጢአት ላይ ቢወድቅ ወዲያው መጸጸትና ንስሐ መግባት አለበት። ጋጢአትን መናቅና ምንም እንደሌለበት መገመት ከጥፋት ላይ ያደርሳል።

በመጀመሪያው መቶ ዓመት ላይ የሚገኙ ገዥዎች ክርስቲያኖችን ለማጥፋት ስላደረጉት ብዙ ጥረት ታሪክ ይነግረናል። ክርስትናን ለማጥፋት ካለመቻላቸውም በላይ ለማጥፋት የደረጉት ሙከራ የበለጠ የአማኞችን ቁጥር እንዲጨምር አደረገ።

ገዥዎቹ የአሰቡት ሁሉ ስላልተሳካ ተበሳጭተው ክርስትናን ለማጥፋት የሚችሉበትን መንገድ ለመነጋገር ክፍተኛ ሸንጎ ስበሰቡ። በጉባዔው ላይ የተገኙትም ተሰብሳቢዎች በየተራ እየተነሱ ክርስትናን ያጠፋል ብለው ያሰቡት ዘዴ ፦ አማኞችን ማሰር፥ መግረፍና መግደል

የሚሉት ሀሳቦች ነበሩ። ነገር ግን ክዚህ በፊት ይህ ሁሉ ተሞክሮ በሰዎች ልብ ውስጥ ያለውን የክርስቶስ ፍቅር እሳት ምንም እንዳላጠፋው ገዥዎቹ ያውቁ ስለ ነበር በቀረበው ሀሳብ አልረኩም። በዚህ ዓይነት ሸንጐው ሲመክር ክዋለ በኋላ ክርስቲያንን ምን ያጠፋዋል? የሚለው ጥያቄ መልስ ሳያገኝ በእንጥልጥል እንዳለ ሊበታተን ይነሳል። በዚህ ጊዜ አንድ ሰው ተነሳና «ሰሙኝ! እንድ ጊዜ ብቻ አድምጡኝ! ክርስቲያኖችን ማጥፋት የሚችለው ስደት መከራና ሞት አይደለም። እንደምንም ብለን ጋጢአት እንዲያደርጉ ብናደርጋቸው፤ ቀስ በቀስ ማንም ላይነካቸው ይጠፋሉ። ምክንያቱም የክርስቲያኖች ፀር የሆነው ጋጢአት ግለታቸውን ያጠፋል፤ ድፍረታቸውን ይወስዳል፤ ኃይላቸውን ይሰርቃል፤ ሕይወታቸውንም ያደርቃል» ሲል ተናገረ። ገዥዎቹም ክቀረበው ሀሳብ ሁሉ አስደሳች ሆኖ ያገኙት ይህንን በመጨረሻ የቀረበውን ሐሳብ ስለ ነበር ክርስቲያኖችን በጋጢአት ለማደናቀፍ ትልቅ ዘመቻ ማድረግ ጀመሩ ይባላል።

እንደ ጋጢአት ሕይወትን የሚያደናቅፍ ነገር የለም። የጽድቅ ጠላት ይህንን ያውቃል። ስለዚህ ክርስቲያን በጋጢአት እንዲኖር ማለትም ንስሐ ሳይገባ ጋጢአት ተስማምቶት እንዲኖር የተለያየ የተንኰል ዘዴውን ይዘረጋል።

ክርስቲያን ጋጢአትን መሸሽ አለበት። በጋጢአት ክወደቀም በቶሎ በንስሐ መስተካከል አለበት። (1ዮሐ. 1፥7) መንፈሳዊ ሕይወቱ ከመደናቀፍ ሊጠበቅ የሚችለው በዚህ ነውና።

2. <u>ሕይወትን ስድ መልቀቅ</u>፤ የክርስትና ሕይወት ክርስቶስና ሐዋርያቱ በጻፉልን መመሪያ መሠረት የሚመራ ሕይወት ነው። ያለምንም መመሪያ ሕይወታችንን እንደፈለግነው ስድ ልንለቀው አንችልም። የግድ ዲሲፕሊን ሊኖረን ይገባል።

አንዳንድ አማኞች ለምሳሌ የእስተሳሰብ ልቅነት የሚያመጣውን ጉዳት አያውቁም። ስለሆነም ወደ እእምሮአቸው ለሚመጣውና ለሚያስቡት ሀሳብ ገደብና ወሰን የሚሰጥ ምንም መመሪያ የላቸውም።

ሁሉ ነገር አስቀድሞ በሰው አእምሮ ውስጥ የነበረ ሀሳብ ነው። በሰማይ የሚበረው አውሮፕላን፥ በምድር የሚሽከረከሩት ተሽከርካሪዎች

ሌሎችም ነገሮች ሁሉ ከመሠራታቸው በፊት በሰዎች ሀሳብ ውስጥ ነበሩ።

በተግባር የምንፈጽማቸውም ነገሮች ሁሉ አስቀድሞ በሀሳብ የተውጠነጠኑ ናቸው። ለዚህ ነው በአእምሮአችን ለሚመጣው ሀሳብ ሁሉ ልቅ መሆን አደገኛ የሚሆነው። ያዕቆብ በመልእክቱ ሊያስጠነቅቅ፥ «ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች» ይላል ያዕቆብ 1፥15 ሰሎሞንም በምሳሌ 23፥7 ላይ «ሰው በልቡ እንደሚያስበው ነው» ይላል። የምናስበውን እናደርጋለን። የምናደርገው ማንነታችንን ከገለፀ ለአስተሳሰብ ዲሲፕሊን ያስፈልጋል። ጳውሎስም መንፈሳዊ ሰው ክርስቲያናዊ ባሕርይ እንዲኖረው አስተሳሰቡ በምን በምን ላይ ማተኮር እንዳለበት በመዘርዘር፥ «እነዚህን አስቡ» በማለት በመልእክቱ መመሪያ ይሰጣል (ፊሊጵ. 4፥8)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «የተራራው ስብከት» በመባል በሚታወቀው ትምህርቱ በሀሳብ በሚደረጉ ወይም በድርጊት በሚፈጸሙ ኃጢአቶች መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ አስተምሮአል። ለምሳሌ ያህል ማቴዎስ 5፥27 ላይ የተጠቀሰውን ማቅረብ ብቻ በቂ ነው። «አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሌት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል»

በአስተሳሰብ ኃጢአት መሥራት ከተቻለ የአስተሳሰብ ዲሲፕሊን ሊኖረን ይገባል። እኛ ራሳችን ባናመነጨውም እንኳ ዲያብሎስ ወደ አእምሮአችን ሀሳብ መዝራት ይችላል። ስለዚህ ዲስፕሊን ያስፈልገናል ስንል ሀሳቡን እንዳይፈጠር እናቆማለን ለማለት አይደለም። ነገር ግን ሀሳብ ተግባራዊ የሚሆነው በአእምሮአችን ከተፀነሰ በኋላ በተግባር እስኪውል ድረስ ተደላድሎ ሲቀመጥ ነው። ሀሳብን ተግባር ከመሆኑ በፊት አስቀድሞ ማስጨንገፍ ይቻላል። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የማይሄደውን ማንኛውንም ሀሳብ በመቀበልና በማስተናገድ ፈንታ መቃወም አለብን። በጸሎት፥ በቃሉ፥ በሌሎችም መንገዶች ሁሉ ሀሳቡን ብንቃወመው ከአእምሮአችን ይወጣል። ለዚህ ነው ብዙ ክርስቲያኖች መጥፎ ሀሳብ አእምሮአቸውን ዘልቆ ሲገባ ከመስረጹ በፊት በኢየሱስ ስም እየገሰጹ የሚያባርሩት።

ክፉን ሀሳብ ማቆም የምንችለው ክፉ ማሰብን ስንተው ነው። ደግ

ሥራ መሥራት የምንችለውም ደግ ነገር ማሰብ ስንለማመድ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የፊሊጲስዩስ ክርስቲያኖች ማሰብ ስለሚገባቸው ነገሮች የነገራቸው ከዚህ የተነሳ ነው። የአስተሳሰብ ዲስፕሊን ማጣትና ልቅ መሆን ለመንፈሳዊ ሕይወት አንቅፋት ይሆናል።

አንዳንድ ሰዎችም ዓለማዊውን ነገር ሁሉ አቅልለው ስለሚመለከቱ «ጉዳት የለውም፤ ምንም አይደለም» የሚል አስተሳሰብ አላቸው። ብዙ ጊዜ ሰዎች የናቁትና ያቃለሉት ነገር ለሕይወታቸው ወጥመድ ሲሆን አይቻለሁ። ትናንሽ ነገሮችን ደጋግመን ስንለማመዳቸው እየወደሱና እየመነደሉ ሄደው በኋላም ጥፍር አድርገው የሚያስሩን ልማዶች ይሆናሉ። ከሕይወት መንገድ ወደኋላ አፈግፍገው የቀሩት ወንድሞቻችን ሁሉ በአንድ ቀን ዱብ ዕዳ ወርዶባቸው ያደረጉት ነገር አይደለም። ከእንደዚህ ያለ ደረጃ የሚደረሰው ከብዙ ቀን የኃጢአት ልምምድ ጥርቅም፥ የተነሳ ነው። ስለዚህ መንፈሳዊ ሕይወታችን ምንም አንቅፋት እንዳያጋጥመው በአስተሳሰባችንም ሆነ በሌሎች ነገሮች ሁሉ ክርስቲያናዊ ዲስፕሊን ይኑረን።

3. <u>ውልከስ መንፈሳዊነት</u>፤ ውልከስ መንፈሳዊነት የምለው መንፈሳዊ ያስኘናል በማለት ከልብ ሳይሆን በልማድ የምናደርጋቸውን ነገሮች ለመግለፅ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሌሎች ሰዎች ሲያደርጉአቸው በጣም መንፈሳዊ ናቸው ብለን የምንገምታቸው ነገሮች እኛንም ሰዎች በዚያ መልክ እንዲያዩን ብለን ልንቀዳቸው እንችላለን። አንዳንድ ንግግሮችም መንፈሳዊነትን በመግለጽ በኩል በቤተክርስቲያን አካባቢ የታወቁ ናቸው። ለምሳሌ፥ «ሃሌሉያ» ብሎ መጮኽ፤ «ጌታ ይመስገን» (ፕሬይዝ ዘ ሎርድ) ብሎ መናገርና «አሜን» ማለት፥ የመሳሰሉትን እዚህ ላይ መጥቀስ ይቻላል።

«አሜን»፥ «ጌታ ይመስገን»፤ ወይም «ሃሌሉያ» በማለት ምንም ስህተት የለም። እነዚህ የክርስቲያን ቃሎች ናቸው። በአስፈላጊው ቦታና በተስማን ጊዜ እነዚህን ቃሎች ማወጁን አምንበታለሁ። ራሴም ማወጅ የምወዳቸው ቃሎች ስለሆኑ ማንንም እንደዚያ ከማለት ተስፋ ማስቆረጥ አልፈልግም። እኔን የሚያሳስበኝ በእድገት ላይ ያለ ክርስቲያን ከልቡ እነዚህ ነገሮች እስኪፈልቁ በመጠበቅ ፈንታ፤ መንፈሳዊነቱን

የሚገልጹለት ስለሚመስለው ብቻ ቢጠቀምባቸው፥ ዕድገት ማለት እነዚያን ነገሮች መናገር ብቻ ስላይደለ፥ እድገቱ በአጭር ተቀጭቶ እንዳይቀር ነው። የታወቁ ክርስቲያናዊ ቃላትን ማስማት ማንንም መንፈሳዊ አያደርግም።

በተጨማሪም ክልብ ያልሆነ ትህትና እንደ ፀሐፍትና ፈሪሳውያን ለታይታ የሚደረግ ሃይማኖታዊ ተግባሮች ሁሉ ውልክስ መንፈሳዊነት ስለሆኑ መታረምና መወገድ አለባቸው።

4. <u>ስንፍናና ቸልታ</u>፤ መጽሐፍ ቅዱስ ስንፍና ስለሚያደርሰው ጉዳት የሚናገረውን ሁሉ በጹሑፍ ማስፈር ቢፈለግ በዚህ ርዕስ ብቻ አንድ ትልቅ መጽሐፍ መጻፍ ይቻላል። ስንፍና ሕይወት ጐጂ ነው። ሰነፍ ከሆንን ኑሮአችን ብዙ ይጐዳል። መንፈሳዊ ሕይወትም በስንፍና ምክንያት ይጐዳል። የነፍሳችን ባላጋራ ዲያብሎስ ራሱ እንኳን በሰነፍ እንደሚፈተን በሌላ በማንም አይፈተንም። ዲያብሎስ ተንኮል ስለሚሠራ በመጽሐፍ ቅዱስ «ፈታኝ» የሚል ስም ይሰጠዋል። ፈታኝ የሆነው ዲያብሎስ ራሱ መልሶ የሚፈተነው በሰነፍ ክርስቲያን ነው። ስለዚህ ከዚህ በፊት ያልተጠቀመበትን ተንኰልና የእመጽ ሀሳብ ሁሉ ለመከራ የሚሠራበት (ላብራቶር) የሰነፍ አእምሮ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ስንፍናን የሚያወግዘው ለዚህ ነው።

ቸልታ ደግሞ በጐውን እያወቁ በማድረግ ፈንታ ዝም ማለት ነው። ቸልታ የትጋት ተቃራኒ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው ሰነፍ እንዳይሆን፤ ቸልተኝነትም እንዳያጠቃው እያስጠነቀቀ በሁሉ ነገር ትጋት እንዲኖረው ይመክራል። «ትጉና ጸልዩ» ሲል ጌታ ያዘዘውን ቃል ለምሳሌነት ብንመለከት፤ ለጸሎት ትልቁ እንቅፋት «ስንፍና» ወይም «ቸልታ» እንደሆነ ልንገነዘብ እንችላለን። ጸሎትን ቸል የሚል ክርስቲያን ወይም ተነስቶ ለመጸለይ ተራራ የሚመስለው ሰነፍ የትም አይደርስም። ለዲያብሎስም ወጥመድ የተጋለጠ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ጌታ «ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ» ባላለም ነበር (ማቴ. 26፥41)።

በስንፍና ምክንያት ቃሉን የማይመገብ ክርስቲያን በራሱ ሕይወት

ላይ ወንጀል ይፈጽማል። ቸል የሚለውም እንደዚያው ነው። የቅዱሳንን ሕብረት ቸል የሚል ወይም ወደ ቅዱሳን ስብሰባዎች እንዳይመጣ የሚሳነፍ ሰው ትልቅ መንፈሳዊ በረከት ያመልጠዋል። እግዚአብሔር በረከቱ እንዲወርድ ያዘዘው በቅዱሳን ሕብረት ውስጥ ነው። (መዝ. 133)። ከዚያ መጉደል ከበረከት መጉደል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክት፥ «በአንዳንዶች ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው መሰብሰባችንን እንተው፤ እርስ በእርሳችን እንመካከር አንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ» ይላል (ዕብ. 10፥25)።

የተሰጠን አዲስ ሕይወት ክቡር ነው። ይህንን እውነት ካወቅን በኋላ ትጋት ቢጐድለን ወደ ፊት እንጸጸትበታለን። የእግዚአብሔር ቃል፥ «እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንል እንዴት እናመልጣለን?» ሲል የሚያስጠነቅቀን ለዚህ ነው (ዕብ. 2፥3)።

ስንፍናና ቸልታ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ታላላቅ እንቅፋቶች ናቸው። አስቀድሜ እንዳልኩት በእነዚህ በሁለቱ ሀሳቦች ላይ ብዙ ዝርዝርና ትምህርት ማቅረብ ይቻላል። ይሁን እንጂ የዚህ ክፍል ዋና ዓላማ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ጐጂ የሆኑትን ነገሮች ለመጠቆም ብቻ ስለሆነ በሀሳቡ ላይ ሰፈ ጥናት ማድረጉን ለእንባቢው እተወዋለሁ።

5. <u>ሌላውን መምሰል (ሰውን ኮፒ ማድረግ)</u>፤ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ምሳሌ ከሚሆኑልን ሰዎች ሕይወት ትምህርት መውሰድ ተገቢ ነገር ነው። በተለይም ገና ወደ ጌታ የመጡ ክርስቲያኖች የክርስትና ሕይወት ልምምድ ስለሚያንሳቸው ምሳሌ የሚሆኑላቸውን ሰዎች ማግኘት እለባቸው። ለክርስትና ሕይወት እንቅፋት ነው የምለው ከሰዎች ሕይወት ምሳሌነት ማግኘቱን አይደለም።

ወደ ጌታ ከመጣን በኋላ ሁላችንም ስለ ክርስትና ማወቅ ያለብን ሐቅ እለ። ክርስትና ክርስቶስ እንደሆነ ተደጋግሞ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎአል። የክርስቲያን ግቡ ክርስቶስን መምሰል እንደሆነም ከመጀመሪያው ጀምሮ የተመለከትነው ሐሳብ ነው። በእድገት ማስጋሴ መሮጥ ያለብን ወደዚህ ልንመስለው ወደሚገባ ጌታ ነው።

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ አማኞች ይህ እውነት ይሰወርባቸውና

ምሳሌ ይሆነናል ብለው በሚያስቡት አንድ ሰው ላይ ያተኩራሉ። እንደዚያ ሰው ለመምሰልም ይደክማሉ። ይህ ሁኔታ ችግር ውስጥ የሚጥለው በዚያ ሰው ሕይወት ጉድለት በሚያገኙበት ጊዜ ብቻ አይደለም። ሰውዬው ጉድለት ባይኖርበትም እንኳን የእድገታቸው ግብ እሱን በማድረጋቸው እድገታቸው ባጭር ይቀራል። ይህም የሚሆነው ያንን ሰው ኮፒ እያደረጉት ሲሄዱ ሲያድጉ የሚችሉት የዚያን ሰው ያህል ብቻ ስለሆነ ነው። ከዚያ ኮፒ ከሚያደርጉት ሰው በላይ ማደግ ስለማይችሉም። የዚህ ዓይነትም ግብ በቀላሉ ይደርስባቸዋል። እነርሱንም ስህተት ላይ ይጥላቸዋል። በተጨማሪም ሕይወታቸውን ምሳሌ ከእደረጓቸው ሰዎች ሕይወት ጋር እያወዳደሩ የደረሱባቸው ወይም የበለጡአቸው መስሎ ከታያቸው በዕድገታቸው ላለመቀጠል ፈተና ውስጥ ይገባሉ። ወደፊትም ለመራመድ አይችሉም።

ለከርስትና ሕይወት ምላሌ (ሞዴል) የሚሆነን ክርስቶስ ከሆነ ግን እድገታችን ከተወሰነ ቦታ ባጭሩ አይቆምም። በዚህ ምድር መቶ ዓመት ብንኖር እንኳን እሁንም በእድገት ጉዳና ወደ ፊት ለመዘርጋት እንችላለን። ያለምንም እንቅፋት ወደፊት መራመድ የምንችለው ይህ ሀሳብ ዋና መመሪያችን ሲሆን ነው።

ዕድገትና ምርጫ

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

እድገትና ምርጫ

የሰው ልጅ ከእንስሳትና ከሌሎች ፍጥረታት የሚለይበት ሦስት ታላላቅ ምክንያቶች አሉ። እነዚህ ሦስት ነገሮች ፈጣሪ አምላክ በቀጥታ ለሰው ልጅ ሰይቶ የሰጣቸው መብቶች ናቸው። እነርሱም ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1ኛ. <u>ነፃነት</u>፤ አግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ከሙሉ ነፃነት ጋር ነው። እንዳንድ ተቃዋሚዎች እግዚአብሔር በዔደን ገነት ውስጥ ለምን ያችን ዛፍ ተከለ? ለምንስ አዳም እንዲፈተንና እንዲበላ አደረገው? እያሉ ይጠይቃሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን እንዴት እንደፈጠረው ብዙ እያሰተውሉም። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር «በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር»አለ፥ ዘፍጥረት 1፥26። በሰድሰቱ የፍጥረት ቀናት ከተፈጠሩት ፍጥረታት ውስጥ ከሰው በቀር አግዚአብሔር በራሱ መልክና ምሳሌነት የፈጠረው ሌላ ምንም ነገር የለም። ሰው ብቻ በአምላኩ መልክ የተፈጠረ ክቡር ፍጥረት ነው።

እግዚአብሔር በመልኩና በምሳሌው ሰውን ሲፈጥረው ሙሉ ነፃነትን አጐናጽፎ ነው። ነፃነት ባለበት ሁሉ <u>ፈቃድናምርጫ</u> ይኖራል። ሰው ከራሱ ምርጫና ፈቃድ ውጭ ምንም እንዲያደርግ አይገደድም።

«ነፃነት» ለሰዎች ሰጦታ ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠራቸውን ሰዎች አዳምና ሔዋንን ዛሬ ፈረንጆች «ሮቦቶች» የሚሉት ነገር ዓይነት እድርጐ በፈጠራቸው ነበር። «ሮቦቶች» የራሳቸው ፈቃድ የላቸውም። በሰው በቀረበላቸው የአሠራር ቅንጅት (ፕሮግራም እንደ ተደረጉት) ብቻ ይሠራሉ፤ እንዲነኩ የታዘዙትን ይነካሉ፤

ምስጋና

ይህንን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ በሀሳብና በጸሎት ድጋፍ ላደረጉልኝ ሁሉ ምስጋና አቀርባለሁ። በተለይም አቶ ጎሩይ ጽጌ ጽሑፉን በማተሚያ ኮምፒዩተር በማዘጋጀትና በማረም፤ አቶ እቢይ ግርማ በመጽሐፉ ጎትመት፥ እንደዚሁም አቶ አዲሱ ወርቁ በሃሳብ ማበረታታት ሰላደረጉልኝ ያልተቆጠበ እርዳታ ከልብ አመሰግናለሁ።

***

አላቃለለም። «ማንም የሚወድ ቢኖር ይከተለኝ» ... «ብትወዱ ትዕዛዜን ጠብቁ» የሚሉትን ዓይነት ልመና ብቻ ነው ያቀረበው። ሰዎች እርስ በእርሳቸው ይህንን ትልቅ መብት ይጋፉ እንጂ እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠውን መብት ከማንም አልወሰደም።

2ኛ. ፈቃድ፤ ነፃነት ብቻውን አይመጣም። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ነፃነት የሚመጣው ፈቃድን፥ ምርጫንና ኃላፊነትን ይዞ ነው። ሰው ነፃነት ሰለተሰጠው ከዚህ ከተሰጠው ነፃነት ጋር አብሮ የሚሄድ የራሱ ፈቃድ አለው። በነፃነቱ ደስ ሲለው የሚችለው የራሱ ፈቃድ ሰላለው ነው። የምንፈቅደው ነገር አለ፤ የማንፈቅደውም ነገር አለ። ከፈቃዳችን ውጭ የሚደረግ ነገር ሁሉ ግዴታ ነው። ስለምንኖርበት ቦታ፤ መብላት ሰለምንፈልገው ነገር፤ ሰለ ሌላም ብዙ ነገሮች የራሳችን የሆነ ፈቃድ አለን። እግዚአብሔር ፈቃዳችንን ያከብራል።

3ኛ. ምርጫ፤ ከነፃነትና ከፈቃድ ጋር ለሰው የተሰጠው ሦስተኛው ችሎታ፥ የሚፈልገውን መምረጥነው። ሥጋ ለብሶ የተፈጠረ ሰው ሁሉ ምርጫ አለው። አዳም ምርጫ ነበረው። ምርጫ የሚኖረው ከአንድ በላይ የሆኑ ነገሮች ሲኖሩ ነው። ሰለዚህ በዔደን አዳም ምርጫ ነበረው። እያንዳንዱ ምርጫ ወዴት እንደሚያመራም አሻሚ ባልሆነ አነጋገር በግልጽ ለአዳም ተነግሮት ነበር። መታዘዝ ምርጫ ነው። አለመታዘዝም ምርጫ ነው። ግዴታ ከታከለበት መታዘዝ ነፃነትን ይገፋል። በፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነገር ብቻ ምርጫ ይባላል። ሰለዚህም ኃላፊነትን መቀበል ምርጫ ነው። እግዚአብሔር የሚለውን መስማት ምርጫ ነው። ከርሰቶሰን መከተልና ከርሰቲያን መሆን ምርጫ ነው። የማንደድበት ነገር ሁሉ ምርጫ ነው። በዚህ ረገድ እኛ «ሲያል» ወይም «መንግሰተ ሰማይ» በማለት የምንጠራቸው ቦታዎች እንኳን በመሠረቱ የሰው ምርጫዎች ናቸው። እንደዚህ በሕይወት የሚያጋጥመን ነገር ሁሉ ምርጫ ካለው በመንፈሳዊ ሕይወት ያለንም ነገር ሁሉ በምርጫችን ላይ ይመረኰዛል። ስለሆነም በመንፈስ ማደግና አለማደግም ምርጫ

ይሆናል።

«ምርጫ» በመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ሁሉ የምናነበው ሀሳብ ነው። እግዚአብሔር ለእሰራኤላውያን የተናገረውን ቃል ለምሳሌነት ብንጠቅስ እንዲህ ይላል፥ «በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳሰቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በእናንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፤ አግዚአብሔርም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይሰሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ፥ እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ።» ዘዳ. 30፥19-20፤ በዚህ ጥቅስ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ትክክለኛውን ምርጫ አንድናደርግ ይፈልጋል። ቃሉንም የሰጠን ዋና ምክንያት በጉ ፈቃዱን እንድናውቅ፤ ከፈቃዱም የሚያወጣን ምን አንደሆነ አውቀን በኋላ ከመፀፀት ዛሬ ጥሩ ምርጫ እንድናደርግ ነው።

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው ነገሮች አግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጣቸው መሠረታዊ መብቶች ናቸው። ሰው እነዚህ ከጐደሉት ከእግዚአብሔር የተሰጡት ሰብዓዊ መብቶቹን ተገፏል።

ነፃነት፥ ፈቃድ፥ ምርጫ የሚያመሩት ወደ ውሳኔ ነው። እነዚህ መብቶቻችን በግል ሕይወታችን ጉዳይ ከሚያጋጥሙን ምርጫዎች መካከል ይጠቅመናል የምንለውን ነገር ለማድረግ እንድንወሰን ይረዱናል።

በምንም ነገር ውሳኔ ላይ ሰንደርስ ውሳኔያችን ውጤት አለው። ውሳኔ አቅጣጫን ይሰጣል። ከሁለት መንታ መንገዶች ላይ ቆሞ ከቀረቡለት ምርጫዎች አንዱን በመውሰድ በዚህ በኩል እሄዳለሁ ብሎ የወሰነ ሰው የሚሄድበት አቅጣጫ የተወሰነ ነው። ወደ ምዕራብ ያለ ወደ ምዕራብ ያዘግማል። ወደ ምሰራቅ መሄድ የፈለገም ወደ ምሰራቅ ይሄዳል። ወደ ሰሜን ለመሄድ የወሰነም ወደ ሰሜን ይገሰግሳል። የምንወሰነው ውሳኔ ሁሉ የምናመራበትን አቅጣጫ ይተልማል። በወንጌል ውሰጥ ጌታ ሰለጠባቡ መንገድና ሰለሰፊው መንገድ ሲናገር ሁለቱም ወዴት አቅጣጫ እንደሚወስዱም ሞምር አስተምሮአል። (ማቱ.

7፥13-14)። ለሥጋዊው ወይም ለመንፈሳዊው ሕይወት የምናደርጋቸው ውሳኔዎች ልንሄድበት የምንችለውን አቅጣጫ ይወስናሉ።

አቅጣጫ ደግሞ የምንደርስበትን ግብ ይወስናል። ከየት መነሳታችንና ወዴት አቅጣጫ መሄዳችን ብቻ ሳይሆን ይዋል ይደር እንጂ ከቀጠልንበት የት መድረሳችንንም ይወሰናል። ጌታ ስለ ሰፊውና ስለ ጠባቡ መንገድ እንደነገረን ጠቅሰናል። እነዚያ መንገዶች የሚያደርሱበትንም አቅጣጫ አይተናል። ሰው ህሳቡን የመለወጥ መብት አለው። መሳሳቱን ሲያውቅ፥ ከፈለገ ይመለሳል። የንስሐ መንገድ የሚሰበከውና ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ የሚባለውም ለዚህ ነው። ነገር ግን ከተሳሳትንበት አቅጣጫ መመለስ ከሌለ ያመራንበት አቅጣጫ ብንወድም ባንወድም የሚያደርሰን ግብ አለ።

አንዳንድ ሰዎች በተሳሳተው አቅጣጫ ሄደው ከሚፈልጉበት የሚደርሱ ይመስላቸዋል። አቅጣጫና ግብ ያላቸውን ግኑኝነት አያስተውሉም። በሰፊው መንገድ ተጉዞ (ካልተመለሱ በቀር) መንግስተ ሰማይ መድረስ አይቻልም።

ስለዚህ፥ ውሳኔ አቅጣጫን፤ አቅጣጫም ግብን ካመጣ፤ ለምንወሰነው ውሳኔ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። አንዳንድ ሰዎች የውሳኔ ሰዎች አይደሉም። የትኛውንም አቅጣጫ ላለመከተል ሲሉ ውሳኔ አይወስኑም። በተለይ በመንፈሳዊ ጉዳይ አለመወሰን ራሱ ውሳኔ ነው።

ውሳኔን በሚመለከት መንገድ የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ሮናልድ ሬጋን የተናገሩትን መጥቀስ አስፈላጊ ይመስለኛል። ሚስተር ሬጋን ገና ልጅ በነበሩ ጊዜ የራሳቸውን ውሳኔ ሌላ ማንም ሰው እንዳይወስንላቸው ከአንድ ሁኔታ ትልቅ ትምህርት እንዳገኙ ያወራሉ። ይህም ገና ልጅ ሳሉ አክስታቸው ጫማ ሊያሰሩላቸው ይዘዋቸው ወደ ገበያ ይወጣሉ። ከጫማው ቦታ እንደደረሱ አክስታቸው ለልጃቸው ጫማ እንዲሰራላቸው ይጠይቃሉ። የዚህ ጊዜ ሚስተር ሬጋን እንደሚሉት ጫማ ሰፊው፥ «ማሙሽ፥ ምን ዓይነት ጫማ እንድሰራልህ ትፈልጋለህ? ከፊቱ አራት ማዕዘን የሆነውን ወይስ ሾል ያለውን? የትኛውን ትመርጣለህ?» ሲል ይጠይቃቸዋል። እሳቸውም የዚህን ጊዜ

ዝም ይሉና መልስ ሳይሰጡ ያቀራሉ። ጫማ ሰፊውም እግራቸውን ለካና እንደገና «በል በሌላ ጊዜ መጥተህ የትኛውን ዓይነት እንድሠራልህ እንደምትፈልግ ንገረኝ» ብሏቸው ይለያያሉ። ሚስተር ሬጋን ግን ሄደው ለጫማ ሰፊው ውሳኔያቸውን ሳይነግሩት ቀሩ። አንድ ቀን በአጋጣሚ ጫማ ሰፊው ያገኛቸውና «አሁንም አልወሰንክም? በል ነገ መጥተህ ንገረኝ፥ ያለዚያ የሚቀጥለው ሳምንት በመስለኝ መንገድ ጫማህን ሰርቼ እሰጥሃለሁ።» ይላቸዋል። እሳቸውም ውሳኔያቸውን ለመናገር ሳይሄዱ ይቀራሉ። በመጨረሻም ጫማው ተሠርቶ ይላከላቸዋል። ሚስተር ሬጋን የጫማውን እሽግ በሚከፍቱበት ጊዜ ጫማው አንዱ እግር ባለ አራት ማዕዘን ሌላኛው ሹል ሆኖ አገኙት። ከዚያ ወዲህ ጫማውን ባዩ ቁጥር ሰላልተደሰቱ የደረሱበትን ውሳኔ ሲናገሩ «ከዚያ ከልጅነት ጊዜዬ ጀምሮ የውሳኔን አስፈላጊነትና በተለይም እኔ መወሰን የሚገባኝን ውሳኔ ሌላ ሰው እንዲወሰንልኝ ማድረግ ትክክል እንዳልሆነ ተማርሁ» ይላሉ።

መንፈሳዊ ሕይወት ምን እንደሆነ፤ እንዴት ማደግ እንዳለበት፤ የእድገት አቅጣጫውና ግቡ፤ ከእድገት ጉዳና የሚያደናቅፉን መሰናክሎችና ለእድገት የሚጠቅሙንም ነገሮች ምን እንደሆኑ እስከአሁን ድረስ በሰፊው ተምረናል። ለቀረበልንም ምርጫ የሚሻለውን ውሳኔ ማድረግ የእኛ ፈንታ ነው።

እስከ አሁን የተመለከትናቸው ነገሮች ምርጫ መሆናቸውን ባለመዘንጋት በክርስትና ሕይወት ዓላማ የሚኖረን ቁርጥ ውሳኔ ሊኖረን ነው። ውሳኔ ዓላማን ያመጣል። ዓላማ ካለን አቅጣጫና እርምጃ አለን። ዓላማ የሌለውም የትም አይደርስም። ከላቲን አሜሪካ መሪዎች መካከል አንድ ሰው፥ «ዓላማ ከሌለህ የትኛውም መንገድ ካሰብክበት ያደርሰሃል» ይሉ ነበር። ያሰበው የትም ላለመድረስ ስለ ሆነ ያንን የሚነፍገው ምንም ሰለሌለ ነው። በአሜሪካ ለሕፃናት ከተሠሩት ፊልሞች መካከል አንድ የታወቀ ፊልም ላይም፤ ልጅቱ ሦስት መንታ የሆነ መንገድ ላይ ደርሳ የትኛውን መንገድ መከተል እንዳለባት ግራ ስትጋባ ትታያለች። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች ድመትን ታገኛለች። እሷም «ውሮ! እባክህን ንገረኝ፤ ከእነዚህ ከሦስቱ መንገዶች በየትኛው ልሂድ?» ስትል ድመትን ጠየቀችው። ድመትም ትክክለኛውን አቅጣጫ ለማሳየት ልትሄድ የምትፈልግበትን ማወቅ አስፈላጊ ስለሆነ፥

«ትከከለኛውን መንገድ እንድጠቁምሽ ልትሄጂ ያሰብሽበትን ቦታ ንገሪኝ» ሲል ጥያቄዋን በጥያቄ ይመልስላታል። እሷም «ወዴት እንደምሄድ አላውቅም» ትላለች። ድመትም ሳቅ ይልና እንደገና፥ «በይ እንዲህ ከሆነማ የትኛውንም መንገድ ብትከተይ ምንም አይደለም» ይላታል። በከርሰትና ሕይወት ከሚያሳዝኑት ነገሮች አንዱ ለሕይወት ምንም ዓላማ የሌላቸውን ሰዎች ማየቱ ነው። ሕይወት ትርጉም የሚኖረው ዓላማ ሲኖር ነው። ጌታ ኢየሱስ እረኛ እንደ ሌላቸው ሰዎች ወዲያና ወዲህ ሲቅበዘበዙ ያያቸውና ያዘንላቸው ሰዎች እነዚህን የመሳሰሉት ናቸው።

ዓላማ ያለው ኃይል አለው። መከራንና ፈተናን ሁሉ አልፎ ይሄዳል። ዓላማ ያለው ትዕግሰት አለው፤ በመንገድ ላይ የሚያጋጥመውን ችግር ሁሉ አልፎ ካሰበበት ይደርሳል። ይህ ሁሉ የሚሆነው በተሰጠን ነፃነትና ምርጫ ተጠቅመን ውሳኔ ለማድረግ ስንችል ነው። ለማደግ ከፈለግን እስከ አሁን ያገኘናቸው ምክሮች ሊጠቅሙን ይችላሉ።

ትከከለኛውን ምርጫና ውሳኔ ለማድረግ እንዲረዳ በማሰብ የአወቅሁትንና የተማርሁትን በመለማመድም ላይ ያለሁትን ነገሮች በነጭና በጥቁር ቀለም አሰፍሬ ይህንን መጽሐፍ በትህትና ሳቀርብ አንባቢው ሁሉ በሃሣቡ እንዲጠቀም ልባዊ ምኞቴና ጸሎቴ ነው።

ጥያቄና አስተያየት ቢኖርዎ በሚከተለው አድራሻ ይጻፉልን።

Ethiopian Christian Fellowship Church
P.O.Bx 740581
Houston, TX. 77074, USA